ቀይ ሰይጣን

መንፈሳዊ ቴአትር

በመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ኆኅተ መንግስተ ሰማያት ሰንበት ት/ቤት ኪነ ጥበባት ክፍል የተዘጋጀ

ድርሰት፡-ኃይሉ ለገሠ

“ቀይ ሰይጣን”

አንዳንድ ነገር

ተውኔቱ በአንድ ገቢር እና በስድስት ትእይንትቶች የተከፋፈለ በቤተሰብ ዙርያ የሚያጠነጥን ከአሳዛኝ እና ልብ አንጠልጣይ ዘውግ ውስጥ ይመደባል። መነሻ ሀሳቡ በንጉስ ዳዊት ልጆች ላይ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ ወጥልቦለድ ተውኔት ነው።

ግዜው ባለንበት ዘመን ነው። ቦታው ደግሞ ከአዲስ አበባ በውጭ ማንያውም ክፍለ ሀገር። ተውኔቱ ሀይማኖትን እንጂ የትኛውንም ባህልና ልማድ አይከተልም። የገጸ-ባህርያቱ¨የመግባቢያ ቋንቋቸው አማርኛ ቢሆንም በየትኛውም ቋንቋ ቢተረጎም የሚያ መጣው ችግር አይኖረውም።

የትእይንቶቹ አመዳደብ

ጽሀፈት፡- ተውኔቱ የተውኔት አጻጻፍ ስልትን የጠበቀ ከትእይንት አንድ እስከ ፍፃሜው ፍሰቱን እንደያዘ የእውቂያ አሰረጫጨት፣ እውቂያ+ ትውስብ፣ ትውስ+ ኡጠት ከዛም ልቀት በመጨረሻም በመፍትሄ አፈላለግ ይደመደማል።

የትዕይንቶቹ ፍሰት

ትዕይንት አንድ፡- ከገጽ 6-15:- እውቂያ አሰረጫጨት

ትዕይንት ሁለት፡- ከገጽ 16-29:- ትውስብ

ትእይንት ሶስት፡- ከገጽ 30-44:- ትውስብ+ ኡጠት

ትእይንት አራት፡- ከገጽ 45-58:- ጡዘት

ትእይንት አምስት፡- ከገጽ 59-68:- ጡዘት+ልቀት

ትእይንት ስድስት ከገጽ 69-78:- ጡዘት+ ልቀት+ መፍትሄ= ድምዳሜ።

ገጸ ባህርያት

እናት፡- እድሜያቸው 50 (ሀምሳ) የደፈሩ ወ/ሮ ናቸው። የአቢሲሎም፣ የስምኦን፣ የአምኖን፣ የትምአአር እና የራማ እናት ሲሆኑ ከግዜ በኋላ ምንነቱ ባልታወቀ በሽታ እጃቸው በድን እንዲሁም እንቅበታቸው ይዘገሃል እምነተ ጠንካራ በመሆናቸው መዳናቸውን በሀኪም ቤት ሳይሆን ከፈጣሪ ሚጠብቁ ልጆቻቸውን በስርአተ ቤተ ክርስቲያን ያሳደጉ የተግባር ክርስቲያን ናቸው። ሀዘን እና ጭንቀታቸውን የሚገልጹት በእንባቸው ነው።

አቢሰሎም፡- እድሜው 30 (ሰላሳ) የሆነ ለቤተሰቡ የመጀመርያ ልጅ ነው። እንደታላቅነቱ ሁሉም የሚያከብሩት ከሁሉም ጋር ተከባብሮ የሚኖር ስለቤተሰቡ መልካም እና ቅን ነገርን ስለሚያስብ መጥፎ ነገርን ማገናዘብ ይሳነዋል። ሲናደድ በራስ ምታት እና በነስር ይመታል። ፈጥኖ ለውሳኔ የሚቸኩል ቢሆንም ተጸጻች እና ይቅርታ አዋቂ ነው። ለህይማኖቱ የሚቀና ላመነበት ነገር ወደፊት የሚል ለደሀ የሚያዝን የዋህነት የሚያጠቃው ነው።

ስምኦን፡- ለቤተሰቡ ካቢሰሎም አስከትሎ ሁለተኛ ልጅ ሲሆን እድሜውም የ 27 (ሀያ ሰባት) አመት ወጣት ነው። ከቤተሰቡ ጋር መልካም እና አስደሳች አቀራረብ አለው። ገር እና ለስላሳ የሆነው ባህሪው ከወንድሞቹ ይልቅ ሰከን ያለ አድርጎታል።

አምኖን፡- ለቤተሰቡ 3 ኛ ልጅ የሆነ የ 24 (ሀያ አራት) ዓመት ወጣት ነው። ክርስትናው የሚፈተን በሱ ምክንያት ቤተሰቡ በመታወኩ አእምሮው በፀፀት የሚታመስ።

ትእግር፡- እድሜዋ 20 (ሀያ) ነው። እንደወንድሞቿ ቤተሰቦቿን የምትወድ ጠንካራ ክርስቲያን ሴት ነች። እስከ ፍጻሜዋ በድንግልና መነሆርን የምትመርጥ አለምን የናቀች መንፈሳዊ። ለቤተሰቧ ደህንነት አስፈላጊውን መሰዋትነት የምትከፍል፣ ሀዘኗን በልቧ አምቃ መያዝን በመምረጥ ጭንቀቷ ለሷ ብቻ እንዲሆን የምትፈልግ ሴት ናት።

ራማ፡- ለቤተሰቡ የመጨረሻ ልጅ የ 12(አስራ ሁለት) አመት ታዳጊ ናት። ለታላላቆቿ ታዛዥ እና ተወዳጅ፣ በአለም እና በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጎበዝ የሆነች ታዳጊ። የእናቷን ስሜት ከሌሎቹ በበለጠ የምትረዳ፣ ሰውን መመርመር የምትችል፣ ከትንሽ ነገር በመነሳት በሰለ ልቦና ትልልቅ ጉዳዮችን የመገመት ተሰጦ ያላት ባስተሳሰብ የበሰለች ባለ ራእይ ህፃን ናት። ለችግሮች መፍትሄን እና እውነትን ፍለጋ መድከሟን ማንም ያልተረዷት።

ሌጊዮን፡- የ 32 (ሰላሳ ሁለት) አመት ወጣት ነው። እውነታን ሳያውቅ እራሱን በገንዘብ ሽጦ ለተንኮል የተሰናዳ ቢሆንም እውነታን ሲረዳ ግን የሚጸጸት ልብ ያለው ከገንዘብ ይልቅ እራሱን ለፈጣሪ አሳልፎ እስከመስጠት ቁርጠኛ የሆነ ሰው ነው።

ወ/ሮ ትህትና፡- እድሜያቸው 51 (ሀምሳ አንድ) የተጠጋ ወ/ሮ ናቸው። በልጃቸው ናፍቆት የተጎዱ፣ በወጣትነት እድሜያቸው በሰሩት ስህተት እድሜ ዘመናቸው ሁሉ በጸጸት የሚኖሩ ወ/ሮ።

ለራሴ

አንድ ቀን ተመልሼ ከወጣሁበት አባቴ ቤት እንደምገባ አምን ነበር። ያደኩበትን ቤተ ክርስቲያን ጥሎ መውጣት ቀላል አልነበረም ከባዱ ግን ተመልሶ መግባቱ ላይ ነው። ዓለም ሁል ጊዜ እራሷን አስበልጣ ሰላምታሳይ ከሷ በላይ አንድስ እንኳን ነገር እንደሌለ አምና ለማሳመን ጥረቷ ከብረት የጠነከረ፤ ከውሀ የለሰለሰ፣ ከንፋስ የፈጠነ ነው። የስጋዊ ምቾት መደለያዋ ነፍስን በብርቱ ይፈታተናል የሰው ልጅ ለአፍታ እንኳን ልባዊነት፣ ነባቢት እና ህያዊት ለሆነችው ነፍስ እድል ቢሰጥ ፈጣሪዋን እስበልጣ ከእርሱ ሌላ አንድስ እንኳን ምቹ ነገር እንደሌለ ምስክሯ ነው። አለም (አለም ስል በእሷ ውስጥ ያለን ከንቱ ስጋዊ ፍላጎትን ማለቴ ነው) አለም በሳጥናኤል የምትጋለብ በቡቱቶ ያሸበረቀች ሰጋር በቅሎ ናት። በሰረገላዋ ቅናት፣ ምቀንነት፣ ተንኮል፣ ዝሙት፣ ሌብነት፣ ውሸት፣ ትምክህት፣ ነፍስ ገዳይነት ከንቱ ምኞት ወዘተ... እና ብዙ ወዘተ ግሳንግሶችን ታቅፋለች። ይህ ሁሉ ኮተቷን መልካም መአዛ በተሞላ በተብለጨለጨ ጨርቅ ለተጋረደ ሰው ይከተላታል ደርሰውባት እውነተኛ ማንነቷን እንዳይታወቅ የተቀረቧትን ያህል ትርቃለች ሲርቋት ትቀርባለች።

ሲጀምር እግዚአብሔርን ጥሎ አለምን መከተል ከባህር ላይ እንደተቀመጠ ኩበት ነው። ወየው ለሱ! የተናቀ ድንጋይስ የመአዘን እራስ መሆን ቻለዋል በጥልቁ ውስት ቢጣል እንኳን አሳዎች ይንተራሱታል እንጂ በውሀ ፍጹም አይቀልጥም። ያልታደለው ከብት ግን በወጀብ ይገፋል፣ በውሀ ይነፍራል፤ በማአበልም ተበትኖ እንዳልነበር ይሆናል።

ለሰው ልጅ ፍም እና ፍትህ፣ እውነት እና ሀሰት፣ ብርሀን እና ጨለማ፣ ሞት እና ህይወት እንዳማራጭ ቀርቦለታል ያሸውን የመምረጥ ወደፍላጎቱ መንደደርደር የሱ ምርጫ ነው። አንዱን ማጣት እንጂ ሁለቱን መምረጥ ፍጹም አይቻልም። በቃ አይቻልም ታላቁ መፅሀፍም እንዲህ ይላል "ወይ ሞቃት አልያም በራድ ስላልሆንክ ልተፋህ ነው።" አንድ ሎሌ ለሁለት በጌቶች በግዛት እንደማይችለው ሁሉ ሕይወትም አንድ ምርጫ ናት። እንደ ይሁዳ ጽንፍ የሆነ ነገሮችን ከመረጥን ከሁለት አንድ ያጣ እንሆናለን ከክርስቶስም ከገንዘብም እንዳልሆነው ይሁዳ።

ቤተ ክርስቲያን እንደ አለም አይደለችም ከውጫዊ ውበት ይልቅ ወስጧን ታሳያለች መሰረቷ ደም፣ ግንቧ ንጹህ ውሀ፣ መንገዷም ጠባብ ነው። በዚህ መንገድ ላይ የክርሰቶስን መስቀል ተሸክመን እንድንጓዝ ነው ጥሪዋ። እኛ መስቀሉን እንሸክም እንጂ የሚያነበረታን ክርስቶስ ነው የሰው ልጅ የትኛው የጠገገ ወገቡ ነው የጌታን ቃል አልባ መከራ መሸከም የሚቻለው? ጌታ አይደለም ስለ እርሱ የምንቀበለውን

መከራ ይቅርና የገዛ ሀጥያታችን የጣለብንን የመከራ ቀንበር እንደ ገል ቀጥቅጦ እንደስም አቅልጦ ማጥፋት እንደሚቻለው ያላመነ ምንኛ ደንዳና ልበ ይሆን? እርሱም እንዲህ ይላል “እናንት ሸክማቹ የከበደ ኑ ወደኔ አሳርፋቹዋለው” ይለናል። የሰው ልጅ ስስታም ባህሪው ሸክሙን እንኳን ላለማካፈል ተንገብጋቢ ካላደረገው በስተቀር የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል ሸክማችንን ቆንጥረን ለራሳችን ሳናስቀር ክርስቶስ ላይ መጣል። የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው እርሱ ትከሻው ሰፊ ነውና። የቤተ ክርስቲያንም እንደ እርሷ ናት። ስንቀርባት እንደምትታቀፈን ሁሉ ስንርቃት አልቅሳ ትፈልጋለች ራሷም እንዲህ ነው።

እኔ ሳለው በምድር በህይወት ዘመኔ ባባቴ ቤት ባሳለፍኩበት ጥቂት ግዜት ለበርካታ አመታት የሚሆነኝን ስንቅ በልቤ አገልግል ሰንቄ ነው የወጣሁት። ካባቴ ማጀት ከወጣ ቃሉ ቢርበኝም ግን አልከሳሁም ቢሆንም ሞቴ የቀረበ መስሎ ታየኝ ምክንያቱ የሰው ልጅን እርሀብ እንጂ ክሳት ስለማይገለው። ያኔ ራሴን ከቤተ ክርስቲያን ማሳ ስነቅል ፍሬ ያልታየብኝ ግንድ ነበርኩ እንዲህ መሆን ደግሞ እንደዛች በለስ ያስረግማል ላለ መራብ ላለ መሞትና በእርግማን ላለ መቃጠል ስል እራሴን ወደተነቀልኩበት ማሳ መልሼ ተከልኩ ከባቴ ማጀትም ስመለስ እርሀቤ አለም ቀርቶ ነበር።

ባለሀብት እንዲያጸናኝ ዳግም ስደተኛ ሆኜ ባለም መድረክ ባይተዋር እንዳንሆን የእርሱ መልካም ፍቃድ፣ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት፣ የጻድቃን የሰማትነት ተራዳይነት፣ የመላእክት ልማና ከፈጣን አገልግሎት ጋር አይለየኝ። አላበቃሁም…

“ቀይ ሰይጣን”

ገቢር አንድ

ትእይንት አንድ

መብራት ሲበራ በመካከለኛ ደረጃ የሚገኝ የመኖርያ ቤት ይታያል ከመድረኩ በስተቀኝ የመውጫው በር ሲሆን በስተግራ ያለው በር ወደ ውስጥ ክፍሎች የሚያስገባ በር ነው። ወንበር፣ ጠረጴዛ እና ሌሎች የቤት እቃዎች ቦታቸውን ይዘው ተቀምጠዋል።

ራማ መንፈሳዊ መዝሙር ትዘምራለች ሌጊዮን በአግራሞት ይመለከታታል ስምኦን መጻፍ ቅዱስ ያነባል ከአፍታ በኋላ አምኖን ከመኝታ ክፍል ይወጣል ቆሞ የራማን ዝማሬ ይሰማል ራማ ዝማሬዋን ስትጨርስ ሌጊዮን ያጨበጭባል

ሌጊዮን .... /እያጨበጨበ/ በጣም ....! በጣም ....! ጎበዝ። ለዚህ ጉብዝናሽ.... ከኪሱ ቸኮሌት እያወጣ፤ ቸኮሌት ነው የምሸልምሽ

ራማ፡- ጾም እኮ ነው፤

ሌጊዮን፡- ዛሬ ቅዳሜ አይደለም?

ራማ፡- ወቅቱ እኮ የታላቁ የአብይ ጾም ወር ነው።

ሌጊዮን፡- ኦ.... ለካ ጾም ነው!

አምኖን፡- እኔ የምልሽ መቼ ነው ይህንን መዝሙር ያጠናሽው?

ራማ፡- ዛሬ።

ስምኦን፡- ዛሬ አጥንተሽ ነው በቃልሽ የያዝሽው?

ራማ፡- አዎ ለእማማ ልዘምርላት ስመጣ እንቅልፍ ይዟት ነበር አሁን ተነሳች እንዴ?

ስምኖን፡- እንደተኛች ነው። /ሰአቱን ይመለከትና/ ሰአቱ እንዴት ነው የሚሮጠው አሁን እኮ ትእማር እና አቢሰሎም መምጫቸው ነው።

ሰምኦን፡- /ሰአቱን ይመለከትና/ ኦ.... አገልጋዮቹ የነዳያንን ጨርሰው ይሆን?

አምኖን፡- ሁሉም ነገር ተጠናቆ ምግቡም መጠጡም ቀርቧል። ከደቂቃዎች በኋላ ሰባኪያንና መዘምራን ይመጣሉ።

ሌጊዮን፡- እኔኮ የእናንተ ቤተሰብ ፍቅር ግርም ይለኛል! አምኖን፡ እንዴት?

ሌጊዮን፡- በቃ አንዳቹ ሌላኛውን በድብቅ ለማስደሰት የምታደሩጉት ጥረት አስገራሚ ነው።

ስምኦን፡- ስለኛ ስታወራ እራስህን ገለል እያደረክ ነው?

ሌጊዮን፡- የእኔ ድርሻ ጓደኝነት ነው። እናንተ አምስታቹ ከአንድ አባት ከአንድ መሀጸን አደራቹ የእናታችሁን ጡት በየተራ በመጥባት የደጋቹ ባህሪያቹ አመለካከታቹ እና እራእያቹ አንድ ነው።

ራማ፡- ልዩነታችንስ?

ሌጊዮን፡- በስም በጾታ እና በእድሜ።

ራማ፡- አንተም እኮ በእያንዳንዳችን ልብ ውስት አለህ ሁላችንም ደግሞ በአንተ ልብ ውስጥ እንገኛለን።

ሌጊዮን፡- ይሄንን በትክክል አምናለሁ ግን እኔ በእናንተ ደም ውስጥ የለሁም የእናንተ አምስታቹ ደም እኮ ከአንድ ልብ የተቀዳ ነው

አምኖን፡- መወለድ ቋንቋ ነው ሲባል አልሰማህም?

ሌጊዮን፡ ይሄ አባባል ለእናንተ አይሰራም። እዚህ ቤተ እኮ ሰላም፣ ፍቅር፣ እምነት እና እውነት በየማእዘኑ በየዙፋናቸው ላይ ተቀምጠዋል። እግዚአብሔር እናታችሁን ጨርሶ ይፈውሳቸውና እያንዳንዳችሁን በመልካም ስነ ምግባር አንጸው ነው ያሳደጉቹ ዛሬ ሀሳባቸው ሰምሮ ሁላችሁም ታማኝ አገልጋይ መሆናችሁን ሲገነዘቡ ለአንዲት ደቂቃ ብቻ እንደበታቸው ቢከፈት ለፈጣሪ ያላቸውን ምስጋና መዝምታ ነበር የሚገጹት።

ስምኦን፡- አራስህን እንደገለልተኛ አድርገህ ማውራትህን ብትሰማ ደግሞ በተፈቀደላት አንዲት ደቂቃ ተወቅስህ ነበር። የሉቃስ ወንጌል ፰÷፲፱ ምን እንደሚል ታውቃለህ?

ሌጊዮን፡- አላውቀውም

ስምኦን፡- /መጽሀፍ ቅዱስ ለራማ እየሰጣት/ አንብቢለት

ራማ፡- /መጽሀፍ ቅዱሱን ተቀብላ ታነባለች/ "እናት እና ወንድሞቹ ወደ እርሱ መጡ፣ ነገር ግን ህዝቡ ብዙ ነበርና ሲያገኙት አልቻሉም።

"እናትና ወንድሞችህ ከውጭ ቆመዋል፣ ሊያዩህም ይሻሉ "አሉት። እርሱም መልሶ÷እናትና ወንድሞቼ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚያደርጉ እነዚህ ናቸው" አላቸው። ስለቃሉ ያምላካችን ስም የተመሰገነ ይሁን። /አምኖን እና ስምኦን በአንድ ድምጽ/ አሜን።

ሌጊዮን፡- የዚህ ያህልማ አታምሩ እኔ እኮ ለቀልድ ነው ያወራሁት

ራማ፡- እኔ የምልህ ሌጊዮን ይሄ ስምህን አስቀየረው ስልህ እንቢ አልክ አይደል

ሌጊዮን፡- ወይ እህትሽም ውጋት ነው የሆነችብኝ እኔ እኮ ስምን የምጠቀመው ለመጠርያነት ነው

ስምኦን፡- ስብከትም ነው ደግሞ ሌጊዮን ማለት....

ሌጊዮን፡- ጭፍራ ማለት ነው እኔ ግን ጭፍራን እየሰበኩ አይደለም በሞላ ስም የሌሎችን የተደጋገመ መጠሪያ ከምጠቀም ይሄ ይሻለኛ በማለት ነው የመረጥኩት ስንቶችአሉ አይደል እንዴ በቀልን ጥላቻን እና ቂምን የሚሰብኩ ስሞች ይልቀንስ ምንድን ነው ስለ እማማ ጤንነት እየታሰበ ያለው

ስምኦን፡- እንደተለመደው ከመንፈሳዊ አገልግሎት ሌላ የታሰበ ነገር የለም

ሌጊዮን፡- ይሄ ለውጥ ከሌለው ለምንድን ነው ከሀገር ውጭ ወተው እንዲታከሙ የማይደረገው የአባታቹ እርስት የሚያስገባው ረብጣ ገንዘብ አይደለም እሳቸውን ከሀገር ውጭ ልኮ የማሳከም የቅርና በየአስባቡ ምድረ ችጋራምን... ይቅርታ ነዳያንን በቁንጣን ታስጨንቁበት የለ

ስምኦን፡- አየህ እማማ ገና እጆቿ መንቀሳቀስ አቁመው ሲቀዘቅዙ ከጸበል ውጪ የትም መሄድ እንደማትፈልግ ነግራናለች።

ሌጊዮን፡- ለምን

ስምኦ፥ እግዚአብሔር ሊምረኝ ከፈለገ በጸበል ይፈውሰኛል ካልፈቀደ ግን ዶክተር ጋር መሄድ ትርፍ ልፋት ነው ትላለች

ሌጊዮን፡- ታዲ ምን እስከሚሆኑ ነው የሚጠበቅ የእጃቸው አለመንቀሳቀስ ሲያስደነግጠን ጭራሽ እንደበታቸው ተዘጋ ይሄ የአደጋ ወደ ሌሎች አካላቸው አለመዛመቱን ምን እርግጠኛ ቢያደርጋቹ ነው እጅ እና እግራችሁን አጣጥፋቹ የተቀመጣችሁት

አምኖን፡- እግዚአብሔር ሊሰራ ያሰበውን አናውቅም ስለዚህ ጉድለታችንን እርሱ እንዲሞላው መጠየቅ አይሻልም።

ሌጊዮንለ፡- እስከመቼ

አምኦን፡- ስራውን የሚሰራበት የራሱ የሆነ ወቅት አለው እርሱን በሰዎች ግዜ መጠየቅ አይቻልም

ሌጊዮንስ፡- መልካም

አምኖን፡- ስምኦን እንደዚህ ሆነህ ነው እንዴ ትእማርን የምትጠብቃት

ስምኦን፡- አረ ልብወስ እና ጫማ እለውጣለሁ

አምኖን፡- ጫማህ ተወልውሏል

ስምኦን፡- ምን ችግር አለው አንድ አፍታ እወለውለዋለሁ

አምኖን፡- እኔ እወለውልልሀለሁ አንተ ልብስህን ቀይር

ራሚ፡- እኔ አጸዳለታለሁ

አምኖን፡- /ግንባሯን እየሳመ/ አንቺ እማማን ቀስቅሻት እሺ

ራሚ፡- እሺ /ሁሉም ወደ ውስጥ ይገባሉ ሌጊዮን ብቻውን ይቀራል/

ሌጊዮን፡- /በረጅሙ ይተነፍስና/ የዚህን ቤት ልጆች በጓደኝነት ተዋውቄ የበቀል መረቤን ይዤ ከገባው እነሆ ሁለት ዓመት ሞላኝ ልክ የዛሬ ሁለት አመት ነበር እኔ ሆንበዬ እነ እርሱ ግን ድንገተኝና ገጠመኝ በሚመስላቸው አይነት የተዋወኳቸው የዚህን ያህል ግዜ የዚህን ቤተሰብ ፍቅርን በጥላቻ ሰላሙን በሁከት እውነትነቱን በውሸት ልቀይጥ ምሶሶውን ለንጥ ብሞክር አልቻልኩም በርካታ

ሴራዎቻ እሳት እንደላሰው ስም ከፊቴ እየቀለጡ ጠፉ ተስፋ መቁረጥ የሚባል ነገር ግን በህይወቴ አላውቅም ዛሬም መርዛማ መረቤን አጥላላሁ ዛሬም አመተኬላ የሞላበት ጥልቅ ጉድጓዴን እቆፍራለሁ

/ከውስጥ ራማ እናቷን ደግፋ ታመጣና ታስቀምጣቸዋለች/

ሌጊዮን፡- ራማ ከሞቀ እንቅልፍ ይሆን እንዴ ቀሰቀስሻቸው

ራማ፡- አይ ነቅታ ነበር መጣው ልብሴን ቀይሬ

ሌጊዮን፡- እኔ የምልሽ ለትእማር የምትሰጪት አበባስ

ራማ፡- መኝታ ክፍሌ ነው አምጥቼ ከነ አምኖን ጋር ልቀላቅለው

ሌጊዮን፡- ግድ የለም እዛው ይሁን /ራማ/ ወደ ውስጥ ትገባለች/ /ሌጊዮን ጠረጴዛ ላይ ከተቀመጡት አምስት አበቦች ሁለቱን ያነሳ እና አንዱን እናት እግር ላይ ያስቀምጥ እና/

ሌጊዮን፡- እሺ አንቺ ሞት የጠላሽ አሮጊት ፈጣሪ ያልገደለሽ እኔ የምሰራውን ሊያሳይሽ ፈልጎ ሳይሆን አይቀርም ልጆችሽ ትንሿራማን ጨምሮ አቢሰሎም፣ ሰምኦን፣ እምኖን እና ትእማር እኔን የሚያውቁኝ በጓደኝነት የመንፈስ ወንደማቸው እንደሆንኩ ነው ሀ… ! ደሜ ደማቸውን እኔም እንደነሱ የአንቺን መሀጸን ለ ዘጠኝ ወራት የተኮናተርኩ የአንድ አብራክ ፍልቃቂ የስጋ ወንድማቸው መሆኔን ቢያውቁ ምን የሚሉ ይመስልሻል ገና በጨቅላነት ግርማ ሞገሱ በሚያስፈራ በዚያ ግዙፍ ጫካ ከነነፍሴ እንደብጣሽ ስጋ ለዱር አውሬ እንደወረወርሺኝ ቢረዱ ስለገፈኝነትሽ ምን ይሉ ይሆን ፈጣሪስ ለዚህ ግብርሽ እንደበትሽነ ለጉሞ እጅሽን ጠመዘዘው ገና እግርሽን ይቆልፈዋል። /ከኪሱ ቅባት ያወጣ እና ጠረጴዛ ላይ ከተቀመጡት አበቦች አንዱን ይቀባውና በልቃጧን መልሶ ኪሱ ይከተዋል/ ትእማር ስትመጣ ሁላችንም አበባ እንሰጣታለን ከ ሶስቱ ልጆችሽ አንዱ ይህን መስተፋቅር የተቀባበትን አንስቶ የሰጣት በእህቱ ፍቅር ጨርቁን ጥሎ ይከንፋል ያን ጊዜ የቤተሰብ ሊበታትን ዋልታው ሊፈነቃቀል መሰረት ተጣለ ማለት ነው። /እናት እንባዋ የወርዳል/ አልቅሺ ገና በጭካኔ የደፈረሰ መርዛማ ደም ታለቅሻለሽ ነውሬካአንቺ የባሰ እንዳልሆን ሰይጣንም ክርስቶስም ምስክር ይሆኑኛል ግን ለምን እንደዚህ እንደማደርግ ይገባሻል አይደል በቆሻሻ መሀጸን ውስት ስለተበከልኩ እርህራሄ የሚባል ነገር አላውቅም የተቀሩት ለጆችሽ የዋህ መሆን ለኔ አያስደንቀኝም እነሱን ለማጽዳት እኔን አቆሸሽ መጣል ነበረብሽና አደረግሽው ግዜ ሲገለበጥ እንደዚህ ነው አሁን አይደለም አንችን መላ ቤተሰብሽን የማደፈርስበት ወቅት ላይ ደርሻለሁ /ከውስጥ ስምኦን፣ አምኖን እና ራማ ነጭበነጭ ለብሰው ከውስጥ ይወጣሉ ራማ በእጇ አበባ ይዛለች/

ሌጊዮን፡- በጣም ታምራላቹ /አምኖን ወደ እናቱ እየተጠጋ/

አምኖን፡- ምነው እማ /እንባቸውን እየዳበሰ/ ሌጊዮን ምን ሆና ነው

ሌጊዮን፡- ትኩር ብዬ ስመለከታቸው አሳዳጊ እናቴን መሰሉኝ ስለ እሷ ሳወራቸው አልቅሰው አስለቀሱኝ ስሜቴን መቆጣጠር አልቻልኩም /እንደ ማልቀስ ያደርገዋል/

ስምኦን፡- በቃ አታልቅሱ ዛሬ የደስታችን እለት ነው /አቢሰሎም ከውጭ ይገባል/

አቢሰሎም፡- ዋው ..... በጣ ታምረራላቹ

አምኖን፡- ትእግርስ

አቢሰሎም፡- አውቄ ነው ያዘገየኋት

ሌጊዮን፡- /ወደተቀመጡት አበቦች እየጠቆመ/ አበቦቻችንን የዘን እንጠብቃታ /እናት በጭንቀት ጭንቅላታቸውን ይነቀነቃሉ ሁሉም ግራ ይጋባሉ/

ስምኦን፡- ምንድን ነው እማ /እራሳቸውን ደግመው ይወዘውዛሉ/

አቢሰሎም፡- ምንድን ነው እሚታል እንዴ

ሌጊዮን፡- ምን እንደሆኑ እንጃ ቅድምም ከእኔ ጋር ሲያወሩ እንደዚህ ይለኝ ነበር ምናልባት እራሳቸውን አሚቸው ይሆን

አምኖን፡- እማ አሞሻል /እናት ለአሉታ ጭንቅላታቸውን ይነቀንቁ እና ወደተቀመጠላቸ አበቦች በጭንቅላታቸው ጠቁማሉ/

ሌጊዮን፡- ትእማር ሳትመጣ ቶሎ አበቦቻችሁን አንሱ ማለታቸው ሳይሆን አይቀርም /አቢሰሎም ስምኦን እና አምኖን የተቀመጡትን አበቦች ያነሳሉ ትእማር ከውጭ ትገባለች/ ሁሉም በአንድ ድምፅ/ትእማር ትደሰታለች ሁሉንም በማመስገን አቅፋ ትስማለች የያዙት አበባ የሰጧታል ወደ እናቷ ስትቀርብ እያለቀሱ ነው።

ተእማር፡- ምነው የኔናት

ሌጊዮን፡- ደስታ ነው ያስለቀሳቸው ይልቁንስ ልደትዋን ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀውን ይነገራታ

ስምኦን፡- መልካም ውዷ እህታችን ትእማር ሆይ ልደትሽን ምክንያት በማድረግ በትልቁ አዳራሽ ውስጥ ታላቅ ድግስ ተደግሷል

አቤሰሎም፡- እንግዶችሽም ከየአቤያተ ክርስቲያናቱ ደጃፍ የተሰበሰቡ ነዲያን ናቸው

አምኖን፡- በተጨማሪም ከመናፍቃን እና ከአህዛብ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶችሽም ይታደማሉ

ራማ፡- ዘማርያን በድምጻቸው እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ሰባኪያንም ሀዲስ ከበሉያናት እያጣቀሱ ያስተምራሉ

አቢሰሎም፡- እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መናፍቃኑን እና አህዛቡን ወደ አንዲቷ ሀይማኖት እቅፍእንደምናመጣቸው ተስፋ እናደርጋለን።

ትእማር፡- እንደ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን የድንግል ምልጃዋ ስለማይለየን ጌታም ይረዳናል ደግሞ እግዚአብሔር በአንድም በሌላ መንገድ ይናገራል መንፈሱ በእናንተ ላይ አድሮ በልደቴ ምክንያት ወንጌሉ ለማያምኑ እንዲደርስ ሆነ በእውነት ለእናቴ ለወንድሞቼ እና ለትንሿ እህቴ ያለኝ አክብሮት እና ፍቅር ከቃል በላይ ነው

ራማ፡- እኛ ሁላችንም እንወድሻለን ምን ግዜም በአንቺ ደስተኞች ነን

ስምኦን፡- በትክክል መርሀግብሩ ለመጀመር የምንጠበቀው እኛ ለምን አንደሄድም

ሌጊዮን፡- በጣም ጥሩ እናንተ አንድ ላይ ሂዱ እኔ እማማን ይዛቸው እመጣለሁ

ትእማር፡- ለምን አብረን አንሄድም

ሌጊዮን፡- እሳቸው ቀስብለው ስለሚሄዱ እንዳትዘገዩ ነው እኛ እስከ ምንመጣ ከመርሀግብር አስተባባሪዎቹ ጋር እንዳንድ መረጃ ተለወጡ እኛ ስንመጣ በጸሎት ይከፈታል

አቢሰሎም፡- መልካም በቃ እንሂድ /አቢሰሎም ስምኦን አምኖን እና ትእማር ይወጣሉ ራማ ለመውጣት በር ጋር ደርሳ ትመለሳለች/

ሌጊዮን፡- ጥለውሽ ሄዱ እኮ አትሄጂም

ራማ፡- ደስ አላለኝም

ሌጊዮን፡- ምኑ

ራማ፡- እኔንጃ እንዳቻ ነገር መንፈሴን ከበደው

ሌጊዮን፡ ኦ..... ትንሿ ራማ መንፈስሽ ያልተፈጠረ ነገር ያነባል ማለት ነው

ራማ፡- ምናልባት የተፈጠረ ነገር ቢኖርስ

ሌጊዮን፡ ምን ሊሆን ይችላል

ራማ፡- እኮ የተፈጠረውን አለማወቄ አይደል መንፈሴን የከበደው እማማ ከወትሮ የተለየ ጸባይ ለምን አሳየች

ሌጊዮን፡- ይሄ የሁላችንም ጥያቄ ነው በአንዳች ተአምር አነደበታቸው ተከፍቶ ካልተናገሩ በስተቀር በምን ልናውቅ እንችላለን

ራማ፡- /እናት እግር ስር ተንበርክካ/ እማ/እናት ሌጊዮንን ይመለከቱትና በአዎንታ ጭንቅላታቸውን ይነቀንቃሉ/ ምንድን ነው ችግርሽ አሞሻል በአሉታ ጭንቅላታቸውን ይነቀንቁና ሌጊዮንን ይመለከቱታል/ ምንድን ነው ሌጊዮን

ሌጊዮን፡- ምኑ?

ራማ፡- አንዳች ነገር ስጠይቃት አንተን ትመለከታለች ይመስለኛል እንድታስረዳላት የምትፈልገው ነገር አለ

ሌጊዮን፡ እስቲ የሚጠጡት ውሀ አምጪላቸው /ራማ ወደውስጥ ልትገባ ስትል እናት በአሉታ ጭንቅላታቸውን ይነቀንቃሉ/

ራማ፡- /እየተጠጋቻቸው/ ከአጠገብሽ እንድርቅ አትፈልጊም /በአሉታ ጭንቅለታቸውን ይነቀንቁና ሌጊዮንን ይመለከቱታ/

ሊጊዮን፡- በጣም ጥሩ በቃ አንቺ ይዘሻቸው ነይ እማማ አይዞት እሺ ችግር ካለ መፍትሄ አለ ራማ እስቲ እንዴ ነይ እማማ አይዞት እሺ ችግር ካለ መፍትሄ አለ /ለመውጣት ወደ በሩ ይጠጋና/ራማ እስኪ አንዴ ነይ /ትጠጋዋለች ከእናት ፊንጠር ብለው በጎንታ ያወራሉ/

ሌጊዮን፡- እኔ አንዳች ነገር ገመትኩ

ራማ፡- ምን

ሌጊዮን፡- ለአንቺ ከመንገሬ በፊት እሳቸውን ለጠይቃቸው ምናለባት ግምቴ እውነት ከሆነ እንመካከርበታለን ካልሆነ ደግሞ ይቀራል

ራማ፡- መልካም

ሌጊዮን፡- ለትንሽ ደቂቃ ብቻችንን ብትተይን

ራማ፡- እሺ /ራማ ትወጣለች ሊጊዮን ወደእናት እየተጠጋት/

ሌጊዮን፡- እሺ አንቺ አሮጊት በአንቺቤት ማውራት መፈለግሽ ነው ጭንቅላትሽ የምትንጪው? ስሚኝ አንዳች የተለየ እንቅስቃሴ ባይብሽ ከፍተኛ ችግር ነው የሚፈጠረው። ከልጆችሽ ሁሉ የተለየ በሀሪ ያላት ይቺ ፈልፈላ ናት። እሷ ሚስጢር ብታውጣጣ እና አንቺ በሚገባት ቋንቋ አንዳች ነገር ብትያት አንገቷን ቀርጬ ቅሏን አስታቅፌሽ የልጅነት ደሟን እፊትሽ ነው የማርከፈክፈው። እዚህ ቤት ለሁለት አላማ እንደመጣው ይገባሻል፣ አንደኛው አንቺን ለመበቀል፣ ሁለተኛው የዚህ ቤት የተትረፈረፈ ሀብት ያሳሳል።ትላልቅ የእርሻ ማሳዎች፣ በእህል ከአፍ እስከ ገደፋቸው የተሞሉ ግዙፍ መጋዘኖች፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ከብቶች፣ ለቁጥር የሚታክቱ ዶሮዎች ከነ እንቁላሎቻቸው፣ በየወቅቱ እየተቆረጠ በበርሜል እየተሞላ የሚገባው ማር... እነዚህና መሰል ሀብቶች ያሳሳሉ። ገንዘቡ እየተዘረዘረ እህል እየተበጠረ ለምድረ ችጋራም ልቃሚ ደሀ በነፃ ሲሰጥ ውስጤ በቅናት እየቀሰለ ይኮማተራል። ይህንን ሁሉ ንዋይ ለማገኘት የዚህን ቤት ፍቅር መበታተን የተቃቀፋ ልጆችሽን መበተን የግድ ይለኛል፣ ሁሉንም በአይንሽ ትመለከቻለሽ በእርግጠኝነት የምነግርሽ ህልሜ ተፍቶ እውን እንደሚሆን እንጂ ከቶም የተሰፋ መና እንደማይሆን ነው የፈጠረሽ ካልቀደመኝ በስተቀር ይህንን ሳታይ አልገልሽም። ትቷቸው ይወጣል/

ትእይንት ሁለት

መብራት ሲበራ ስምኦን በመስኮቱ አሻግሮ ወደውጭ ይመለከተል ከአፍታ በኋላ አቢሰሎም ከውስጥ ይወጣል ስምኦንን የመለከተውና

አቢሰሎም፡- በመስኮቱ እሽቅበህ ሰማዩ ደረት ላይ ምን እየተመለከትክ ነው /ዝም ይለዋል/ ስምኦን!

ስምኦን፡- /ዞሮ አቢሰሎምን እየተመለከተ/ ሞተህል እንዴ

አቢሰሎም፡- ምንድን ነው ባክህ ተመስጦ ውስጥ የከተተህ

ስምኦን፡- ቀስተ ደመና

አቢሰሎም፡- ለመጀመሪያህ ነው እንዴ ቀስተደመና ስትመለከት

ስምኦን፡- አረ የዛሬውስ የተለየ ነው ናበናትህ ተመልከተው /አቢሰሎም ወደመስኮቱ ተጠግቶ የመለከትና/

አቢሰሎም፡- ዋው .... እንዴት ያምራል በፈጣሪ አረንጓዴ ቢጫ ቀዩ ከመድመቁ በፀሀዩ ዙሪያ መክበቡ

ስምኦን፡- ምን እሱ ብቻ አካባቢውን ደመና ሸፍኖት የጸሀዩ ብርሀን የፈካው ጋራ ላይ ያለችው ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን ላይ ነው

አቢሰሎም፡- ልዩ ነው /ወንበር ላይ ሄዶ ይቀመጣል/

ስምኦን፡- ወትሮም የቃል ኪዳኑ ምልክት በቀለማት ተውቦ በደመና ተሰቅሎ ስመለከተው እደነግጥ ነበር ዛሬ ደግሞ መንፈሴ ይበልጥ ተረበሸ

አቤሴሎም፡- እንዴት

ስምኦን፡- ምልክቱ ሲታየኝ ህሊዬ በምናብ አስረኛው ትውልድ የኖህ ዘመንን ያሳየኛል ምድር በሀጥያት የተጨማለቀችበት የእግዚአብሔር ክብር ተረስቶ ጣኦታት በየፈርጁ የቆሙበት ሰዎች በሰዎች ደም የሚታጠቡበት፤ ሁከት ጫጫታ፤ ጭፈራ፤ ዝሙት የበረታበት፤ ውሸት ቅጠፈት፤ ክህደት፤ ሌብነት፤ ያለከልካዩ የነገሱበት፤ እግዚአብሔር ሰውን በመፍጠሩ ተጸጽቶ የሀጥያት ጥላሸት ያጠለበት የተጨማለቀ ትውልድን ከአለም ላይ ለማጽዳት እግዚአበሀሔር አርባ መአልት ከአርባ ሌሊት ነው ምድሪቱን በንፍር ውሀ የቀቀላት።ከዚያ ቦኋላ ህዝቡን በፈላ ውሀ እንደማያጠፋ ለኖህ የቃልኪዳን ምክትን የሰጠው ቀስተደመናን ነው ይህ ምልክት ሲያሳየን ምን ሊለን እንደፈለገ ግልጽ ነው ሀጥያታችን ከኖህ ዘመን እንደባሰ እንዳያጠፋን ቃሉን የማያጥፍ አምላክ መሆኑን ሲነግረን ወደልባችን እንድንመለስ ሲያሰጠነቅቀን ቀስተደመናን ከሰማይ እንብርት ወደ ምድር ውሽመጥ ቀንፎ ያሳየናል።

አቢሴሎም፡- በትክክል ከኖህ ዘመን ህዝብ በብዙ እጥፍ በዝተናል ቁጥራችን ብቻ ሳይሆን የሀጥያቱም አይነት የዛሬ ያህል ተባዝቷ። የተለያዩ ምንፍቀና እና በአድ አምልኮ እለት እለት ከሰይጣን ጉያ ይመነጫሉ። ለጣኦትም ለሰው ይሰግዳል። መተተኞች፣ የሚርት ባለቤት፣ የድግምት፣ አፍቃሪ፣ የለሊት ኮኮብ ቆጣሪ፣ የማለዳ ተበታቢዮች፣ አዚም ጠሪ፣ አመድ ነስናሽ፣ ቅጠል በጣሽ፣ ለውቃቤ አዳሪ፣ ቃልቻነን ባዮች፣ ስንቱ ነው በየጠንቋይ ቤት ግንባሩን ከመሬት የሚያላጋ? ዛሬም በሰው እንባ መታጠብ በደም መለቃለቅ አለ። ወገን በወገኑ ላይ መንግስትም በመንግስት ላይ ሲነሳ እየተመለከትን አይደል? ዛሬም በእራስት እና በነገድ እርስ በእርስ የሚከፋፍል የሚከፋፈልም አለ።ሀልዎተ እርሱነቱን ለሚጠራጠሩ ደንዳና ልባሞች ተፈጥሮ እንኳን እንደሚታዘዝለት ሲያሳይ በአርመሞ ገቢር ውሃ በነቢብ ከተፈጠረው ደረቅ መሬት ቀንጽል አካል ላይ ወቶ ሲያጥባት ያሳየናል፣ የጸሀይንሀሩሮችንም እያከረረ ያስተምረናል።

ስምኦን፡- የሚገርመው እንደዚህም ሆኖ አይደለም የጌታን የራሱን ጨኸት እንኳን ማዳመጥ የተሳነው ትውልድ አለ። በእግዚአብሔር ተመርጦ የሙሴን እግር የተካው ኢያሱ እንኳን ለነገዶቹ እርስት ነው ያከፋፈለው። ዛሬ የማንን እግር እንደተኩ፣ ከየት እንደመጡ የማናውቃቸው ግን ልባችንን ለመከፋፈል ሲጣደፉ እናያለን። እኛን መስለው ከውስጥ የመነጨ ወዛችንን መሳይ ቅባት ቆዳቸውን አርሰው ሊበታትኑን በምንፍቅና እና በሞት መረብ ሊያጠምዱን በለምድ ክፈፍ ውስጥ የተሸሸጉ ተኩላዎች እልፍ ናቸው። ግን የምንገፍ እንጂ የማንወድቅ፣ ብንዛቅ እንኳን የማናልቅ፣ መሰረታትን በክርስቶስ ደም ላይ እንደሆነ አልገባቸውም። በቅዱስ መጽሀፍ እንዳናስተምራቸው ለማያምኑ ቢከፈት እንኳን የተከደነ ነው። ሲጀምር እኛ ነገዳችን መቶኛ፣ ህብረታችን ከመላእክት፣ ሀገራችን በሰማይ ነው። ንጉሳችን በመንበረ ጸባኦት በዘባነ ኪሩብ የሚቀመጠው የአንድነት የሶስትነት ሚስጥሩ ሳይገባቸው እንደፍጡር የአማላጅነትን መአረግ የከናነቡት እርሱ ነው የሁሉ ፈራጅ እና ጌታ። ለዚህም አይደል በሶስቱ ታላላቅ ከተሞች በኢዮር፣ ራማ እና ኤረር የሚገኙ እልፍ አእላፍ መላእክት ስለክብሩ ቅዱስ ቅዱስቅዱስ እያሉ በፍርሀት እያመሰገኑ የሚሰግዱለት።

አቤሰሎም፡- ይህንን የሚጠራጠር ካለ ከአንዲቷ ቅድስት ሀይማኖት ከተዋህዶም እቅፍ ውጭ ነው።

ስምኦን፡- ቀስተደመናውን ስመለከት የእግዚአብሔር ክብር የተዘነጋ፣የሞት ቀስታችን ከሞት ካስማ ላይ እንደተቋጠረነው የሚታየኝ። /ራማ ከውጭ ነጠላዋን አጣፍታ ትገባለች/

ስምኦን፡- ኦ.... ታናሿ ራማ በጠዋት የት ጠፋሽ

ራማ፡- ሰንበት መሆኑን እረሳከው

ስምኦን፡- ታድያ እኮ ቅዳሴ ካለቀ ቆይቷል እትው በሰላም ከተባለ በኋላ የምታስቀድሺበት ቦታ ስመጣ የለሽም በቅጽሩም ላገኝሽ አልቻልኩም።

ራማ ፡- የሰበሰብናቸው ነዳየን ጋር ሂጃጄ ነው

አቢሰሎም፡- ቁርስ ሳትበይ በሰንበት ጾም እንደማይዋል ታውቂያለሽ

ራማ፡- እዛው ከአባባ አሻገሬ ጋር በልቻለሁ።

አቢሰሎም፡- ማናቸው አባባ አሻገሬ?

ራማ፡- እኛ እረጅም ነጭ ጢም ያላቸው ሰውዬ

ስምኦን፡- አወኳቸወስ

ራማ፡- ፍልፈላ ደብረ ገነት ኪዳነ ምህረት እና ጻድቁ አቡነ ተክለ ሀይማኖት ተብሎ ስለሚጠራው በ 1890 ዓ/ም በእጨጌ ቴዮፍሎስ በደቡብ ወሎ ሀገር ስብከት በአንባለል ወረዳ ስለምትገኝ እጨጌው የህግ ገዳም አድርገው ስለመሰረቷት ጥንታዊ ገዳም ሲነግሩኝ እንዴት ደስ አለኝ መሰላቹ።

ስምኦን፡- እስኪ ከሰማሽው አካፍይን

ራማ፡- እጨጌው እንጸው ታቦቱን ከስገቡ በኋላ 6 ደብተራ 9 ዲያቆናት 8 ቀሳውስት 1 አቃቤ እና 1 አበምኔት በቦታው መድበው ስትገለገል ከቆየች በኋላ ከእርሳቸው ቀጥለው የተሾሙት እጨጌ ገ/ስላሴ ማህሌቱን ጨምረው በማሰራት እንድትስፋፋ አድርገዋል አስገራሚው ነገር ግን እንደሆነ ታውቃላቹ?

አቤሰሎም፡- አናውቅም እስቲ ንገሪን

ራማ፡- በገዳሙ በርካታ ስውራን ቅዱሳኖች ይገኙበታል ለሊት ለሊት በታዘዘ ነብር የሚጠበቅ ሲሆን ማለዳ ካህናቱ ለአገልግሎ ሲመጡ ነብሩ ታማኝነቱን፣ ለማረጋገጥ ከታያቸው በኋላ ወደ ዱር ይገባል።

አቢሰሎም፡- የዱር እንስሳቶች አለበት ማለት ነው

ራማ፡- ታድያስ ነብር፣ ጉሬዛ፣ ጦጣ፣ ጭላዳ፣ ዝንጀሮ፣ ጥቆሬ ዱኩላ፣ ሰስ፣ ሚዳቆ ሽኮኮ እንዲሁም አእዋፍ በብዛት እና በአይነት ይገኙበታል።

ስምኦን፡- ቦታው ሄደሽ ነበር እንዴ

ራማ፡- የሰማሁትን ነው የምነግራቹ!

ስምኦን፡- ስቀልድሽ ነው። እኔ የምልሽ እነዛ ስወራን ቅዱሳኖች የሚገለጡበት ወቅት አለ?

ራሚ፡- ካህናቱ ለአገልግሎት በማይገቡበት ወቅት ቤተክርስቲያናቱ በስውራን ቅዱሳኖች ስትገለገል ታድራለች ይሄ ስለሚታመን ካህናቱም ሆነ ዲያቆናቱ ለአገግሎት ሲመጡ፣ አልያም ደውል እንኳን ለመደወል ሲገቡ የማይረብሽ የኮቴያቸውንም ድምጽ ሳያሰሙ ይገባሉ። ይህን ችል ብሎ የገባ አንድ ዲያቆን በእርሱ ተራ ወቅት ምን እሆናለው ብሎ በድፍረት ድምጹን እያሰማ በመግባት ደውሉን አጮኸው።

አቢሰሎም፡- እርግጠኛ ነኝ እዛው ደውሉ ስር በድን ሆኖ ነው የቀረው።

ራሚ፡- እግዚአብሔር እርሱን በመቅጣት ሌሎቹን ማስተማር ስለሚፈልግ ወዲው አልገደለውም። ደውሉን ባጮኸበት አፍታ በትእቢቱ እርኩስ መንፈስ አደረበት። ክብሩንም ማእረጉንም ተነፍጎ ሀይማኖቱን ክዶ እራሱን ፈራጅ በሚያደርግ በጠላት ወንበር ላይ ተቀመጠ። በኋላም ታሞና ተሰቃይቶ እንደሞተ አበባ አሻግሬ ነገሩኝ። /አምኖን ከመኝታ ክፍል እያዛጋ እና እየተንጠራራ ይወጣል/

ራሚ፡- እኔ አላምንም እስካሁን ተኝቼ ነበር እንዳትለኝ?

አምኖን፡- ስንት ሰዓት ሆነ?

ራሚ፡- እኩለ ቀን መሆኑን ለማብሰር ጸሀይ በእናት ትክክል ሆና የለም።

አምኖን፡- ከመቼው?

አቢሰሎም፡- /በቀልድ/ አንተ ተኝተህ እኛ ጸሀይዋን ገፍናት

ስምኦን፤ /በቀልድ/ ለካ ጸሀይዋን ገፍተናታል አይገርምም እረስቼዋለው ምንድነው እጄን የሚያቃጥለኝ ስለው ነበር /ሁሉም ይስቃላ/

አቢሴሎም፡- እንቅልፋሙ ወንድማችን በደህናህ ነው ግን ይህን ያህል ሰዓት የተኛከው?

አምኖን፡- ለሊት እንቅልፍ ሳይወስደኝ እንድቹ ስገላበጥ ነው ያደርኩት።

ስምኦን፡- ምነው የሚያስጨንቅህ ነገር አለ?

አምኖን፡- አረ የለም። ትእማርስ

ስምኦን፡- ገበያ ሄዳለች።

አምኖን፡- ብቻዋን!

ስምኦን፡- ማለት

አምኖን፡- ዛሬ የገበያ እለት ነው። ግርግር በሚበዛበት በዚያ ገበያ እንዴት ብቻዋን ትሄዳለች?

አቢሰሎም፡- አምኖን ምን ሆነህል?እንደ ሁሉ አገልጋዮች እያሉ ከዚህ ቀደምስ ብቻዋን ሄዳ ታውቃለች እንዴ?

ራማ፡- /ወደ አቢሰሎም ተጠግታ/ ሆ....ሆ ማታ እሰጥሻለሁ ብለከኝ የነበረውስ

አቢሰሎም፡- መኝታ ክፍልሽ አስቀምጬልሻለው/ራማ እየሮጠች ወደውስጥ ትገባለች/

ስምኦን፡- ይልቁንስ ማታ ስለንብረቶቻችን ስናወራ ተኝተህ ነበረ።

አምኖን፡- በግዜ ነው ትራሴ የናፈቀኝ፣ ፍሬ ነገሩ ምን ነበር?

ስምኦን፡- ለቀጣዩ አንድ አመት ንብረቶቻችንን በሙሉ አንተ እንድታስተዳድር መርጠንሀል።

አምኖን፡- ለዚህ ሀላፊነት እኔን ባትመርጡኝ መልካም ነበር

አቢሰሎም፡- ለምን

አምኖን፡- ሀላፊነቴን በአግባቡ መወጣት የምችልበት ወቅት ላይ አይደለሁም።

አቢሰሎም፡- የዛሬ አራት አመት እዚህ ሀላፊነት ላይ ስናስቀምጥህ በአግባቡ ነበር የተወጣከው

አምኖን፡- አው ... አሁን ግን

አቢሰሎም፡- አሁን ደግሞ ከአራት አመት በኋላ እዚህ ሀላፊነት ላይ ደግመን ስናስተምጥህ በእድሜም በእውቀትም የበለጠ በስለህል። ደግሞ ይህን ሀላፊነት እየተፈራረቅን እንደምንሰራው አትርሳ አሁን ግዜው የአንተ ነው። /ከውጭ ሌጊዮን ይገባል/

ሌጊዮን፡- እንደምን አረፈዳቹ

ስምኦን፡- እግዚአብሔር የተመሰገነ ይን እንደምን አረፈድክ

ሌጊዮን፡- ባልጎልም ባልሞላ አለሁ ይቺን ታህል!

አቢሰሎም፡- ምነው ስለህልወናህ ገደብ አጣህለት። የኖርከውን እድሜ ያህል ልብህ አልጠገበም?

ሌጊዮን፡- ልባችን መች ይጠግባል። በህይወታችን ያሉ ጉድለቶች በሙሉ መቀመጫቸው በልባችን ላይ ነው የሚገርመው ልባችን እነዚህ ሁሉ ጉድለቶች አያውቃቸውም

አቤሰሎም፡- ማለት

ሌጊዮን፡- ገልጽ እኮ ነው አንድን ነገር ተወጣነው ስንል ሌላው ይተካል፣ይሄንን ዘጋነው ስንል ማዶ ይከፈታል

ስምኦን፡- በስጋ ፍቃድ ሁሉንም ማለፍ አይቻለም የልባችንን ድክመ መንፈስ እንዲረዳው መጸለይ አያስፈልግም ትላለህ

ሌጊዮን፡- ጉድለቶቻችን እንዲሞሉ መቅደሱ ስር ተንበርክከን እጃቻችንን አሸቅበን ትግራችንን በሙለ ዘርዝረን ጸሎታችንን ጨርሰን ከመቅደሱ ስንወጣ ከዘረዘርናቸው በላይ ያልተነገሩ ችግሮች እልፍ ሆነው ከፊታችንን ይደቀናሉ። ለዚህ ነው በልባችን ላይ ያለትን ችግሮች እራሱ ልባችን አያውቀም ያልኩት።

ስምኦን፡- ለምን እንደሆነ ግን ይገባሀል

ሌጊዮን፡- አይገባኝም

ስምኦን፡- ልባችን በደካማ ስጋችን ውስጥ ስለተቀበረች ነው ለብርቱ መንፈስ መገዛት ፈተና የሆነባት። ለዚህም ነው የሀጥያት ቀንበር ተጭኖን፣ የችግሮች ሁሉ ስር የሆነው። ግን ይሄንን ሁሉ ማለፍ ይቻላል።

ሌጊዮን፡- ሁሉንም ማለፍ ቢቻልም ሁሉንም የማለፍ ጸጋ ግን ለሁሉም የተሰጠ አይደለም

አቢሰሎም፡- ስህተት ቀድመን ልባችንን ለሽንፈት ስለምናዘጋጅ ነው እንደዚህ የምንለው። እምነታችንን አጉድለን ሁሉንም በጥርጣሬ መነጽር ስለምንመለከት ከመንገዳችን የተሰነቀረ የሀጢያት ቋጥኝን ደካማ ስጋችን መዝለል እንደማይችል ይነግረናል። በዚህ ሰአት ወይ መንገዳችንን እንቀይራለን፣ አልያም ከቋጥኙ ስር እንደተቀመጥን ይመሻል። አይደለም ቋጥኝ አድማሳትን የሚጋርድ ቦርጫም ተራራ እንኳ ቢሆን እምነት ካለን ከስፍራ ስፍራ እራሱን እንዲያግዝ ማድረግ እንችላለን አይደለም እንዴ አምኖን?

አምኖን፡- /ከሀሳቡ ነቃ ብሎ/ እ.... እ... አዎ ማ... ማለቴ ሊሆን ይችላል

ስምኦን፡- እ....

አምኖን፡- ከዚህ የተለየ ሀሳብ የለኝም

ስምኦን፡- በሙሉ ልብህ አልሰማከንም አልያም ተኝተህ ነበር ማለት ነው

አምኖን፡- ሀሳቤ እየሸፈተ አስቸገረኝ

ስምኦን፡- ወዴት

አምኖን፡- /ፈገግ እያለ/ ወደ ልቤ ጫካ /ሁሉም ይስቃሉ/

ስምኦን፡- በሉ በሉ ከአባታችን ጋር ያለኝ የቀጠሮ ሰአት ደርሷል። አብሬያችሁ ብጫወት ደስ ይለኝ ነበር። ግን ያ ይበልጥብኛል።

አቢሰሎም፡- ትቆያለህ

ስምኦን፡- አላውቅም። አምኖን ስመለስ ስጦታ ይዤልህ እመጣለሁ የምሰጥህ ግን ቃል ስትገባልኝ ነው።

አምኖን፡- የምን ቃል

ስምኦን፡- አልተኛም ብለህ ቃል ግባልኝና /አምኖን ሊመታው የሶፋ ጨርቅ ያነሳል ስምኦን እየሳቀ የወጣል ሁሉም ይስቃሉ/

ሌጊዮን፡- አምኖን ከመቼ ወዲ ነው እንቅልፋም የሆነው

አቢሰሎም፡- አዲስ ያመጣው ጸባይ ነው፡፡ ቀድሞ ሁላችንም እማማ መኝታ ቤት ተሰባስበን ስናመሽ አልያም መጻህፍት ሲያነብ ለሊቱን አጋምሶ ነበር የሚተኛው፡፡ ማለዳ አእዋፍ መንጋቱን የሚያውቁት አምኖን መነሳቱን ካዩ በኋላ ነበር ዝማሬያቸውን የሚያሰሙት፡፡

ሌጊዮን፡- አሁን ከጸሀይ መውጫ እስከ መጥለቂያዋ ድረስ ከመኝታው አይነሳም እያልከኝው ነው

አቢሰሎም፡- በትክክል፡፡ አንተ እንኳን መጥተህ ተኝቶ ሳታገኘው የተመለስክበት ቀን ምን ያህል ነው

አምኖን፡- ሰሞኑን ዝም ብሎ ይደክመኛል፡፡ እንቅልፍ ዋና መቀመጫውን በኔ ላይ ሳያደርግ የቀረ አይመስለኝም፡፡ እርግጠኛ ነኝ ይሄ ታሪክ ከእንግዲህ አይደገምም /ያዛጋል/

አቢሰሎም፡- አሁንም እኮ ልትተኛብን እያዛጋህ ነው

አምኖን፡- ለሊት እንቅልፍ አልተኛሁም እያልኩህ

አቢሰሎም፡- ችግር ገጥሞህ እንደቀላል እያለፍከው ከሆነ ነገ መንገድህ ላይ የማትወጣው ዳገት ነው የሚሆንብህ

አምኖን፡- ሊሆን ይችላል

አቢሰሎም፡- ስለአንተ አንድ ጥያቄ አለኝ

አምኖን፡- ባትጠይቀኝ ደስ ይለኛ

አቢሰሎም፡- ለምን

አምኖን፡- እኔ ስለራሴ የማውቀውን ያህል ነው እናንተ የምታውቁኝ፡፡ አንዳችም የተሰወረ ነገር እንደሌለኝ ተምናለህ፡፡

አቢሰሎም፡- እውነቱን ልንገርህ ከትእማር .....

አምኖን፡- /ደንግጦ/ ከትእማር .... ከትእማር ምን

አቢሰሎም፡- ከትእማር ልደት በኋላ ፍጹም ተለውጠሀል ብቸኝነትን ትመርጣለህ .... በሀሳብ ትዋጣለህ... መተኛገት አብዝተሀል.... ያነጫንጭሀል... ስለዚህ የሆነ ነገር እንደሆንክ እገምታለሁ

አምኖን፡- እያወራኸኝ ያለኸው ስለምትገምተው ነገር ነው። ግምት ደግሞ ትክክል ላይሆን ይችላል።

ሌጊዮን፡- ሊሆንም ይችላል

አምኖን፡- አላውቅም ስለምትሉኝ ነገር እራሴ ላይ አጣሁት

አቢሰሎም፡- ግድ የለህም ወንድሜ ሆይ ፍርሀትህን ከውስጥህ አውጣ እስከ ዛሬ ፍቅራችንን የሚያውኩ፣ አንድነታችንን የሚበትኑ፣ እነዚያ ጠላት ያነገበባቸውን ክፉ ግዜያትን ተሸግረን እዚህ ደርሰናል።

አምኖን፡- ያሳለፍነውን ታሪክ አልረሳም እነዛ አስቀያሚ ወቅቶች እንደማይደገሙ አምናለው።

ሌጊዮን፡- እርግጠኛ ነህ

አምኖን፡- በሚገባ

ሌጊዮን፡- ታድያ ችግርህን ተናገራ

አቢሰሎም፡- አየህ ክርስቶስ የተቸገሩትን የሚረዳ፣ያዘኑትን የሚያጽናና የተጨነቁትን የሚያረጋጋ ነው። እሱ እኮ እንደለተሎች አማልክት ነኝ ባዮች አስጨናቂ አይደለም። የኛ ጌታ የትህትና አምላክ ነው። ትህትና እና ትሁታንን ይወዳል እርሱ ሰላም ሆኖ ከሰላም አርበኞች ፊት የሰለፋል እርሱ ሰላም እና ፍቅር ነው።

አምኖን፡- ፍቅር ከእርሱ ሌላ የለም?

አቢሰሎም፡- ጽድቅን የመሻት የመልካም ነገር ፍቅር የጌታችን የበሀሪ ገንዘቡ ነው የሀጥያት ፍቅር ጸብ እና ጥላቻ ግን የጥንት ጠላታችን የዳቢሎስ ማእረግ ናቸው። /ራማ ከውስጥ ትወጣለች/

ራማ፡- አቢ እማማ ተንስታለች ፀሀይ መሞቅ ሳትፈልግ የቀረች አይመስለኝም። ሌጊዮን እንደምን አረፈድክ

ሌጊዮን፡- /ጎንበስ እያለ/ከወገቤ ጎንበስ ብዬ ሰላምታ አቀርብልሻለው

ራማ፡- /እያጎነበሰች/ እኔም ጎንበስ ብዬ ምስጋና አቀርባለው /ራማ እና አቢሰሎም ወደውስጥ ይገባሉ/

አምኖን፡- መንፈሴ ተረጋግቶ ሊቀመጥ አልቻለም።ጠባቡ አይምሮዬ በየማእዘኑ በጭንቀት አውታር ተወጥሮ ይጮሀል እሪታን ያሰማል

ሌጊዮን፡- የምን ጩኸት

አምኖን፡- እኔም ለሰማው እና ላስተውለው የተሳነኝ እሱ ነው። ግን ይጮሀል። የተደበለቀ ጩኸት በውስጤ ሲያስተጋባ ይሰማኛል። ራሴን ለማዳመጥ ብዙ ሞከርኩ። ግን አልቻልኩም።

ሌጊዮን፡- ፍቅር ይዞሀል/አምኖን ደንግጦ ዝም ይለዋል/ መልስህን እየጠበኩ ነው

አምኖን፡- በ.... ጭራሽ

ሌጊዮን፡- ደግመህ አስብ

አምኖን፡- ይሄው ነው

ሌጊዮን፡- ቀድሞ ፍቅር ክርስቶስ መሆኑን ትመሰክር ነበር፡፡ አሁን ግን ፍቅር ከክርስቶስ ሌላ መኖሩን አቢሰሎምን ጠየከው፡፡ ይሄ ምን ማለት ነው? ወይ በክርስቶስ እምነት የለኸም አልያም ከእርሱ ሌላ ፍቅር መኖሩን ታምናለህ ማለት ነው፡፡

አምኖን፡- ጥያቄህ ክርስቶስ አይሁዳውያንን የዮሀንስ ጥምቀት ከሰማይ ወይንስ ከምድር? ብሎ የጠየቃቸው አይነት ከበደኝ፡፡ በክርስቶስ እምነት አለኝ በልህ? ሌላ ፍቅር መኖሩን ሰለምን አቢሰሎምን ጠየከው ትለኛለህ ሌላ ፍቅር መኖሩን አምናለው ብልህ ክርስቶስን እንደከዳሁት ተቆጥርብኛለህ፡፡ መልስ የለኝም ጥያቄህ እምነቴን በብርቱ ፈተነው፡፡

ሌጊዮን፡- ሀሳብህን ልረዳ እንደጂ እምነትህን ልፈታተን ፈልጌ አልነበረም፡፡ አቢሰሎም ለምን እንደጠየከው ገብቶኛል፡፡

አምኖን፡- ይሄ ምለት እኮ በውስጤ ያለውን ጩኸት አዳምጠህል ማለት ነው፡፡

ሌጊዮን፡- አዎ የውስጥህ እሪታ በአይንህ እየወጣ ይሰማኛል ወንድሞችህ ይህን ማዳመጥ አይንህን ማንበብ ነው የተሳናቸው አምኖን ቀጥተኛ መልስ ስጠኝ ትእማርን ትወዳታለን አይደል /አምኖን ደንገጦ ዝም ይለዋል/ የእናት አባትህ ልጅ ከልጅነት እስከ እውቀት በመደጋገፍ ያደጋቹ እህትህ ነች፡፡

አምኖን፡- አዎ! ማንም ሰው እህቱን የሚወደውን ያህል እወዳታለሁ

ሌጊዮን፡-ተው ተው እኔ አቢሰሎም ወይም ስምኦን ስላልሆንኩ አትፍራኝ፡፡ የምፈልገው ስለማውቀው ነገር ከአንደበትህ ማረጋገጫ ነው፡፡ ማንም ወንድ ለእህቱ ካለወ መውደድ በላይ አንተ ትእማርን በእህትነት ሳይሆን በፍቅር ነው የምትመለከታት፡፡ ከእንግዲህ እህትህ ሳይሆን ባለቤትህ ተብላ እንድትጠራ ትፈልጋለህ፡፡

አምኖን፡- ሀሰት! ሌጊዮን ስለፈጠረህ ተወኝ!

ሌጊዮን፡- መልካም ፍላጎትህ እንደ ሀሳቤ ካልሆነ እማርን ማግባባት እችላለው ማለት ነው

አምኖን፡- በምን?

ሌጊዮን፡- በፍቅሯ የተንበረከከ ለትዳር የሚመኛት ሰው አለ እንዳገናኘው ሲለምነኝ አንተ ትፈልጋታለህ ብዬ ነበር ልጁን ቸል ያልኩት ሀሳብህ ይሄ ከሆነማ እሷን አግባብቼ አገናኛቸዋለሁ፡፡

ትእማር፡- ለሰርጉ ለት ተሞሽራ እንደኮከብ አብረቅርቃ በፀአዳው ውበቷ ሀገሬው ጉድ ሲለኝ ያኔ አጨብጭበህ ትሸኛታለህ /ለሌጊዮን ሊወጣ ሲል ራማ ከውስጥ ተመጣለች/

አምኖን፡- /በጩኸት!/ ቆይ

ራሚ፡- /ደንግጣ እያማተበት/ ምንድን ነው አምኖን እንደዚህ በቁጣ ያስጮኸክ

አምኖን፡- ምንም አልሆንኩም

ራሚ፡ ተቆጣከኝ እኮ

አምኖን፡- /በቁጣ/ ምንም አልሆንኩም

ራሚ፡- አሁንም እኮ እየተቆጣህ ነው

አምኖን፡- እባክሽ ዝም በይ

ራሚ፡- እንደዚህ መሆንህንማ እያየው ዝም አልልም፡፡ ማንም ሰው ያለአንዳች ችገር በቁጣ አይገነፍልም፡፡

አምኖን፡- አንቺ ልጅ ነሽ በትልልቆች ጨዋታ መሀል ልግባ አትበይ

ራሚ፡- ከዚህ ቀደም የምታውቀው በሙሉ ስትነግረኝ ልጅ ነሽ ብለኸኝ አታውቅም፡፡ የዛሬዋ ቀን ከወትሮ በምን ተለየች /ዝም ብሏው ወደ ሌጊዮን እየተጠጋች/ምንድን ነው ሌጊዮን

ሌጊዮን፡- ምኑ?

ራሚ፡- እየሆነ ያለው ነገር

ሌጊዮን፡- ለአንቺ የሚነገር አይደለም

ራሚ፡- ለምን

ሌጊዮን፡- ልጅ ስለሆንሽ

ራሚ፡- /በንዴት እና በእልህ አተኩራ እየተመለከተችው/ እዚህ ቤት ውስጥ የተተከለው መጥፎ ነገር ምንድን ነው

ሊጊዮን፡- እኔ ምን አውቃለሁ?

ራሚ፡- ታውቃለህ! ከታእማር ልደት በኋላ እማማ ፍፁም ሰላም እርቋታል፡፡ያንተ ስም ሲነሳባት እንኳን ገፅታዋ ሲለወጥ አስተውላለሁ፡፡ ስለአምኖን ፀባይ መለወጥም የምታውቀው ነገር ይኖራል፡፡

ሌጊዮን፡- ስሚኝ! ስለ እናትሽ እርሳቸውን ጠይቂያቸው፡፡ ስለ አምኖንም ይሄው እፊትሽ፡፡

ራሚ፡- አንተ ልትነግረኝ አትችልም?

ሌጊዮን፡- አልችልም

ራማ፡- ለምን

ሌጊዮን፡- ህፃን ስለሆንሽ /በንዴት ትወጣለች/

አምኖን፡- ትንሿ እንደዚህ ከሆነች ትልልቆቹን እንዴት ነው የማልፈው

ልጊዮን፡- በትንንሽነገር አይምሮህን አታስጨንቅ። እራስ ምታት የሆነብህበአለም ላይ እንደዚህ ያለ ባለታሪክ እኔ ብቻ ነኝ ብለህ ስለምታስብ ነው። ለነገሩ የአለምን ህይወት ስለማታውቅ ብታስብም አይደንቅ። የገጠመህ ነገር እንዴት ቀላል እና የምታከብደውን ያህል እንዳልሆነ ብሎም ትእማርን የግልህ የምታረግበት ዘዴ ወጣ ብለህ የህይወትን አንዱን ገፅታ ብትመለከት ታገኘዋለህ። እኔ ያንን ህይወት ላሳይህ ቃል እገባልሀለሁ። ልብ አርግ አለምን ማየት መንፈሳዊነትን መክዳት ማለት አይደለም።

አምኖን፡- እንዴት ብዬ ነው ቤተሰቦቼን የአለምን ህይወት ማየት እፈልጋለሁ ብዬ የማሳምናቸው

ሌጊዮን፡- ጅል አትሁን እንጂ የሆነ ገዳም መጎብኘት እፈልጋለው ብሎ ሰበብ ማቅረብ ምራቅን የመዋጥ ያህል ቀላል ነው። ለማንኛውም እኔን ማግኘት ከፈለክ ማታ እታቸኛው ግሮሰሪ እጠብቅሀለው።/ለመውጣት ወደበሩ እየኄደ/ ይሄ ሁለተኛው ምእራፍ ነው።

አምኖን፡- /በተመስጦ ከወድያ ወዲህ ይንጎራደዳል ትእማር ትገባለች አላያትም ብቻውን ያወራል/ ችግር እንጂ ጭንቀቱ አልገባውም። የኔ ችግር የልቤ እርሀብ ትእማር ነች። ጭንቀቱ ውርደቱ ሲገለፅላቸው ማቅ ለብሰው ትቢያ ነስንሰው ስለነውሬ ቤተሰቦቹ እግዚኦ ማለታቸውን ሳስበው ምድር ከዳኝ እመቀምቅ የምወርድ ነው የሚመስለኝ።

ትእማር፡- እምኖን/አምኖን ሲያት ይደነግጣል/ መብራት ይጠፋል

ትዕይንት ሶስት

/መብራት ሲበራ እናት ተቀምጠዋል። ትእማር ፀጉራቸውን ተሰራቸዋለች። አቢሰሎም ይፅፋል። ራማ ከውስጥ ሆና ትዘምራለች። ዝማሬዋን ስትጨርስ፡-

ትእማር፡- እንዴት አይነት ዘማሪ እንደሆነች ሰማሻት አይደል? ሀያ አራት ሰዓት ሙሉ ብትዘምር የሚደክማት አይነት አይደለችም። በቀደም የእመቤታችን የንግስ በአልለታ ምእመኑን በቅፅሩ ሰብስባ ዘምራ ስታዘምር ነው ያመሸችው።በዝማሬ አገልግሎት ከሰንበት ትምህርት ቤቱ ዘማርያን ብሳ ተገኘች። የሰማት ሁሉ በአግራሞት እጁን በአፉ ጭኖ በተመስጦ ይሰማት ነበር።

አቢሰሎም፡- ትምህርት ቤቷ እንኳ በሙዚቃ ክፍለ ጊዜ ሌሎቹ ሲዘፍኑ እሷ ትዘምራለች አሉ

ትእማር፡- መምህሯ ምን ትል ይሆን

አቢሰሎም፡- በጣም ደስተኛ ነች። በትምህርት ሰበብ በየክፍሉ እያዞረች ታዘምራታለች። እማ እኔ ቀርቼብሽ እንደ ትእማር እና ራማ አይነት ሰላሳ ብትወልጂም አይቆጨኝም።

ትእማር፡- እንደውም አንተ ባትወለድ ነበር የሚቆጨው ባይሆን ራማ እንጂ እኔን የመሰለ ሰላሳ ምን ያደደርግላታል? አንተ እኮ እንደታላቅነትህ የሁላችንም መምህር ነህ ከአንተ ጋር ተቀምጦ በእውቀት እና በምክር ሳይሞላ የማይቀር ማንም የለም።

አቢሰሎም፡- አረተይ ትእማር

ትእማር፡- በትእግስትህ እና ለችግሮች መፍትሄ በመፈለግ የሚስተካከልህ የለም። አንተ እኮ የጠቅላላ እውቀት መጸሀፍ ነህ /አቤሰሎም ይስቃል/የምሬን እኮ ነው አንተ ቁም ነገር ማውራት ከጀመርክ በተመስጦ የሚያዳምጥህን ማነው ነፍሱን ይማረውና አባታችን እንኳ ጭንቀት ሲገጥመው አልያም ለችግሩ መፍትሄ ሲሻ ከስርህ አይጠፋም ነበር። እማማም አንተ አባባን ስትመክሪው

ሰምታ“ቀስ በቀስ አባታቹ አቢሰሎምን አባዬ ብሎ እንዳይጠራው” እያለች ታስቀን ነበር። አይደል እማ /እናት በአዎንታ ጭንቅላታቸውን ይነቀንቃሉ/

አቢሰሎም፡- አረ ዝም በሉ እንዲህ ስታወሩ ባተሌ መሆኔን የማያውቅ ሰው እንደ ታላቅ ቤተ መፅሀፍት ነው የሚቆጥረኝ

ትእማር፡- ነህና

አቢሰሎም፡ አይባልም

ትእማር፡- መቼምውዳሴ ከንቱን ፈርተህ እንዳልሆነ ተ ሰፋ አደርጋለው

አቢሰሎም፡- የለበስኩት ስጋ ደካማ መሆኑን ተጠራጥረሽ በውዳሴ ከንቱ አለመሸነፌን እርግጠኛ ያደረገሽ ምንድን ነው?

ትእማር፡- ወንድማችን እኛን እያበረታ ይሸነፋል ብዬ አልገምትም። እማዬም ጠንካራ ልጅ እንዳላት አትጠራጠርም /ከውጭ ስምኦን እና ሊጊዮን ይገባሉ/

ስምኦን፡- አምኖንስ

ትእማር፡- አረቀስ ወንድሜ ሆይ መጀመሪያ ሰላምታ አይቀድምም

ስምኦን፡- ከእናንተ ጋር አብረን ነው የከረምነው። እምኖንን ግን ላለፉት ለስምንትቀናት ሙሉ ስላላየሁት በጣም ናፍቆኛል።

አቢሰሎም፡- ለኛስ ወንድማችን አይደለም የማይናፍቀን መሰለህ?

ስምኦን፡- ወጣኝ?

አቢሰሎ፡ አልወጣህም።

ስምኦን፡- አልኩኝ?

አቢሰሎም፡- አላልክም። ግን በደንብ ይነፍቅሀል።

ስምኦን፡- እንዴት?

አቢሰሎም፡- ለተጨማሪ አምስት ቀናት እቆያለሁ ብሎ ደውሏል።

ስምኦን፡- አያደርገውም ጠዋት እየመጣው ነው ብሎ ደውሎልኝ?

ትእማር፡- እንግዲህ መንገድ ከጀመረ በኋላ ሌላ ገዳም አግኝቶ ሊገበኝ ይሆናል።

ስምኦን፡- ኡጭ ሲናፍቁት የማይገባው ምን አይነት ወንድም ነው ያለን /አቢሰሎም እና ትእማር ይስቃሉ/ ዋጡ ቅጧት

ሌጊዮን፡- እማማ እንደምን አረፈዱ? /ሊስማቸው ሲል ፊታቸውን ያዞሩበታል። ቀናሲል ራማ ወታለች ፊት ለፊት ይተያያሉ ሌሎቹን ሲመለከት አላስተዋሉትም/ ራማ እንዴትነሽ?

ራማ፡- ደህና

ትእማር፡- እማ ስምኦን ሲያኮርፍ ምን እንደሚመስል አየሽው

አቢሰሎም፡- የዚህን ያህል ከናፈቀህ ለምን ያለበት ቦታ አትሄድም

ስምኦን፡- እሄድስ

ትእማር፡- ሁኔታህ ትላንት አቢ የነገረንን ተረት መሰልከኝ። አቢ ተረቱን ለእማ ንገራት አጊሰሎም ይሄውልሽ እማ....

ራማ፡- አቢ እማማ መኝታ ክፍሏ መግባት ወይም ውጭ መሆን ፈልጋለች

አቢሰሎም፡- በምን አወቅሽ

ራማ፡- ጠየኳት

አቢሰሎም፡- ፈልገሻል እማ /እናት በአዎንታ ራሳቸውን ይነቀንቃሉ/ ታድያ ሁላችንም በአትክልቱ ስፍራ ሆነን ለምን አንጨዋወትም

ራማ፡- አይ በአሁን ሰአት ብቸኝነትን ነው የምትመርጠው /እናትን ይዛ ወደውጭ ትወጣለች ሌጊዮን ወደ መጣበት ይመለከታል/

ትእማር፡- ይቺልጅ የእማማን ስሜት ማንበብ ችላለች ማለት ነው

ሌጊዮን፡- እንግዲህ ከሁላችሁም ለእናታችሁማህፀን በቅርብ እርቀት ስለምትገኝ ይሆናላ

ትእማር፡- ሊሆን ይችላል። እንዴት ነበር የሄዳችሁበት ሰርግ

ስምኦን፡- ከቃል በላይ ነው። እንዴት ያምራልመሰላችሁ ሙሽራው ከነሚዜዎቹ ሙሽሪትም እንደዛው ከነ አጃቢዮቿ ፀአዳ መስለው ዘማርያኑ በማርያኑ በያሬዳዊ ስልት መርሀዊ ሰማያዊ እያሉ በመላእክት ጥኡም ልሳን ሲቀኙ ለቅዳሴ የተገኘ ምእመን በእልልታ እና በዝማሬ እያጀባቸው የሙሽሮቹን ትዳር የአብርሀም የሳራ ዘራቸውን እንደ ይስሀቅ በስላሴ ብስራት የተነገረለት እንዲሆን ሲመኙን ካህኑምይህንኑ እያለ ሲባርክ የሙሽሮቹ አይን እንባ አቀረረ።

አቢሰሎም፡- ለምን

ስምኦን፡- ፅድቅእርቀን በሀጥያት ለረጠብነው ለእኛ እግዚአብሔር እንደዚህ አደረገልን ሲሉ

አቢሰሎም፦-ሁላችንም በደለኞች ነን። ሰማይ እና ምድር እንኳ በእርሱ ዘንድ ንፁህን አይደሉም። እስከዛሬም ያለነው እንደሀጥያታችን ሳይሆን እንደ ቸርነቱ፣ እንደ በደላችን ሳይሆን እንደ ይቅር ባይነቱ ነው። ምንግዜም ከሺ በደላችን ይልቅ አንድ መልካም ጎናችንን ይመለከታል የበደላችሁትን ሰባ ጊዜ ሰባ ሰበባት ይቅር በሉ የሚል እሱ ምን ያህል ጊዜ ይምረን ይሆን?

ሌጊዮን፦- ስምኦንም ስርአተ ተክሊሉን ሲመለከት ለዚህ የሚደርስበትን ቀን ናፈቀ።

ስምኦን፦- እውነት ነው የእናንተንም የጋብቻ ቀን የምመለከትበትን እለት ተመኘሁ እናታችንም የኛን ጋብቻ ስትመለከት ደስታዋ ወሰን አይኖረውም።

ትእግር፦- የሰርጋችሁን እለት እንዲያሳየኝ እፀልያለው እናንተ ግን የእኔን አታዩም /ሁሉም በአንድ ድምፅ/ለምን

ትእግር፦- ሀዋርያው ብትችሉ እንደኔሁኑ ይላል። እንደሱ በድንግልና መኖር ቀላል ሆኖ አይደለም ፈተናው እጅግ የበዛ ነው። ቢሆንም ግን ሀይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለው።

ሌጊዮን፦- እና ሳታገቢ በድንግልና መኖርን ነው የምትመርጪው

ትእግር፦- አዎ /ከውስጥ አምኖን ፀጉሩን እና ፊቱን በፎጣ እያደራረቀ ይወጣል

አምኖን፦- ስምኦን /ስምኦን ሲመለከተው ግራ ይገባና በደስታ ሰውሜት ያቅፈዋል ይተቃቀፋሉ ሰላምታ ይለዋወጣሉ

ስምኦ፦- ትጫወቱብኛላቹ አይደል /አቢሰሎም እና ትእግር ይስቃሉ/ ስለናፈከኝ አንተን ለማግኘት እየጋለብኩ ስመጣ ተመካከረው ለተጨማሪ አምስት ቀን ይቆያል አይሉኝ መሰለህ /አምኖን ይስቃል ከሌጊዮን ጋር እያተቃቀፈ ሰላምታ ይለዋወጣሉ።

ሌጊዮን፦- እንኳን ለቤትህ አበቃህ

አምኖ፦- እንኳን ደህና ቆያችሁኝ

ስምኦን፦- የዚህን ያህል ቀን ተለያይተን ስለማናውቅ ናፍቆት የሚባል ነገር አሁን ነው የገባኝ። በዚህ አይነትማ ለረጅም ጊዜ ሳንተያይ ብንቆይ ምንድን ነው የሚውጠን

አምኖን፦- ያለያየን አምላክ መልሶ እስከሚያገናኘን ናፍቆቱን በትዕግስት መቻል ነው

ትእግር፦- /የአምኖንን ፀጉር እና ፊቱን እየዳበሰች በስስት ትመለከተዋለች ከስተህ ነው? ወይንስ አይኔ ነው?

አቢሰሎም፦- ሰውነቱ ትንሽ ቀንሷል

ስምኦን፦- ለኔምታይቶኛል

ሌጊዮን፦- ምን ማለታችሁ ነው? የሄደው ገዳም እንጂ ሆቴል እኮ አይደለም

ትእማር፡- እስቲ ስለገዳሙ ንገረን

አምኖን፡- የሚገረማችሁ በገዳሙ ውስጥ አባቶች አሉ /ትእማር ስምኦን እና አቢሰሎም በአንድነት ይስቃሉ/ /አምኖን እና ሌጊዮን ይተያያሉ

አምኖን፡- ምነው

አቢሰሎም፡- አባቶች የሌሉበት ገዳም አለ እንዴ

አምኖን፡- እንዳዛ ለማለት ፈልጌ ሳይሆን ከወጣቶች እድሜ ጠገብ እስከሆኑ አባቶች ተሞልቷል በዘመናዊ የቀለም ትምህርት ከሰርተፍኬት አንስቶ በየደረጃው እስከ ፕሮፌሰር ድረስ አለብት የድግሪ ምሩቃንማ ብዙ ናቸው

አቢሰሎም፡- አለም በቃኝ ብለው

ሌጊዮን፡- መቼም ማስተርሳቸውን ለመስራት ገዳም አይገቡም። እኔ የምልህ የዱር እንስሳቶችስ አሉ

አምኖን፡- እጅግ በጣም ብዙ

ሌጊዮን፡- ደግሞ ታማኞች ናቸው አይደል

አምኖን፡- ታማኝነታቸውን ስትመለከትማ ሰዎች ነው የሚመስሉህ

ስምኦን፡- የገዳሙን ስም እኮ አልነገርከንም

አምኖን፡- /ደንገጥ ብሎ ሌጊዮንን ይመለከትና/ እ...... እ....

ሌጊዮን፡- ክብረ ቅዱሳን የአንድነት ገዳም ነው ያለከኝ

አምኖን፡- እ .... አዎ መጠርያው እንደዛ ነው

አቢሰሎም፡- መቼ እና በማን ተመሰረተ? በገዳሙ ያየኸው አስደናቂ ነገርስ ጥንታዊ ቅርሶችስ አሉበት።

አምኖን፡- /ይደነግጥ እና ሌጊዮንን ይመለከተዋ ሌጊዮን ዝም ይለዋል ወደ አቢሰሎም እየተጠጋ/ አንተ አረጀህ እንዴ የምን ሽበት ነው የሚታየኝ

አቢሰሎም፡- ሽበትኩ እንዴ/ስምኦን እና ትእማር የአቢሰሎምን ፀጉር ይመለከታሉ/

ስምኦን፡- ሽበት የታለ

አምኖን፡- ጆሮው ላይ።

ትእማር፡- ጆሮው ላይ?

አምኖን፡- ማ .... ማለቴ ጆሮው አካባቢ

ስምኦን፡- አረ የለም

አምኖን፡- አይኔ ነው ማለት ነው

ስምኦን፡- መሆን አለበት

አምኖን፡- /በረጅሙ ይተነፍስና/ ድካሙ አለቀቀኝም ማለት ነው

አቢሰሎም፡- እሺ ...

አምኖን፡- እኔ የምለው ስለሰበሰብናቸው ነዲያን ምን ታሰበ

ትእማር፡- ይሄ የአንተ ስራ ነው።ሀላፊነቱን እኮ የሰጠንህ ንብረቶቻችንን ብቻ እንድታስተዳድር ብቻ ሳይሆን እነዚህን እና መሰል መንፈሳዊ ስራዎችን በበላይነት እንድትመራ ነው።

አምኖን፡- ቢሆንስ የእናንተ እርዳታ አያስፈልገኝም

ስምኦን፡- እሱማ የግድ ነው። ላለፉት 15 ቀናት ቀድሞ በነበረው አሰራር ነው የቆየነው። አሁን ደግሞ የአንተን አዲስ ሀሳብ እንሻለን።

አምኖን፡- ስለዚህ ዛሬ መጀመር እንችላለን

አቢሰሎም፡- ደስ ይለናል

አምኖን፡- መልካም። ሰራተኞቹን ለአራት ህብረት እንከፍላቸዋለን። አንዱን ህብረት አቢሰሎም ያዝና ስለነዳያን መረጃ ሰብስብ። እያንዳንዱን ነዳይ በጥልቀት መርምር። በምን አይነት የስራ መስክ ተሰማርተው አራሳቸውን እንደሚችሉ ጥናት አድርግ ሀሳቤ ገብቶሀል

አቢሰሎም፡- በትክክል

አምኖን፡- ትእማር ደግሞ ሁለተኛውን ህብረት እየመራሽ በአጥቢያው የሚገኙትን ሀያ ሶስቱንም አብያተ ክርስቲያናት የጎደላቸው ነገር ምን እንደሆነ በአጭር ግዜ በመካከለኛ እና በረጅም ጊዜ ሊሟላላቸው የሚገቡ ነገሮች ምን እንደሆኑ ጥናት ታደርጊያለሽ

ትእማር፡ ታዛዥ ነኝ

አምኖን፡- ስምኦን ደግሞ ሶስተኛውን ህብረት ይዘህ ሀያ ሶስቱም አብያተ ክርስቲያን የሚሳተፉበት በወር ሁለት ግዜ የሚደረግ ትላልቅ የአንድነት ጉባኤ እንዲዘጋጅ ታደርጋለህ።ለጉባኤው ማግር ከከተማም ሆነ ከሩቅ ሀገር መምጣት ያለበት ነገር ካለ ይምጣ።

በተለይ የጉባኤው መክፈቻ እና መዝጊያ እለት ምእመኑ ከተለያየ ሀገራት እንዲመጡ በመገናኛ ብዙሀን ማስታወቂያ አስነገር። ምዕመኑ ሲመጡ የሚያርፉበተ ድንኳኖች ከወዲሁ እንዲሰሩ አድርግ። ተግባባን?

ስምኦን፡- ግልፅ ነው

አምኖን፡- አራተኛውን ህብረት ደግሞ ከእኔና ከሌጊዮን ጋር በመሆን የገበያ ጣናት እናደርጋለን። በዛውም እያንዳንዱ አምራች ለምርት የሚቀምባቸው ግብአቶች ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ እና የምናመርታቸው ምርቶች ለተጠቃሚ ሲደርሱ ፍፁም እንከን የለሽ መሆኑ በጥንቃቄ እንመረምራለን።

አቢሰሎም፡- ጥሩ ጅምር ነው

አምኖን፡- ስለዚህ ስራችንን ሰራተኞችን ለአራት ህብረት በመክፈል አሁን እንጀምር። ደሞዝም እንጨምርላቸው።

ስምኦን፡- መልካም /አቤሴሎም ስምኦን እና ትእማር ይወጣሉ/

ሌጊዮን፡- በረጅሙ ይስቅና/ ለምንድን ነው ስለገደሙ ሲጠይቁህ አንደበትህ የከዳህ

አምኖን፡- ስለማላውቀው ነገር ምን ብዬ ነው የማወራው ውሸት ለካ እንደዚህ ቀፋፊ እና አስደንጋጭ ነገር ነው

ሌጊዮን፡- ቀፈፈህ

አምኖን፡- መረረኝ አያልኩህ እርግጠኛ ነኝ ከተማ ለከተማ በየመሸታና ጭፈራ ቤት ሴተኛ አዳሪዎች ላይ ተንጠልጥዬ እንደከረምኩ ሳይገባቸው አልቀረም ስሜቴን ማንበብ ይችላሉ እያንዳንዷ የልቤን ትርታ ያዋቁታል።

ሌጊዮን፡- ባክህ አትጨናነቅ በገዛ ምናብህ የግምት ስእል እያስቀመጥክ ራስህን በፍርሀት የምትወጥረው እራስህ ነህ። ፊትህን እንጂ ስሜትህን ማንበብ አይችሉም። ፊትህ የስሜትህን እንዳያስነብብ የመጠንቀቁ ድርሻ ያንተ ነው፡፡

አምኖን፡- አለምን አየኋት ሁሉንም ነገር በጥቂቱም ቢሆን ቀመስኩት። ምንድን ነው ቀጣይ ማድረግ ያለብኝ ትእማርን የግሌ የማደርግበት ዘዴ የቱጋር ነው

ሌጊዮን፡- ሀብትህን በጠቅላላ ለበጎተግባር ማዋል ተገቢ ነው። ግን ለአንዳንድ የግል ጥቅሞችህ ገንዘብ እንደሚያስፈልግህ ተማምነናል

አምኖን፡- አዎ። ግን ከጠቅላላ ገቢው ላይ እንዴት ነው ገንዘብ ቆርጬ የማስቀረው

ሌጊዮን፡- ከጠቅላላ ገቢው ላይ ሳይሆን የራስህን መሬት ቆርጠህ ታከራየዋለህ መሬቱን በተመለከተ ሀላፊነቱን የሰጠኸው ለራስህ ስለሆነ ቤተሰቦችህ የሚያውቁት ነገር አይኖርም። እዛ ቦታ ላይ የምንመድበው ሰራተኛ መሬቱ ተቆርጦ እንደተከራየ መረጃ የማያቀብል ሰው መሆን አለበት።

አምኖን፡- ታድያ አሁን መሬቱን የሚቆጣጠረው ልጅ ምን ይደረግ

ሊጊዮን፡- ከቦታው ላይ ይወገዳል

አምኖን፡- /ደንግጦ/ ምን ልጁ እኮ በጣም ምስኪን ነው ቅጠል ሸጠው ያሳደጉት እናቱ ዛፍ ወድቆባቸው ላመታት የአልጋ ቁራኛ በመሆን የሚሰቀጥጥ ስቃይ ደርሶባቸዋል። በመኪና አደጋ የሞተችውን የታላቅ እህቱን ሶስት ህፃን ልጆች የማሳደግ ሀላፊነት በእርሱ ትከሻ ላይ ነው። ይሄ ሁሉ ችግር የሚጋፈጠው የኔን መሬት እያስተዳደረ በሚያገኘው ገንዘብ ነው። ይሄ ልጅ ስራውን ካቆመ ህመም የሚያሰቃያቸው ምስኪን እናቱ እና ከፋውን እና ደጉን ለይተው የማያውቁ የህፃናቱ ተስፋስ አያሳዝኑም

ሌጊዮን፡- ፈጣሪ ያላዘነላቸው አንተ ምን ቤት ነህ? እነሱ በገዛአንጃቸው ነው አንተ ግን ክብርህ፣ ማንነትህ፣ ፍቅርህ ምናልባትም ህይወትህ ስማኝ የግድ አስፈላጊ ከሆነ ለልጁ ሌላ መፍትሄ ይበጅለታል ግን የግድ ከቦታው ላይ መነሳት አለበት።

አምኖን፡- እናስ ቦታውን ማን ይቆጣጠር

ሌጊዮን፡ እሱን እና መሬቱን የሚከራዩትን ሰዎች ፈልጎ የማምጣቱን ድርሻ ለኔ ተወው ተከራዮቹ በቦታው የሚቆዩት አንተ ይህን ሀላፊነት ለመልቀቅ እስከተቃረብከበት ወቅት ብቻ ነው

አምኖን፡- መልካም

ሌጊዮን፡ ዋናው እና ትልቁ ስራህ የሚሆነው ትእማርን መገናኘት

አምኖን፡- ማለት

ሌጊዮን፡- ከጭኖቿ መሀል ገብተህ ዘርን ከአንተ እንድትቋጥር ታደርጋለህ /አምኖን ይደነግጣል/ የፍራቻህን ያህል ከባድ አይደለም። ከአንተ ከፀነሰች ፈሪሀ እግዚአብሔር ስላለባት ፅንሱን ሆዷ ውስጥ አፍርጣ አትገድለውም። ከአንድ ሰው ውጪ ከሌላ ጋር ግንኙነት መፍጠር አመንዝራነት መሆኑን ስለምታምን ከአንተ ሌላ ወንድ አታስብም ይሄ ግዴታዋ ይሆናል።

አምኖን፡- ቤተሰቦቼ እንደዚህ ያለ የተጨማለቀ ሀጥያት ውስጥ መግባቴን ሲረዱ ያወግዙኛል ትእማር እንደዚህ በፍቅሯ እየነደድኩ አምራ ብትጠላኝስ

ሌጊዮን፡- ቤተሰቦችህ የራሳቸውን እንጂ የሰውን ሀጥያት አይመለከቱም ይሄ እነሱን ልዩ የሚያደርጋቸው ሲሆን ለአንተ ደግሞ ልዩ እድል ነው። ማንም ሰው የምትፈልገውን አጊኝተህ ሁሉም ነገር ከተረጋጋ በኋላ ለዚህ መልካም ባህሪያቸው ምስጋናን እንደምታቀርብላቸው አውቃለሁ ለምን መሰለህ እግዚአብሔር እነሱን ከነከረፋ ሀጥያታቸው እንደወደዳቸው ስለሚያውቁ አንተን አይጠሉህም

አምኖን፡- እሺ ፈጣሪዬስ ለዚህ በደሌ የሚያዘጋጅልኝ ቅጣት ምንድን ነው? ከልጅነት እስከ እውቀት ህጉ እና ወንጌሉን በቤቱ እየተማርኩ አድጌ በድፍረት ሳሳዝነው በሰይፍ ነው የሚቀጣኝ

ሌጊዮን፡- ለምንድን ነው በራስህ ላይ ፍርሀት የምትጭረው? የአንተ ሀጥያት ከሰዶም እና ገሞራ ቢብስ ነው እንዴ እርሱን የሚያሳዝነው? ስማ አይደለም አንተ የአለም ህዝብ በሀጥያት ቢጨማለቅ የጤፍ ፍሬ ታህል አይደለም ክብሩ ደመና እንኳን ዝቅ አይልም። ሁላችንም በሞት ጥላ ስር ብንመላለስ እጣ ፈንታችንን እያሰብን ወየው ለኔ እያልን ልናለቅስ የሚገባን እኛ ነን።ከእንግዲ ሰውን

በመፍጠሩ አይፀፀትም።አንዴ ዋጋ ከፍሎልና እዳው የኛው ነው። ደግሞ አራቱን ባህሪያተ ስጋን ተሸክመህ ፍጹም መሆንን አታስብ ሁሉም ሰው ተፈትኖ ይወድቃል፤ ብርቱዎች ደግሞ ከውድቀታቸው ይነሳሉ። እስቲ ንገረኝ ማነው እንከን የሌለበት አብርሀም ጣኦት አምላኪ ነበረ። ያእቆብ አባቱን ኤሳው ነኝ ብሎ አታለለው ሙሴም በጥፋቱ በሲና ተራራ በስውር ተቀበረ። እንደ ልቤ የተባለው ዳዊት እንኳ በርሳብሄን አስተኝቶ ባሏ ኦርዮንን በጦር ሜዳ አስገደለ። ጥበበኛው ሶሎሞንም ቤተመቅደስ በገነባበት እጁ የጣኦት ቤትን አነፀ።የክርስቶስ ምሳሌ የተባለው ሶምሶንም በዝሙት እና በስካር መንፈስ ወደቀ። ንገረኝ እስቲ አንተ ከማናቸው ትበልጣለህ? ደግሞ አንተ በምኩራቡ በአገልጋዮቹ እግር ስር ተቀምጠህ ሀሁ እና ወንጌሉን ስትማር እግዚአብሔር ሃጥያተኞችን ይቀጣል ከሚለው ቃል በላይ ፍቅሩንና ይቅር ባይነቱን ተምረሀል።

አምኖን፡ እና

ሌጊዮን፡- እናማ እንደነገርኩህ ነው። እርግጥ ነው ወንድሞችህም ሆኑ ትእማር ሊደነግጡ ይችላሉ አማራጭ ስለሌላቸው የግድ ይለምዱታል። ግድ የለህም እኔ እያለሁልህ አትፍራ። እስከመጨረሻው ከጎንህ ነኝ። ደግሞ ቅድም ስለጋብቻ ሲወራ የመግባት ፍላጎት እንዳላት ስታወራ ነበር። ሊያገባት የሚፈልግ ወንድ አግኝታ ከማግባት ወደ ኋላ አትልም። ደግሞ ለትዳር የሚፈልጋት ሰው እንዳለ ነግሬሀለው። ስለዚህ ፍጠን ብቻዋን የምታገኝበትን ግዜ እና ቦታ እኔ አመቻችልሀለው። /ከውጭ እናት እና ራማ ይገባሉ/

እምኖን፡- እማ እንዴት ነሽ? በጣም ናፍቀሽኛል። አሁንስ ጤንነትሽ እንዴት ነው /አብሯቸው ወደውስጥ ይገባል/

ሌጊዮን፡- /ብቻውን ይስቅና/ ሶስተኛው ምዕራፍ ሊጀምር ነው። አጀሪት ድንግልናዋን ጠብቃ በምንኩስና ልትኖር....! ህ..... ህልሟ ቅዠት ሆኖ ይቀራል። እኔ ግን ህልሜን ለማሳካት አንዳችም የሚሳነኝ ነገር የለም። አምኖን ሙሉ በሙሉ በመዳፌ ውስጥ ነው። በተመቸኝ ሰዓት ወዳሻኝ ቦታ እንደከብት ልነዳው መብት አለኝ። ትእማር የንፅህናዋ ምልክት የክብሯ ምልክት የድንግልና ስጋዋ በገዛ ወንድሟ ሲቀረደድ ከክብር አሳንሷት ደሟ ሲቆሽሽ ያኔ ቀሚሷን ቀዳ ማቃ ለብሳ ትቢያ ነስንሳ በገዛ እንባዋ የወጣትነት ገላዋን ስትቀቅለው..! አምኖንም በጠላትነት ከገዛ ወንድሞቹ ጋር ተፋጦ ለበቀል ሲፈልጉት..! ያን ግዜ.. ያን ጊዜ የዚህ ቤት የህልውና አምዶች እንደ ገመድ ተጠቅልለው ይበጣጠሳሉ። /አምኖን እና ራማ ከውስጥ እያወሩ ይወጣሉ/

ራማ፡- እንዴት ነበር የ 15 ቱ ቀን ቆይታህ?

አምኖን፡- በጣም አስደሳች ነበር?

ራማ፡- እውነት ግን ገዳም ነበር የሄድከው?

ሌጊዮን፡- ምነው ንግግርሽ ላይ ጥርጣሬ ታየበት?

ራማ፡- መጠርጠሬ ስህተት ይሆን?

ሌጊዮን፡- ላይሆን ይችላል ግን እንዲሁ በባዶሜዳ?

አምኖን፡- ምንድን ነው ያጠራጠረሽ?

ራሚ፡- የት/ቤት ጓደኞቼ ቅዳሜ እና እሁድን በከተማ ከዘመዶቻቸው ጋር ነው የሚያሳልፉት ሁለቱም ጓደኞቼ ወንድሞችሽን በከተማ አየናቸው አሉኝ።

አምኖን፡- ተመሳስዬባቸው እንዳይሆን?

ራሚ፡- እኔም ተሳስተው መስሎኝ ነበር።

ሌጊዮን፡- ነበር ማለት አሁን አመንሻቸው?

ራሚ፡- በትክክል

አምኖን፡- ማመንሽ ስህተት ነው። ከአቢሰሎም ወይንስ ከስምኦን ጋር ነው ያዩኝ

ራሚ፡- ሌጊዮንም ወንድሜ ነው የሚመስላቸው። ስለዚህ ከእሱ ጋር ሊያዩህ ይችላሉ። ገዳም አለመሄድህን ያረጋገጠልኝ ግን ሌላ ነው

አምኖን፡- ምን

ራሚ፡- ልብስህን ለአጣቢዋ ለመስጠት ሻንጣህን ስከፍት አንተ ላይ ያለመድኩትን ጠረን በልብስህ ላይ አገኘሁት። ቀድሞ በቅዳሴ እጣን የታወደው ልብስህ አሁን ግን ሲጋራ ሲጋራ ይላል።/አምኖን ደንግጦ ሌጊዮንን ያየዋል/ እሱን አትየው ለኔ መልስ ስጠኝ

አምኖን፡ ምን መሰለሽ ለምሳ ያረፍኩበት ሆቴል አጠገቤ የተቀመጠው ሰውዬ ሲያጨስ ነበር

ራሚ፡- እንደዛስ ቢሆን ያደረከው ልብስ ላይ እንጂ ሙሉ ልብስህ ላይ ነው ወይንስ ሰውዬው ሻንጣህ ውስት ገብቶ ነው ያጨሰው? ጃኬትህ ኪስ ውስት አንድ ጅምር እና ሁለት ያልተለኮሱ ሲጋራዎች ከነላይተራቸው አገኘሁ። ልብስህም መልካም ሽቶ ተቀብቷል። ይሄ ግራ ሲያጋባኝ ያስደነገጠኝም ነገር አገኘሁ።/ከኪሷ ኮንዶም አውጥታ እያሳየችው/ ቀድሞ ስሙ እንኳ እዚህ ቤት ተጠርቶ የማያውቀው ነገር አንተ ሻንጣ ውስጥ ግን በቀለማት እና በአይነት በክብር ተቀምጧል። የዚህ ጥቅም በመንፈሳዊ አይን ብንመለከተው የዝሙት ጠንቅ መከላከያ አልያም እግዚአብሔር ምድርን እንድንሞላበት የሰጠንን ዘር ማምከኛ ነው።

ሌጊዮን፡- ምነው የዚህን ያህል የሰይጣን መሳርያ አደረግሽው

ራሚ፡- መልካምነቱ ለአለማዊ ኑሮ ለስጋ ጥቅም ነው የእግዚአብሔር መንግስት ለሚሹ መንፈሳዊያን ግን እንዳልከው የሰይጣን መሳርያ ነው አምኖንም ይህን ያምን ነበር

ሌጊዮን፡- ነበር ስትይ

ራሚ፡ ምናልባት አለምን አሳይተከው ሀሳቡን ካልቀየረ በቀር

ሌጊዮን፡- ይሄ አንቺ እና ጓደኞችሽ ተባብራችሁ የቃዣችሁት ቅዠት ነው።

ራሚ፡- ሌጊዮን እዚህ ቤት ውስጥ ምንድን ነው ያለው

ሌጊዮን፡- አላውቅም

ራማ፡- ቅድም እማማን ሰላም ልትላት ስትል እንዴት ፊት እንደነሳችህ ተያይተናል ሌሎቹ አይናቸው እንጂ ማስተዋላቸው ስለተከደነ አላስተዋሉህም። አምኖንም ከቀደሞ ምንነቱ ውጭ እንደሆነ እኔም አንተም እናውቃለን

ሌጊዮን፡- እና ምን ይፈጠር ነው የምትይኝ

ራማ፡- የእናቱ እና የወንድሜ ደህንነት ያሳስበኛል ስለዚህ

አምኖን፡- ስለዚህ እሱ ምን ያድርግሽ? ራማ ደግሞ አንቺ ልጅ ነሽ ሁሉንም ነገር ልወቅ አትበዪ። እድሜሽ ማወቅ የሚገባሽን ነገር ስትሻገሪ ብቻ ነው መልካም የሚሆነው። ከአቅምሽ በላይ ልወቅ ብሎ መንጠራራት ግን የአእምሮሽን ጫንቃ በድካም ማዛል ነው ትርፉ።

ራማ፡- መንፈሴ ተጨነቀ። እስከ ዛሬ በፍቅር እና በፈገግታ ነበር ያደኩት

አምኖን፡- እናስ ጎደለብሽ?

ራማ፡- ካንተ አዎ። አካሄድህ እንዲህ ከሆነ እንዳልነበርን እንሆናለን። የማማም ፀባይ እኮ እንደዚህ አልነበረም ለኔ እንደሚገባኝ በነዚህ ችግሮች የሌጊዮን እጅ የእንዳለበት ነው። ደግሞም አልተሳሳትኩም

ሌጊዮን፡- ሴትዮ ቀስ ብለሽ ከላዬ ላይ ውረጂ

ራማ፡- ስማኝ እማማ እንደበቷ ዝግ ነው አምኖንም አንተ ካልፈቀድክለት በስተቀር እሱም ከሷ አይለይም

አምኖን፡- ራማ

ራማ፡ አዎ አንዳች ነገር ስጠይቅህ ልጅ መሆኔን ትነግረኛለህ። ያልጠየኩህን ስትመልስ መናገር እንደማትችል ገባኝ። የእማማን ስሜትስ ከፊቷ አንብበኋዋል። /ወደሌጊዮን እየተጠጋች/ ለዚህ ነው ለአንተ ያላት ጥላቻ ምን ያህል የመረረ እንደሆነ የገባኝ።

አምኖን፡- /በቁጣ/ ብቻችንን መሆን እንፈልጋለን ተይን

ራማ፡- አንተም ተቆጣሽኝ? መልካም የቀደመ አንተነትህ ተለውጧል ለሊት በሰዓታት፣ ንጋት በማህሌት፣ ማለዳ በቅኔ ከመቅደሱ እንዳልተለየህ አሁን መገኛህ አልጋ ስራህ እንቀልፍ ሆኗል። የቤተ መቅደስ የእጣኑ መአዛ በልብስህ ታትሞ የክርስትና ህይወትህን እንዳልሰበሰከ ያሁኑ የሲጋራ ጭስ የቱን ህይወትህን እንደሚመሰክር ግልፅ ነው። ቀድሞ እግዚአብሔር መንግስት ለመውረስ እንዳልተንበረከክ አሁን ግን በአለም መድረክ ላይ ጨፈርክ።

አምኖን፡- በቃሽ ራማ በቃሽ!

ራማ፡- አንተም ይብቃህ “የቀደመው ፍቅርህን ትተሀልና የምነቅፍብህ ነገር አለኝ።” የተባለው ላንተ ነው ከእንግዲህ ከወዴት እንደወደክ አስብ። ንስሀም ግባ።የቀድሞ ስራህንም አድርግ። አለበለዚያ ይመጣብሀል መቅረዝህንም ከፊትህ ይወስደዋል። የተደገፍክበት

አለም ቀልጣ ትጠፋለች። አለምን የፈጠረ እግዚአብሔርን ብትይዝ ግን ለዘለአለም ህያው ትኖራለህ። ወንድሜ ሆይ ለእስቂያስ የተሰጠ ንስሃ ለአንተም ነው እንደ ጴጥሮስ ከውድቀትህ ካልተነሳህ እንደ ይሁዳ ትሞታለህ /ትታው ወደ ውስት ትገባለች/

ሌጊዮን፡ እህስ ጌታው የዝህችን ህፃን ንግግረ ሰምተህ ከሷ ጋር ትሆናለህ ወይንስ ከኔ ጋር። /ዝም ይለዋል/ ትልልቆቹን ለመሻገር ትንሿን ማለፍ የግድ ነው /ዝም ይለዋል/ ጌታው ወስና እኔን ወይስ....

አምኖን፡- ከአንተ ሌላ ምን ተስፋ አለኝ አነተን ተማምኜ አይደል እንዴ መንገድ የጀመርኩት መንገዴን ጨርሼ ትእማርን በእጄ ካላስገባው በጭንቀት እብጄ መሞቴ አይቀርም። ከገባሁበት መከራ ትታደገኝ ዘንድ የአንተ እርዳታ ያስፈልገኛል።

ሌጊዮን፡- መልካም። በጥልቀት እንዳናወራ ይሄ ቤት አልተመቸኝም። አንድ ሁለት እያልን ብናወራ ቅር ይልህል

አምኖን፡- አረ በጭራሽ አሁንማ ለምጄው። እንዲያውም እራሴን እያመመኝ ስለሆነ ያስፈልገኛል። ደግሞ ወይን ያስተፈስህ ልበ-ሰብ ተብሎ የተመለከረለተን የህይወት ውሀ ጋብዘከኝ ልቃወምህ ነው ባይሆን በኔ መሪነት እንጂ /ሁለቱም ይስቃሉ/ በል እንውጣ /ለመውጣት በሩ ጋር ደርሰው/

ሌጊዮን፡- ኦ... ኮቴን እረስቼ ልወጣ ነበር/ሌጊዮን ሲመለስ አምኖን ይወጣል ለጊዮን ኮቱን ከወንበር ላይ ያነሳና ራማ ወደገባችበት እየተመለከተ/ራማ ላጠፋሽ አልፈልግም ነበር ከዚህ በላይ ግን በመንገዴ ከገባሽ በህይወትሽ ነው የምገባው። /ወደውጭ ይወጣል/ መብራት ይጠፋል

ትዕይንት አራት

/መብራት ሲበራ ስምኦን ብቻውን ከወዲያ ወዲህ ይንጎራደዳል። ከአፍታ በኋላ አቢሰሎም ከውስጥ ይወጣል/

ስምኦን፡- እማማተኛች?

አቢሰሎም፡- መተኛቱ ቀርቶባት እንባዋን ባቆመች። እዚህ ቤት የተተከለ ሰይጣን ምን አይነት ነው? የቀድሞ የደመቀ ፍቅር፣ ሳቅርና ጨዋታ ጠፍተው ተራቸውን ለዝምታ እና ለሀዘን ለቀቀ።

ስምኦን፡- ትእግር በመረረ ሀዘን እንደታሰረች ልቧ እንደቆሰለ ዝምታዋ ይጮሀል። እስራቷን በጥሰን በቁስሏ ዘይት እንዳናፈስ ፍቃዷ አይደለም። ያለተለመደ ዝምታዋ ይጨንቃል። የፊቷ ቋጠሮ እንደ ጅራፍ የተገመደ ከነሀሴ ሰማይ ይለቅ የጨፈገገ ሆኗል። አቢሰሎም እባክህን አንድ ነገር ማድረግ አለብን።

አቢሰሎም፡- ምንድን ነው ማድረግ ያለብን ስምኦን? የትእግርን የችግር መንስኤ እና መፍትሄ ፍለጋ ያለእንቅልፍ በጭንቀት ያሳለፍናቸው ለሊቶች አይታሰቡህም? በሷ እንደዚህ መሆን ይሄው እንደምታየው እማማ ሁለት ወር ሙሉ መፈጠሯን ጠልታ በምሬት እያነባች ይሄው አይኗ ሊጠፋ ነው። የራማም ለጋ አእምሮም ተጨነቀ። እማማም ራማም እኛም የተገፈፍነውን የሰላም ካባ እንጎናፀፍ ዘንድ የትእግር መፀዳት የግድ ነው። ይሄን ለማድረግ ሁላችንም ፈጣሪያችንን በፀሎት እያማረርነው ነው። ታዲያ ከዚህ በላይ ምን ማድረግ አለብን ትላለህ ስምኦን?

ስምኦን፡- እግዚአብሔር ፈተናችንን ያበዛው እንደ እዮብ ፃድቆች ሆነን አይደለም የገዛ ሀጥያታችን ነው የሚያሳድደን። በንፁህን እጆቹ አድበልብሎ ቅዱስ እስትንፋሱን መግቦ በእለተ አርብ በአምሳሉ የፈጠረን እኛ መቅደስ የሆነው አካላችንን ብናቆሸሽ መቅደስ የሆነውን አካላችንን ብናቆሸሽ... አጥቦ ያነፃን ዘንድ በእለተ አርብ ስለኛ ሞቶ ዳግም ወለደን። በነፍሱ ነፍሳችንን አጥቦ ሀጥያታችንን በቁስሎቹ መሀል ቀብሮ በሱ ቁስል እኛ ተፈወስን። እኛም ይህን ውለታውን ዘንግተን ዘላለማዊ ህይወትን ትተን ሞትን ፍለጋ መዳከራችንን ሲመለከት... ህጉን ትተን የሀጥያት ትስታብ በወገባችን ስለታጠቅን ነው የቀጣን።

አቢሰሎም፡- ለዚህ በደላችን የሚቀጣን ምን ይሆን እንደኖህ ዘመን በፈላ ውሀ ቀቅሎን እንደ ሰዶማውያን በእሳት ከጠበሰን በኋላ እንደ ግብፃውያን በባህር ይጥለናል አሳ አንባሪው እንደ ዮናስ ማደርያ ሳይሆን መቀበርያችን ነው የሚሆነው። /ከውጭ ትእግር ትገባለች የሀዘን ስሜት ይታይባታል አልፋቸው ወደውስጥ ልትገባ ስትል

ስምኦን፡- ዛሬ ሰላምታ የለም?

ትእግር፡- ሰላም ለናንተ ይሁን።

አቢሰሎም፡- የሰላም ምኞትሽ ከልብ አይደለም። በሀዘን ባህር ጥለሽን የጭንቀት ማእበል እያንገላታን ከልብ ደርቆ እንደበት ያመነጨው ሰላምታ ባዶ ሰላምታ።

ትእግር፡- አቢሰሎም!

አቢሰሎም፡ ትእግር! ባንቺ የተነሳ የደረሰብንን አይንሽ እያየ ልቦናሽ አስተውሎታል። ከዚህ በላይ ህይወታችን ወደምን እንዲያመራ ነው የምትፈልገው

ትእግር፡- እኔ የእናንተን ህይወት አልመራውም። ጭንቀቱ አስደንግጦ ዝምታዬ እንዳስደነገጣችሁአውቃለሁ። ግን እባካችሁ የኔን ነገር ለኔ ተውት።

ስምኦን፡- እና ያየነውን እንዳላየን ሆነን ወደ ህይወትሽ ወደ አስደንጋጭ ነገር ስንትንደረደር ዝም እንበል? የዚህ ያህል ልበ ደንዳናናጨካኞች አደረግሽን እንዴ? እለተለት በአንባ መንሰቅሰቅሽ አነዳች ብርቱ ችግር ገጥሞሽ እንዲ የንስሃ እንዳልሆነ ያስታውቃል።

አቢሰሎም፡- እህቴ ሆይ እባክሽ እንደቀድሞአችን እንመካከር። የቀድሞ ሁኔታሽ ናፈቀን ሳቅና ጨዋታሽ እራበን ያደግንበት እንጂ ያለመድነው አይስማማንም።

ትእማር፡- የማልረባ ነኝ አይደል? የቤተሰቤን ፍቅር ያደፈረስኩ በሀዘን ገመድ ቋጥሬ በዝምታ ባህር የሰመጥኩ ከንቱ ነኝ አይደል?

አቢሰሎም፡- አይደለሽም።

ትእማር፡- ነኝ አወቃለው! ነኝ የቀድሞ ማንነቴ እንደተለወጠ ይገባኛል። ልቤ ቆስሎ ተቃጠለ፣ ከክብር አነስኩ፣ነፍሴ ጨቀየች፣ መፈጠሬን አምርሬ የተመኘሁትን ያህል ሞቴን በብርቱ ተመኘው።

ስምኦን፡- እንደዚህ የሚያማርር ተስፋ የሚያስቆርጥ ምን ነገር ተገኝቶ?

ትእማር፡- የልቤን ትርታ ካዳመጣችሁ አይበቃም?

አቢሰሎም፡- እባክሽን የታመመ ለመዳን መታመሙን ሳይሆን በሽታውን መናገር አለበት። ሀጥያተኛ ሰውም ለመፅደቅ ሀጥያተኛ መሆኑን ማመን ብቻ ሳይሆን ሀጥያቱን መናዘዝ የግድ ነው። ይህ ካልሆነ ግን የታመመምሀጥያተኛም አይፀደቅም።

ትእማር፡- ይህን አምናለሁ። ግን ለሁሉም ግዜ አለው። አንድ ቀን ልቤ ተከፍቶ ውርደቱን ታዩት ይሆናል። አልያም ከነውርደቴ ወደመቃብር እወርዳለው።

አቢሰሎም፡- እሺ የኛስ ይቅር ለእናታችንስ በጨዋማ ትኩስ እንባዋ ፊቷን ስትቀቅለው ከምግብ እርቃ እራሷን ስትቀጣ ትንሽ አታዝኝላትም የጇ መቀዝቀዝ ያንበደበቷ መዘጋት ሳያንሳት በአንቺ ምክንያት አይኖቿ ይጥፋ ምነው የዚህን ያህል ጨካኝ ባትሆኚ

ትእማር፡- ጭካኔዬ እናንተ የምታስቡትን ያህል አይደለም ችግሬን ብነግራችሁ ሁላችሁም ትቆስላላቹ። ያኔ ነው የእማማ አይን የሚጠፋው ያኔ ነው እራሷን በረሀብ የምትገድለው ያኔ እንዳልነበርን እንሆናለን ለዚህ ነው ዝምታዬ። የተፈረደብኝ ህመም ለኔ ብቻ እንዲሆን የምመርጠው ስለዚህ ተወኝ።

ስምኦን፡- አልተውሽም። ህመምሽ ህመማችን እንዲሆን እንፈልጋለን ስትሞቺ ዝምታን ከመረጥን ባንቺ ነፍስ እኛ ነን ተጠያቂዮቹ ስለዚህ ዝም አንልም።

/ከውጭ ራማ ትገባለች ትእማርን በስስት እየተመለከተች/

ራማ፡- እማማ አሁንም እያለቀሰች ነው እሷ ፊትስ ደስተኛ ለመሆን ብትሞክሪ ምናለ እኛስ አናሳዝንሽም ምናለ የሆንሽውን ተናግረን እፎይ ብንል ትእማር ትወጂኛለሽ? ዝም ትላታለች/ እባክሽን ዝም አትበይኝ

ትእማር፡- ምነው ብትተይኝ ራማ

አቢሰሎም፡- የጠየቀችስን መልሸለት

ትእማር፡- /ራማን አቅፋ እየዳበሰች/ እወድሻለው በጣም እወድሻለው

ራማ፡- ፈገግታሽ ራበኝ ጨዋታሽ ናፈቀኝ

ትእማር፡- ብቻዬን መሆን እፈልጋለው /አቢሰሎም እና ስምኦን ይተያዩና ስምኦን ይወጣል አቢሰሎም ወደውስጥ ይገባል/

ራማ፡- ትእማር.....

ትእማር፡- የሰለቸኝን ጥያቄ እንዳትጠይቂኝ

ራማ፡- መልስ እስከማገኝ ድረስ እጠይቅሻለው

ትእማር፡- ያንቺ ድርሻ ትምህርትሽን መማር የጎደለሽን መጠየቅ በቃ አለቀ ከዚህ በተረፈ ግን ቢነግሩሽ የማይገባሽን ነገር አትጠይቂኝ።

ራማ፡- ካስረዳሽ ለምንድን ነው የማይገባኝ ደግሞስ ስለቤተሰቤ ደህንነት አያገባኝም?

ትእማር፡- ኦ..... ኦ.... አንቺ ልጅ ነሽ

ራማ፡- ምን ....

ትእማር፡- እንደልጅነትሽ ከእኩዮችሽ ጋር ተጫወቺ ሁሉንም ነገር ልወቅ ማለት ለአንቺ ጥሩ አይደለም።

ራማ፡- አንቺም... አንቺም ልጅ ነሽ አልሽኝ? በአምኖን ያልተደሰትኩበትን ቃል ደግሜከአንቺ ሰማሁት? ለኔ የሚያስደስተኝ የእናንተን ችግር መካፈል ነው አንድም በችግራችሁ እማራለው። ነገ እኮ ታሪክ ይቀየራል። እኔም እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ ነገ ትልቅ እሆናለው ዛሬ በናንተ የህይወት ፈተና ካልተማርኩ ነገ በእንደናንተ አይነት ችግር ተጠልፌ ብወድቅ ልታዝኑ ነው እህትነት እኮ እንደዚህ አይደለም

ትእማር፡- ለምንድን ነው እኔንስ የማትረዱኝ?! ዝምታዬ ለኔ ማስታገሻ ሆኖ ሳለ ለምንድን ነው ውስጤ የሚቀጣጠለውን ረመጥ በንትርካቹ የምትቆሰቁሱት?! እባክሽ ምን አለ አንቺ እንኳ ብቸኝነት ጓደኛዬ እንዲሆን ፈቅደሽ ዝምታዬን ባታደፈርሽው።

ራማ፡- ጨነቀኝ ዛሬ ለሊት ያየሁት ህልም አስደነገጠኝ ፍራቻዬ ልቤን ሲቀሰፈው ነው ጨቅጭቄ

ትእማር፡- ራሴን እንዳዳምጥ ፍቀጂልኝ /አምኖን ከውጭ ይገባል/

ራማ፡- እኔ ግን ይሄ እጅ ስራ የሌጊዮን ሊሆን እንደሚችል ገመትኩ

ትእማር፡- ሌጊዮን የኔን ህይወት የማመስ ስልጣን የለውም። ሁላችሁም እሩቅ ታስባለቹ እኔም ከፉ ነገር ከሩቅ ይመጣል ብዬ ነበር የማስበው ሁላችንም ከህይወታችን ተዋህዶ አጠገባችን ያለውን ስለማንጠረጥር ነው በሞት ወጥመድ የምንጠመደው።

ራማ፡- የሩቁ እኮ የሚያጠቃን አጠገባችን ባለው ነው

ትእማር፡- /አምኖንን ተጠግታ/ ነው እንዴ /አምኖን ያቀረቅራል/

ራማ፡- የሩቁ ያጠፋናል ብለን እንደምንጠብቀው ስለሚያውቅ በማንጠረጥረው መንገድ ይመጣብናል ይሄ የጠላት አሰራር ነው። ሰይጣን እራሱን ሆኖ ቢመጣ ሄዋን የምትሳሳት ይመስልሻል? የአብርሀም እንግዶችስ በሰው አምሳል በመሆን እራሱን ፈንኮቶ በየማእዘኑ በመቀመጥ ያሳሳታቸው ሰይጣን መሆኑን ቢያውቁ ኖሮ አብርሀም ይራብ ነበር በጭራሽ።

አምኖን፡- ግን ለምን ሌጊዮንን ገመትሽ

ራማ፡- እማማ በምን ምክንያት እንደሆነ ባላውቃም ለሌጊዮን ያላት የመረረ ጥላቻ ፊቷ ላይ ይታየኛል ይሄን የዝምታ ባህሪዋ የመጣው ከልደት ፕሮግራሙ በኋላ ነው። ማናችሁም ግን ይሄንን ማስተዋል አልቻላችሁም። አንተንም በተሳሳተ መንገድ እየመራህ ነው ስለዚህ ተእማርንም በረቂቅ ተንኮሉ አድምቷት ሊሆን ይችላል። እኔም ችግሯን ስጠይቃት እንዳንተ ልጅ ነሽ ትለኛለች ሁል ግዜ ልጅነትን እንዳላዋቂነት ለምን እንደምትቆጥሩት ነው የማይገባኝ። እንደ ህፃናት ካልተመለሳቹ የእግዚአብሔርን መንግስት አትወርሷትም መባሉን አገትርሱ። /ወደ አምኖን ተጠግታው/ ህልም አየው።

አምኖን፡- ህልም? የምን ህልም እንደ ያእቆብ ህልም የመፍታት ፀጋ ባይኖረኝም ልስማው

ራማ፡- እኔም እንደ ዮሴፍ ህልመኛ አይደለውም። ግን አስፈሪ አስጨናቂ ህልም አየው

አምኖን፡- ምንድን ነው?

ራማ፡- የዚህ ቤት መሰረት ተሰንጥቆ በእማማ እንባ የራሰ ይመስለኛል ትእማር የሞተ ዕንስ ስትወልድ አቢሰሎም አንተን የሚያሳድድህ ይመስለኛል ስምኦን ሲጮህ ሌጊዮን ግን ይስቃል። /ሁለቱም ዝም ይሏታል/ ፍቺው ምን ይመስልሀል

አምኖን፡- አላውቅም።

ራማ፡- አንቺስ?

ትእማር፡- ይሄን ህልም ለማን ተናገረሻል?

ራማ፡- ለማንም

ትእማር፡- ለማንም እንዳትናገሪ

ራማ፡- ለምን

ትእማር፡- እኔ አስፈታልሻለው

ራማ፡- እሺ /ራማ ወደውስጥ ትገባለች/

ትእማር፡- እውነት ራማ እንዳለችው ሌጊዮን ከጀርባህ ይኖር እንዴ?

አምኖን፡- በጭራሽ

ትእማር፡- ታድያ እንደዛ በእግዚአብሔር ስም አልቅሼ እየለመንኩህ እንባዬ ደረትህን እያራሰው ስንሰቀሰቅ ያስጨከነህ ገላዬን ያስመኘህ ምን አይነት ሰይጣን ይሆን

አምኖን፡- እየተጠጋት/ ትእማር...

ትእማር፡- አትጠጋኝ

አምኖን፡- ምነው የዚህን ያህል በተጠዩኝ

ትእማር፡- ትወደኛለች ብለህ አስበህ ነበር እንዴት ምን ያለህ ጨካኝ እና ልኩ ደንዳና ብትሆን ነው ከወገብህ በታች ደረከኝ ጌታዬን ምን ብበድለው ነው በገዛ ወንድሜ ያዋረደኝ

አምኖን፡- ይሄ ውርደት አይደለም

ትእማር፡- /በጥፊ እየመታችው/ ከክብር አሳንሰህ ደሜን ማቆሸሽ ነው ውርደት ያልሆነው የድንግልና ፀጋ ማህተቤን አፍርሰህ በምንኩስና የመኖር ህልሜን ማናገፍህ ክብር ነው ጌታ ቤተ መቅደስ የሆነው ሰውነቴን ስታረክሰው ልቤ ጮኾ የስጋዬን መቆሸሽ ነፍሴ ተፀየፈችው። እንደ ህሳብህ አብሬ መኖርን መጥላት ብቻ ሳይሆን ለከፋው በደልህ እንኳን ይቅርታ ማድረግ ተሳነኝ።

አምኖን፡- የዚህን ያህል ከጠላሽን ልብሽ ቅንጣት ታህል እንኳን ለይቅርታ ቦታ ከሌለው ግደይኝ። ንፁህ ልብሽ ጥላቻን ካበቀለ የዘራሁት እኔ ነኝና ከህይወት መዝገብ ላይ ሰርዢኝ። አንቺን ማጣት ሞት በአንቺ መጠላት የሞት ሞቴ ነው ሁለት ወር ሙሉ አብሬሽ አነባው አይኖችሽ ወደውጭ እንባን ሲረጩ የኔ አይን ግን ወደውስት ደም ነበር የሚተፋው። ከራሴ በላይ እያፈቀርኩሽ ሀዘንሽን ከማይበሳት ባህር መጥልን እመርጣው። በኔ የተነሳ ቤታችን ቀዘቀዘ። ግደይኝ! ትእማር ተበቀይኝ! ድፍረቴ ሰላም ነስታሽ ልቤም ልብሽን ካላገኘ ውርደቴን በአደባባይ ገልጠሽ ነፍሴን ከስጋዬ ነጥያት።

ትእማር፡- እግዚአብሔር ያነፀውን በማፍረስ ሀጥያት አልሰራም። ጌታዬ ሀጥያቴን በስውር ይዞ ያንተን ሀጥያት በአደባባይ እንድገልፅ አልተፈቀደልኝም። ለዚህ ነው ዝምታዬ ቤተሰቤን ያስጨነቀው ያንተን ነውር ላለመግለጥ ስል እናቴ እንኳን በለቅሶ አይኗ ሊጠፋ ነው። ምናልባት እውነታውን ሲያውቁ ሁሉም ይጠፋይሆናል። ይሄ ሲገባኝ የበለጠ በእንባ ሸለቆ ውስጥ እዘፈቃለው። የኔም እንባ እንደራሄል ከፀባኦቶ ደርሳ ከዙፋኑ ፊት ከጮኸች ያንግዜ እግዚአብሔር ሀጥያትህን ገልጦ በአደባባይ ይበቀልህ ይሆናል። ጌታ ለራማ እውነታውን በህልሟ ነግሯታል። የሴትነት ደንቤ ቀርቶ የበላሁት አልስማማ ሲለኝ ማህፀኔን አንዳች ነገር ሲቀዘቅዘው ታወቀኝ። ምናልባትም ራማ እንዳለችው በድን ፅንስ ይሆን እንዴ በማህፀኔ ቁና የሰፈርኩት

አምኖን፡- /ደንግጦ/ ምን

ትእግር፡- አርገዋለው። ለዚህ በሀጥያት ተፀንሶ ለሰው ልጅ ምቹ ወዳልሆነው ሀጥያታዊ አለም ለሚንደረደረው ጨቅላ አንተ ምኑ ነህ? አባቱ ወይንስ አጎቱ? እኔስ እናቱ ወይንስ አክስቱ? ይህንን መአት ሲሰሙ ምን የሚሉ ይመስልሃል? አቢሰሎም ጨርቁን ጥሎ ያብዳል፣ የስምኦን አንገት በአንተ ሀፍረት ይደፋል። እማማም ዋጋ የልትም፣ ራማ የገዛ ወንድሟ ታማኝ ያልሆነ ማንን የምታምን ይመስልሀል? ማንንም። አቤቱ እኔ ባርያህን ተመልከት ለሶሎሞን ጥበብን እንደሰጠህ በማይመረመር ጥበብህ ከሚዳስስ ሀጥያት ከሚታይ በደል ፈልቀቀህ አውጣኝ።

አምኖን፡- ትእግር…

ትእግር፡ እንዳትጠጋኝ እንዳትጠጋኝ። /ትታው ትወጣለች አምኖነ ግራ ይጋባል ከአፍታ በኋላ ሌጊዮን ይገባል/

ሌጊዮን፡- ትእኖር እንደቀሰት ስትወረወር አየዋት። ዛሬም ተጋጫቹ

አምኖን፡- ካራስ ፀጉሬ እስከ እግር ጥፍሬ በፍርሀት ተመታው። ልቤ ልትወጣ አፌ ጋር ደርሳተመለሰች።

ሌጊዮን፡- ታድያ አጥበህ መልሰህ እንድትከተው ተፍተህ አታወጣም ነበር

አምኖን፡- ቢቻልማ ቅድሚያ የትእግርን የልብ ቁስል አጥቤ ነበር የማፀዳላት።

ሌጊዮን፡- አይቻልማ

አምኖር፡ እኮ አለመቻሉ አይደል ህሊናዬን በፀፀት ያነደደው

ሌጊዮን፡- አምነህ ላደረከው ነገር መፀፀት አያስፈልግም። የጀመርከው መንገድ የሚያደርስ እንጂ የሚመልስ አይደለም።

አምኖን፡- በዚህ መልኩ ማፈቀሬን ልገልፅላት አይገባም ነበር።

ሌጊዮን፡- ከዚህ ሌላ አማራጭ አልነበረህም። በቃል ብትነግራት አውግዛ ተሸሽህ ነበር። ያኔ አሁን ተጎዳሁት ከምትለው በላይ ነበር የምትቆሰለው። ይሄ ድርጊትህ ግን ከቃል በላይ ማፍቀርህን ያረጋግጥላታል። ደግሞ መንገዶች አልጋ በአልጋ እንደማሆኑ እና ዋጋ ሊያስከፍልህ እንደሚችል የነገርኩህን አትርሳ። እስከ መጨረሻው ከጎንህ ነኝ። /ከካፖርት ኪሱ ውስጥ የመጠጥ ብልቃጥ አውጥቶ/ እንካ ጠጣ

አምኖን፡- ይቅርብኝ

ሌጊዮን፡- ግድ የለህም ጠጣ ሺ አመት ለማትኖረው ህይወትመጨናነቅ። በል እንካ ያዝ ጭንቀተህን ከነ ኮሮጆ ድራሽ አባቱን ነው የሚያጠፋልህ። ትእግር ጋር እንድትደርስ ድፍረት የሰጠህ ይህ መሆኑን አትርሳ ይልቁንስ አንተን እያለ ደጅ የጠናውን

ባለውለታህን አጣጥመው። /አምኖን ይቀበልና የጎኑጫል/ የመሬቱን ኪራይ የዚህን ወር ተቀብያለሁ። የሚያስደስተው ጉዳዩ በሚስጥር መሄዱ ብቻ ሳይሆን ወደ ፊትም ቤተሰቦችህ ስለመሬቱ ተቆርጦ መከራየት የማያውቁ መሆናቸው ነው። /ከኪሱ በርከት ያለ ገንዘብ አውጥቶ ጠረጴዛ ላይ ያስቀመጠና/ ከባለ አስገባሪው የመሬቱን ኪራይ ልቀበለው ስሄድ ሰለገጠመህ ችገር በዝርዝር አውርቼው ነበር ከኔ ጋር ይምጣና ይመካከር አሉኝ። /አምኖን ዝም ይላል/ አይዞህ እሳቸው ጋር ሄድክ ማለት እኮ እያስገዱ ለሚያስገብሩለት ጣኦት ተንበረከክ ማለት አይደለም። ደግሞ ደንበኞቻቸው እንጂ እሳቸውስ ክርስቲን ናቸው። በተለይማ ለገብርኤል ልዩ ፍቅረ ነው ያላቸው ምን ልልህ ፈልጌ ነው ሰውዬው በእድሜ የገፉ እና የበሰሉ ስለሆኑ በቂ ምክር ታገኝበሀ። እሀት ማፍቀር በአንተ እንዳልተጀመረ ሁሉ ምክር ለመጠየቅም የመጀመርያው ሰው አይደለህም። ስምኝ በየዘርፉ ታዋዊ የሆኑ ሰዎች እና ሀገርን የመምራት ሀላፊነት ያለባቸው ቱባ ባለስልጣናት ምክረ ካህን የሚሹ ይመስልሀል ሁሉም እኚህ አዋቂ ጋር ነው የቁራ ላባ በመያዝ በለሊተ የሚገርፉት። አንተ ደግሞ እድለኛ ነህ ሰውዬው መሬትህን በመከራየት በአካለ ስጋ ቀርበውሀል ይሄን አጋጣሚ ተመኝቶ ያላገኘ ስንት እድለቢስ ሰው እንዳለ ቤት ይቁጠረው። እየጠጣህ

አምኖን፥- ታዲያ ካፌ ወይም እታችኛው ግሮሰሪ ቅጠራቸዋ

ሌጊዮን፥- ምንልክ እስቲ ድገመው ስማ ይሄ ማት እኮ የሰውዬውን ክብር ማቃለል ነው መስቀል አልጨበጡም እንጂ ካህን ልትላቸው ትችላለህ። ደግሞ ቀድሞ አሉ የተባሉ መሪጌታ ነበሩ።

አምኖን፥- ለነበርማ ሳጥናኤልም መልአክ ያስቆሮቱ ይሁዳም ደቀ መዝሙር ነበር።

ሌጊዮን፥- ደስ ካለህ መተው ትችላለህ ላንተ ይሆናል ይጠቅማል ብዬ የነገርኩህ ረብ የለሽ መስሎ ከታየህ መተው ትችላለህ ከእንግዲህ በአንተ ህይወት ውስት ጣልቃ አልገባም።

አምኖ፥- እንደዛ ለማለት ፈልጌ እኮ አይደለም

ሌጊዮን፥- በቃ

አምኖን፥- ሌጊዮን

ሌጊዮን፥- ጠጣው

አምኖን፥- /አምኖን በአንድ ትንፋሽ መጠጡን ያጋምሰውና/ በቃኝ

ሌጊዮን፥- /ይቀበለውና/ ለሌላ ግዜ ይሆንሀል ቁልፍህን ስጠኝ መሳብያ ውስጥ ላስቀምጥልህ። /አምኖን ከኪሱ ቁልፍ አውጥቶ ይሰጠዋል ሌጊዮን መሳብያወን ከፍቶ እያስቀጣል/ ለወደፊቱ የዚህን ያህል በአንድ ትንፋሽ አይፀለጥም አስራ አምስት ቀናት ሙሉ በከተማ አለማምጄህ እንደጀማሪ ሆንክብኝ እኮ /ብሩን ከጠረጴዛ ላይ አንስቶ መሳብያ ውስጥ እየከተተ/ ብሩም እዘህ ይቀመጥልህ። እህ… ለመሄድ አልተስማማህም

አምኖን፥- ምንም ነገር ቢሆን ትእማርን ከማጣት የሚብስ ነገር የለም ባይሆን አብረከኝ ትሄድ

ሌጊዮን፡- እኔማ ስራዬን ጨርስኩ /አምኖን ሊወጣ ሲል/ ቆይ ቆይ እንዲሁ ዘው ተብሎ ከመቅደሳቸው አይገባም። ለክብራቸው መገለጫ እጅ መንሻ ያስፈልጋል። ምክራቸውን ስትሻ ደንብና ስርዓታቸውን እያከበርክ መሆን አለበት።

አምኖን፡- በሰንበት ተማሪያቸው ነበርክ እንዴ?

ሌጊዮን፡- ባልሆንም ቀኖና ዶግማቸውን አውቃለው። አንተም አንድ ሁለት ቀን እሳቸው ጋር ብትቆይ የበለጠ ትጠቀማለህ ለነስምኦን እንደላማድህ ገዳም ነኝ ብለህ ደውልላቸው /አምኖን ይወጣል/ በጣም። ጥሩ ለአራተኛው ምእራፍ ተንደረደረ ማለት ነው። የቀጣዩ ምእራፍ ዋና ተዋናይ ይቺ ቁልፍ ትሆናለች። ይሄ ነው ሌጊዮን ማለት ማንም እኔን ደግሮ ማቆም አይቻለውም /ከውጭ ከበደ እየተገላመጠ ይገባል/ እንዴት ነው።

ከበደ፡- እንደደነበረ በቅሎ ነው አካሄዱ

ሌጊዮን፡- /ወደውስጠኛው ክፍል እየተመለከተ/ አቤሴሎም አልወጣም ውስጥ እንዳለ ነው። ሁሉን ነገር እንደነገርኩህ። ደግሞ የሚረዳን ተጨማሪ ነገር አግኝቿለሁ።

ከበደ፡- ምን

ሌጊዮን፡- /ቁልፍ ያሳየውና ከካፖርት ኪስ ውስጥ የሆነ ነገር አውጠቶ መሳብያ ውስጥ ይከትና መሳቢያውን ሳይዘጋ ገርበብ አድርጎ ቁልፉን አንጠልጥሎ ይተወዋል።

ከበደ፡- ከውስጥ ሰው እየመጣ ነው መሰለኝ ድምፅ ይሰማኛል

ሌጊዮን፡ ፈጠን በል እንውጣ /ሁለቱም በፍጥነት ወደውጭ አቢሰሎም ከውስጥ ይወጣል ከምግብ ጠረጴዛው ላይ ቡርቱካን አንስቶ በቢላዋ ይቆርጥና ተመልሶ ወደ ውስጥ ሊገባ ሲል የተከፈተውን የአምኖንን መሳቢያ ይመለከትና/

አቢሰሎም፡- /ድምፁን ከፍ አድርጎ/ አምኖን መተሀል እንዴ /ወደ ውስጥ ሊገባ ሲል መሳቢያ ውስጡን ይመለከታል ብር ኮንዶም እና ሲጋራ አውጥቶ ይመለከታል ግራ መጋባት ስሜት/ ወደውጭ በር ተጠግቶ/ /እምኖን… አምኖን /ከውጭ ከበደ ይገባል

ከበደ፡- እንደምን ዋላቹ /አቢሰሎም የያዘውን ያይና ደንገጥ ብሎ/ ሰአሊነ ቅድስት ጌታዬ እርሶም እንደዚህ ያለ አፀያፊ ነገር ይፀዛሉ እንዴ?

አቢሰሎም፡- የ… የኔ አይደለም /መሳቢያ ውስጥ ከቶ ይቆልፈዋል/ አ…. አዎን

ከበደ፡- አ….. አወቁኝ

አቢሰሎም፡- መልክህ አዲስ አልሆነብኝም

ከበደ፡- የአምኖንን መሬት ለማስተዳደር የዛሬ ሁለት ወር ገደማ የተቀጠርኩ ነኝ።

አቢሰሎም፡- አዎ አሁን አወኩህ።

ከበደ፡ ፈልጌዎት ነበር?

አቢሰሎም፡ እኔን?

ከበደ፡ ከህፃኗ ልጅ በስተቀር ቤት ውስጥ ያለ ማንንም ሰው

አቢሰሎም፡- ምን ነበር

ከበደ፡ ጌታዬበዛ ቦታ ከተቀጠረኩበት ቀን ጀምሮ በህሊናዬ እየተመላለሰ የሚያስጨንቀኝ አንድ ጥያቄ አለ አምኖንን ለመጠየቅ ባስብ ብቻውን ላገኘው አልቻልኩም ቢጨንቀኝ እቤት ድረስ መጣው፡፡

አቢሰሎም፡- ጉዳይህስ?

ከበደ፡- ምናልባት በንግግሬ መሀል የማትወደውን ቃል ብናገር ባለማወቄ ሊሆን ይቻላልና ቅድሚያ ይቅርታ እየጠየኩ ታቦት እና ጣኦት ባንድላይ ይሄዳል ባለህ ታስባለህ?

አቢሰሎም፡- በጭራሽ፡፡ በክርስቶስ ክርስቲያን የሆነ ሰው ታቦትን በልቡ አትሞ ጣኦትን ግን ከእግር በታች እየረገጠ ይሰባብራል፡፡

ከበደ፡- ታዲያ ይህንን እያመናችሁ ነው እንዴ መሬቱን ቆርጣችሁ ለባለ ጣኦቱ ቤት ማሰሪያ ያከራያችሁት?

አቢሰሎም፡- አቤት!

ከበደ፡- እዛ የሚያህል አዳርሽ ውስጥ ሰው ሁሉ ከሩቁ እየመጣ ለዛ ለቆመው ጣኦት እየሰገደ የንብረታቸውን አስር በመቶ ይገብራል፡፡ አምኖንም ከቤት ክርስቲያን መልስ አይን እያለው ለማያይ፣ ጆሮ እያለው ለማይሰማ፣ አፍ እያለው ለማይናገር ጣኦት ተንበርክኮ ሳየው ሁሌም ጥያቄ ይፈጥርብኛል፡፡ ስለዚህ ቤተሰብ እንደሰማሁት ከሆነ ቤተክርስቲያን የምታሳንፁ፣ የምታሳድሱ፣ የተቸገረን እንደምትረዱ ነው፡፡ አሁን ግን ምዕመኑ ይህንን ሲሰማ ማጉረምረም ጀመረ ወንድሜ ሆይ እግዚአብሔርን እኮ ማጭበርበር አይቻልም ከማይመስላቹ ጋር አትተባበሩ ለጣኦት የታረደ ደም ለሚለው አምላካዊ ቃል አፀፋው ምላሹ ይህ ሆነ በአንድ እጃቹ ለታቦትም ለጣኦትም መባ ትሰዋላቹ ሞቃት ወይም በራዳ ስላልሆናቹ ልትተፉ ነው እርስ ለብ ያለ አይስማማውም

አቢሰሎም፡- /ንዴት በተቀላቀለበት ቁጣ/ በቃህ..... ውጣልኝ፡፡ /አቢሰሎም ጭንቅላቱን ይዞ ይቀመጣል፡፡ ተነስቶ ይንቆራጠጣል/ ወይኔ አቢሰሎም ይሄ ነው መዋረድ ይሄ ነው ከክብር ዝቅ ዝቅ ማለት ለካንስ ትእማር እውነታው ላይ ደርሳ ነው እንዳትናገር በድግምት እንደበቷን የቆለፈው አቤት መአት አቤት ኩነኔ እግዚኦ ሀጥያት /ከውጭ ሌጊዮን በፍጥነት ይገባል የንዴት ስሜት ይታይበታል/

ሌጊዮን፡- ይቅርታወንድሜ አንዴ ብቻችንን ትተወን /ከበደ ይወጣል/ ስማኝ አቢሰሎም እዚህ ቤት ምን አይነት ቅሌት እና ምንፍቅና እየተካሄደ እንደሆነ ከአንተ መስማት እፈላጋለው... ንገረኝ ለምንድን ነው ዝም የምትለኝ

አቢሰሎም፡- ምን ላድርግ ሌጊዮን እዚህ ቤት እንደዚህ አይነት ነገር የፈፀማል ብዬ እንዴት ላስብ?

ሌጊዮን፡- እሺ ትእማር ተገዳ መደፈሯንስ ለምን ነው ያልነገርከኝ?

አቢሰሎም፡- /ደንግጦ/ ምን

ሌጊዮን፡- ይሄንንም ሽምጥጠኛ መቼም ስምኦን የሚያውቀውን አላውቅም ብትለኝ ጓደኝነቴን ከልብህ ላይ ፍቀህ እንደካድከኝ ነው የምቆጥረው

አቢሰሎም፡- የጌታዬ ደም በፈሰሰበት በክብር መስቀሉ እምልልሀለሁ ስለምትለው ነገር አንዳችም እንኳ የማውቀው ነገር የለም።

ሌጊዮን፡- ስምኦን እንዴት አልነገረህም ከምትወደው ከናቱ ልጅ ካንተ ደብቆ የዚህን ቤት ሚስጥር ዛሬ ጠዋት ላወቀው ሰው ያዘረከርካል ማለት የማይታመን ነው።

አቢሰሎም፡- እባክህ ነፍሴን አታስጨንቃት ማነው ትእማርን ደፍሮ ንፁዋ እህቴን ያቆሸሻት?! ማነው ህይወቷን አጨልሞ ቤታችንን ጭንቀት በወለደው ዝምታ ያመሰው?! ማነው ያይኔን ማረፊያን ያሳዘናት?! ንገረኝ የእንባዋን ከረጢት ሸንቁሮ እንባህ በደረቅ መሬት እንዲፈስ የፈረደባት ማን ነው?! በዝምታዋ ውስጥ የታፈነ ሪታ እነዳለ ይሰማኛል። ተኩሳቴ እያቃጠለኝ አንዳች ነገር ጭንቅላቴን ሲወጋው ተሰማኝ እባክህ እራሴን ከመሳቴ በፊት ንገረኝ

ሌጊዮን፡- የስምኦን ጓደኛ ሲነግረኝ ለማንም እንዳልናገር አስምሎኝ ቢሆንም እንደዚህ መሆንህን እያየሁ ግን ዝም አልልም። አቢ ይህን ሚስጥር ከኔ እንደሰማህ ለስምኦን ላትነግረው ቃል ግባልኝ

አቢሰሎም፡- እንደቃልህ ይሁን።

ሌጊዮን፡- ትእማር ያለፍላጎቷ ደፍሮ ከክብር በታች ያደረጋት የገዛ ወንድማችሁ አምኖን ነው

አቢሰሎም፡- ም.... ምን... አምኖን

ሌጊዮን፡-እኔም ስሰማ እንዳንተ አላመንኩም ነበር ሁሉንም ነገር በደንብ አብራርተው የገለጡልኝ ከተረጋጋው በኋላ ነው እየሄደ በሚሰግድለት በባለ ጣኦቱ ሰውዬ ምክር ተገፋፍቶ የገዛ እህቱን ስጋዋን ቆርሶ ደሟን አፈሰሰው። /አቢሰሎም ይንቀጠቀጣል/ እዛ ጣኦት ቤት እንደሚገኝ ሲነግሩኝ እንዴት ሰበር በደመ ነፍስ እንደሄድኩ አላውቅም ነበር። አጅሬ ሆየየ እንዳገር ሙሉ ጫቱን በጉንጨ ወጥሮ ትንባሆውን እያቦነነ ከአዘማውያን ሴት ጋር በመሆን ለጣኦቱ ሲንበረከክ ተመለከትኩት ማጅራቱን አንጠልጥዬ ላወጣው ስል ዘቦቹ ማጅራቴን ይዘው እንደ ጅራፍ እያወናጨፉ ወደውጭ ወረወሩኝ። /አቢሰሎም ይንቀጠቀጣል ራማ ከውስጥ ትወጣለች አቢሰሎምን ስታየው ትደናገጣለች ለመውደቅ ሲንገዳገድ በፍጥነት ትደገፈዋለች።

ራማ፡- ምንድን ነው እየሆነ ያለው ነገር አቢሰሎም ... አቢ.... ወይኔ ጉዴ ፈላ ደግሞ አንተንስ ምን አደረገህ

ሌጊዮን፡- /በጎንታ/ ስድስተኛው ምዕራፍ /አቢሰሎም መሬት ላይ ይወድቃል ራማ ትጮሀለች

መብራት ይጠፋል

ትዕይንት አምስት

መብራት ሲበራ እናት ተቀምጠዋል ሌጊዮን ከእናት ፊንጠር ብሎ ቆሞ ይመለከታቸዋል ከካፖርት ከኪሱ ውስጥ አውጥቶ ይጎነጫል/

ሌጊዮን፡ አሳዳጊዎቼ የነገሩኝ በችግር ምክንያት የምትልሺው የምትቀምሺው አተሽ እንደጣልሽኝ ነበር እየተረኩ ያሳደጉኝ። እነሱ ሃሳባቸው ወደሽ ስላልጣልሺኝ በአንቺ ላይ ጥላቻ እንዳይኖረኝ ነው። ይሄ የነሱ ሀሳብ ነው። እኔ ግን ከመጣል ውጪ ብዙ አማራጭ እንዳለሽ ነው የሚገባኝ። መጀመሪያውኑ ያለ አቅምሽ አለመውለድ፤ ሁለተኛ ሰርተሽ የማሳደግ አቅም ባይኖርሽ እንኳን ለመፅዋት እጅ ይዘረጋል ልጅን ያህል ያስጣለሽ ደንዳና ልብ ለመፀዋት እጅ ይዘረጋል ሀፍረት ይሰማዋል ማለት ዘበት ነው። ቢሆንም እንኳን ላሳዳጊ መስጠት ትችይ ነበር። /በረጅሙ ይተነፍስና ከመጠጡ ተጎንጭቶ/ አሳዳጊዮቼ እንደነገሩኝ እድሜዬ አምስት እስከሚሞላኝ እየመጣሽ ትጠይቂኝ ነበር ከዛ በኋላ ነፍስ ስለማውቅ እንዳልሞግትሽ ነው መሰል ጠፋሽ እነሱም አንቺን በአድራሻሽ ከመፈለግ ይልቅ እኔን ዝም ብለው ማሳደግ መረጡ። ልክ ናቸው ሳትፈልጊኝ ስለጣልሽኝ ለምን ይፈልጉሻል ደግሞም አንቺ እነሱ ጋር እንጂ እነርሱ አንቺ ጋር ጉዳይ የላቸውም። ከልጅነቴ ጀምሮ እንደጠላሁሽ ነው ያደኩት። ሀሳቤ አድጌ ሳገኝሽ ለምን እንደጣልሽኝ ሳይን ለምን እንደተፋሽኝ ለመጠየቅ እመኝ ነበር። አድራሻሽን ተቀብያቸው ሳነፈንፍ በልጆች ተከበሽ በሀብት ውስጥ ተቀብረሽ ተገናኘን። ይህን ስመለከት የጠፋሽበት ምክንያት ባለፀጋ ስለሆንሽ እንደሆነ ገባኝ። ሀብታም የድህነት ህይወቱን አያስታውስ ከመኖር ይልቅ በሀብት ውስት መሞትን ይመርጣል። ለዚህ ነው በድህነት ውስት ያፈራሽብኝ እኔን የረሳሽኝ። ይህ ሲገባኝ ላንቺ ያለኝ ጥላቻ ከብረት ጠነከረ። የበቀል ስሜቴም በእቶን እንደተመታ አለት በልቤ ላይ ቀለጠ።ቤተሰቦችሽን በትኜ ሀብትሽን የምነጥቅበት ጊዜ ደርሷል። /እናት ያለቅሳሉ ከመጠጡ ተጎንጭቶ/ ትእማር በአምኖን ተደፍራ ስትፀንስ ለሱ ያላት ጥላቻ ከገሀነም የጠለቀ ነው። ይህን የሰማው አቢሰሎም ንዴቱ ከቁጥጥሩ ውጭ ሆኗል። መሬቱ ለባለ ጣኦት መከራየቱን የሰማው የሀገሩ ህዝብ

ባአድ አምላኪ አድርጎ ነው የቀጠሯችሁ። ይህን የሰማው አቢሰሎም በንዴት አይምሮውን ሊናፍጠው ነው። እሱ እና ትእማር ስምኦንን ወረኛ በመሆኑ አምርረው ነው የጠሉት። ይህንን መመልከት ደግሞ ለራማ ጥልቅ ቅጣት ነው። ታድያ ይሄ ቤተሰብ ከሳምንት የዘለለ ዓድሜ የሚኖረው ይመሽልሻል? ያንቺም የህይወት ምዕራፍ መዝጊያ የዚህን ያህል የፈጠነ ነው። ዳግመኛ ባዶ ቤት ካገኘውሽ ግን እገልሻለሁ። ይህንን እንዳትረሺ /ራማ ከውጭ ትገባለች የእናቷን እንባ ታብሰና/

ራማ፡- እማ አታልቅሺ። እንደዚህ አልነበርንም እና ወደቀድሟችን እንመለሳለን። እግዚአብሔርን አምኖ ማን ከሜዳ የቀረ አለ ማንም አዳም የቀድሞ ክብሩ ተመልሶለት ምድርም ዳግም በሰው ሞላች ነገደ ያእቆብም ከነአን ተመለሱ እኛም ያጣነውን ፍቅር እና ሰላም በእጥፍ እንደምናገኘው እመኚ /ሌጊዮን መጠቱን ሲጎነጭ/ እዚህ ቤት ማንም አስካሪ መጠጥ አያውቅም

ሌጊዮን፡- እኔ ጠጣዋ። ደግሞ ይሄ ቤት እንጂ ቤተ መቅደስ አይደለም ታቦት ሳይሆን እንደ አምኖን አይነት ርካሽ ሰው ያደረበት።

ራማ፡- አምኖንን ያረከሰከው አንተ ነህ። ከቤተክርስቲያን እቅፍ ነጥለህ በሀጢያት አለም ውስጥ በዝሙት እና በርካሽ ነገሮች አጥነህ ያረከሰከው አንተ ነህ። ይህን ልትክድ ትፈልጋለህ

ሌጊዮን፡- እናስ ምን ይሁን?

ራማ፡- የወፍጮ ድንጋይ ባንገትህ ታስሮ ወደ ጥልቁ ልትወረወር እንደምትችል አላስተዋልከውም

ሌጊዮን፡- /በረጅሙ ይስቅና/ እኮ ለፃድቅ ሰው መሰናክል በመሆኔ እኔ የምለው ግን አንቺ ነሽ እንዴ ፈራጅ ወይንስ በእስራኤል ላይ እንዲፈርዱ 12 የስልጣን ወንበር የተሰጣቸው ሀዋሪያት አንቺን ንግስት አድርገው በ 13 ኛ ዙፋን ላይ አስቀመጡሽ ፈራጅ ከሀጥያተኛ ተወልደሽ ሀጥያተኛ የሆንሽው አንቺ ሳትሆኚ ቅድመ አለም ከአብ ያለ እናት ድህረ አለም ከማርያም ያለ አባት በድንግልና ተፀንሶ በድንግልና የተወለደው ነው ፈራጅ

ራማ፡- ይህን ያመነ እርሱ የማይወደውን አይሰራም። ሌጊዮን እዚህ ቤት የተከልከው ፍሬ በእሾህ መካከል እንደተዘራ ስንዴ ነው በእርግጥ ያድጋል ግን ቡቃያውን እሾሁ አንቆ እንደሚገለው እዚህ ቤት የዘራከው ጥላሸት በፍቅር ይታነቃል

ሌጊዮን፡- /ይስቃል/ ወይራ እኮ ከሚታየው ግንዱ ቀድሞ የማይታየው ስሩ ነው የሚያድገው አሁን በብርቱ ስለጨለመ በተጠቀጠቀ ጫካ መሀከል የበቀለን ወይራ ፈልጎ መንቀል የማይታሰብ ነው

ራማ፡- ፀሀይዋ እኮ እንደጠለቀች አትቀርም ደግሞ ሊነጋ ሲል እንደሚጨልም አትርሳ

ሌጊዮን፡- እ..እ ይሄ አባባል ነው። ተረትን ስለምታስቀድሙ ነው በህይወት የተቀደማችሁት። ቢዘገይም የምመክርሽ ተረትን ሳይሆን ህይወትን እንድትኖሪ ነው። /ከውጭ ትእማር በንዴት ስሜት ትገባለች/

ሌጊዮን፡- ምነው ትእማር?

ትእማር፡- አልቻልኩም። ህይወቴ በእሳት የተሞላ ሆነ

ሌጊዮን፡ አይዞሽ በቃ

ትእማር፡- ከእንግዲህ ሁሉም ነገር አበቃለት። የሰላም መስኮቶች ላይከፈቱ የተከረቸሙ

ሌጊዮን፡- ክርስቲያን ተስፋ አይቆርጥም ተይኝ አልነበር?

ትእማር፡- ተስፋ አጣሁ ነገሮች የበለጠ ጨለሙ ሁሉም ሰው እኛን እንደ ጣኦት አምላኪ ቆጠሩን። የሰይጣን ታማኝ አገልጋይ መሆናቸውን ለማስመስከር ከወንድሟ ፀሰች እየተባለ ተወራ ፈቅጄ እንዳደረኩት ነው ሁሉም ያመነበት እሺ ያመነበት እሺ ለዚህ ሁሉ መአት ተጠያቂ ማነው

ሌጊዮን፡- ስምኦን

ራማ፡- በጭራሽ

ሌጊዮን፡- ራሱ ስምኦን። ትእማር በአምኖን መደፈሯን እና የጣኦት ቤት ማስገንባቱን ለአደባባይ መንዛት ነበረበት አቢሴሎምን አንድም ይሄ አይደል ጭንቀቱን ያነደደው ሁሉም ነገር አብቅቶ የመፍትሄ ገመዶች እንደ ድር ከተበጠሱ በኋላ እንደታላቅ የምስራች ላቢሰሊም ነገረው

ትእማር፡- ለአቤሴሎም እሱ ነው የነገረው?

ሌጊዮን፡- ታድያ እኔን ያነደደኝ ምን ሆነና

ትእማር፡- እሱ ከየት ሰምቶ

ሌጊዮን፡- ምናልባት አምኖን ሀጥያቱን ተናዞለት ይሆናል። እኔን እኮ በግን ያደረገኝ ካቢሰሎም ይቀልቅ ለኔ አለመንገሩ ነው። ይህ ቢሆን ኖሮ በትኩሱ መፍትሄ እናበጅለት ነበር። ሌላው ቢቀር አንቺን እንኳ ስለ እውነታው አልጠይቅሽም ኦ..! ስምኦን በህይወቱ ትልቅ እና ይቅርታ የማይደረግለት ስህተት ነው የሰራው

ትእማር፡- ስምኦን... ስምኦን... ኦ አምላኬ አምኖን ያቆሰለውን ልቤን እንዳይጠገን አድርጎ ነው እንጨት የሰደደበት

ራማ፡- እንደዚህ አይነት ነውር ስምኦን አይሰራም። በጆሮሽ ያልሰማሽውን መሰረተ ቢስ የሌጊዮን ወሬ ሰምተሽ አትፍረጂ። ከመኮነንሽ በፊት እውነት ስለመሆኑ እርሱን መጠየቅ አይሻልም እመኚኝ ስምኦን እንደዚህ አይነት ሰው እንዳልሆነ ከኔ በላይ ምስክር ትሆኚለሽ፡

ትእማር፡- አምኖንስ እንደዚህ የሰይጣን ደቀ መዝሙር ስላለመሆኑ ምስክር ትሆኚዋለሽ ሁለቱም ከሚዛን ቀለሉብኝ

ራማ፡- ትእማር...

ትእማር፡- /በቁጣ/ በቃሽ አትጨቅጭቂኝ

ራማ፡- እጨቀጭቅሻለው ለምንድን ነው እውነትን ፍለጋ የማትደክሚው

ሌጊዮን፡- ራማ የዚህ ቤት እውነት እኮ የትእማር የእድሜ ልክ ሀዘን፣ የአምኖን አፀያፊ ከክህደተ እና የስምኦን ወሬኛነተ ነው።

ራማ፡- ይሄ አይደለም ዚህ ቤት እውነት

ሌጊዮን፡- እያየነው እየሰማነው ይህ ካልሆነ የዚህን ቤተ እውነተ ከየት ነው የምታመጪው

ራማ፡- ከአንተ መዳፍ ውስጥ ፈልቅቄ ነው የማወጣው። ያን ግዜ የአንተ እውነት ይገለጣል /ከውጭ ስምኦን ይገባል/

ስምኦን፡- / እናቱን ይስምና/ ትእማር እንዴት ነሽ

ትእማር፡- /በጥሪ ትመታዋለች ሁሉም ይደነግጣሉ/ ስሜን አትጥራ አንተ ወረኛ

ስምኦን፡- ምን ሆነሻል

ትእማር፡- ዝም በል። ለዚህ ቤት ያለህ ክብር ያቺን ታህል ነበር እንዴ ምን ጥቅም ብታገኝ ነው የዚህን ቤት ሚስጠር ለንፋስ አሳልፈህ የሰጠከው

ስምኦን፡- /እየተጠጋት/ እኔ…?

ትእማር፡- እንዳትጠጋኝ በቁስሌ የሰደድከውን እንጨት ልትነቀንቀው ነው?

ስምኦን፡- እባክሽን አድምቺኝ

ትእማር፡- ድምፅን መስማት አይንህን ማየት አልፈልግም

ስምኦን፡- ምንድን ነው ነገሩ የጎረስኩበት እጅ ለጥፊ የተነሳበት ምክንያት አልገባኝም ሌጊዮን እ… እማ ምንድነው የተፈጠረው? /እጇን ይዞ/ ስለተፈጠረው ነገር ምንም አላውቅም

ትእማር፡- /አመናጭቃ ታስለቅቀውና ደግማ በጥፊ እየመታችው/ ከሀዲ!

ስምኦን፡- ትእማር ታላቅሽ መሆኔን አትርሽ

ትእማር፡- ድርጊትህን ግን ማንም ታናሽ አይሰራውም /ከውጭ አቢሰሎም በንዴት ስሜት ይገባል/

ስምኦን፡- /እየተጠጋው/ አቢሰሎም

አቢሰሎም፡- /በጥፊ እየመታው/ አትጠጋኝ አንተ ከሀዲ!

አቢሰሎም፡- አንተ ዝርክርክ ድመት እንኳ ነሯን ትደብቃለች ለካንስ ከእንስሳ ያነሰ ልብ ነው ያለህ።

ስምኦን፦ እዚህ ቤት ምን አይነት ሰይጣን ነው የገባው እናቴ ምንድን ነው ነገሩ ጉንጩን በመዳፋቸው የታረሰበት ምክንያት ጥፋቴ ምን ቢሆን ነው ወይንስ በአምኖን ስህተት እኔ ነኝ የምቀጣው?

አቢሰሎም፦ ሁሉም ነገር ተበላሸ

ራማ፦ አልተበላሸም

አቢሰሎም፦ አንቺ ልጅ ነሽ ዝም በይ

ራማ፦ አቢ አንተም... አንተም እኔን ለመስማት ፍቃድህ አይደለም?

ሌጊዮን፦ ምነው ራማ ተጨማሪ ብልሽት ባትሆኚበት

አቢሰሎም፦ ጣኦት አምላኪ ናቸው ተብሎ ውስጥ ውስጡን ይወራ የነበረው አሁን ፈንድቶ ይፋዊ ሆኗል። ለየ አብያተ ክርስቲያናቱ የሰጠነው አስራት ከጣኦት ግብር የተረፈ ነው ብለው መለሱት። ከየ መንገዱ የሰበሰብናቸው ነዳያን ከጣኦት ቤት የመጣ እርዳታ ባፍንጫችን በማለት የሰጠናቸውን ቤት ንብረት ትተው ተበተኑ። በየ አብያተ ክርስቲያኑ መቅደስ የሰቀልናቸው መጋረጃ ወረዱ። ማይፈዱ ከታቦቱ ላይ ተገፈፈ።ለካህናት እና ለሰባኪያን ያሰፋናቸው መጎናፀፊያዎች ወለቁ።የቤተክርስቲያኒቱ የስስት ልጆች ስጦታችሁን ለብሰን ታቦተህጉን አናጅብም አሉ። ለፆም ማስፈለጊያ ያስደገስነውን ለጣኦት የታረደ በማለት ማንም ሰው ሳይበላው ወጡን የሰሩት እንኳን ለጨው የቀመሱትን እንትፍ በማለት ከውስጣቸው እንዲወጣ ተመኙ። ሁለት ወር በሙሉ በአምኖን ተጠንስሶ የታመቀው በአንድ ጀንበር እንዳልነበር አደረገን። ታሪካችን ተገለበጠ። እናስ ራማ ይሄ ሁሉ የውርደት ካባ በላያችን ሰፍሮ የተሰፋ ጭላንጭል ይታይሻል? አሁን ስመጣ በመንገድ ያገኘኝ ሁሉ ቤተ ክርስቲንን አጭበረበራቹ መቅደስን አረከሳቹ ይሉኝ ነበር። ወይኔ አምኖን እንዳንሞት እንዳንሸሽ አድርጎ ነው በውርተት የሰበረን።

ሌጊዮን፤ በቃ ተረጋጋ የዚህ ያህል መሆን ለጤናህ ጥሩ አይደለም።

አቢሰሎም፦ ጤናዬን የሰጠኝን ክርስቶስን እኮ ነው በሰይጣን የለወጠው። የታቦቱን ክብር ለጣኦት መስጠቱን እየተመለከትኩ እንዴት ልረጋጋ።

ሌጊዮን፦ እንዴ ከሆነ በኋላ ምን ታደርገዋለህ?

አቢሰሎም፦ እገለዋለው /ሁሉም በአን ድምፅ/ ምን?ለሚያመልከው ጣኦት ነው የገዛ ደሙን የምገብርለት። ደግሞ ሰደውልለት ቤተክርስቲያን ነኝ ብሎ ስልኩን ዘጋው /ወደ ስምኦን እያፈጠጠ/ ቅሌቱን የደበከለት ወንድምህ ግን የት እንዳለ ታውቃለህ የዘንዶ ቆዳ ታጥቀው ሰው ይሁኑ ሰይጣን ከማለዩ ጋር በመሆን ቁጤማ ጎዝጉዘው ቡና እየተቀቀሉ የጥቁር ዶሮ አንገት ለጣኦታቸው በመጠምዘዝ እግዚአብሔርን ለማስቀናት ይጥራል። ጫቱን እያቀለጨለጨ የፈጣሪውን ትእገስት ይፈታተናል እገለዋለው ስጋውን አይደለም ምሰጥ የሰማይ አሞራ እና የምድር አራዊት እንኳን ይፀየፉታል ደሙን ማፍሰሴ እሱ የባሰ ህጥያት ከሆን እንደ ቃዬል ተቅበዝባዥ ሆኜ ያየን ሁሉ ያሳደኝ ደሙን በኔ ላይ አድርጎ በጥልክ ውስጥ ይበቀለኝ። /ይነስረዋል/

ስምኦን፡- አፍንጫህ እኮ እየደማ ነው

አቢሰሎም፡- እንዳትጠጋኝ አንተም አብረከው ጎነበስ ቀና ስትል ነበር።

ሌጊዮን፡- ና ታጠብና አረፍ በል /ሌጊየን አቢሰሎም ደግፎ ወደ ውስት ይገባሉ/

ትእማር፡- አበቃልን የዚህ ቤት ታሪክ በዚህ ሲጠናቀቅ መዝገቡ ተዘግቶ ዶሴውም ወደ እሳት ሊጣል ነው

ራማ፡- በጭራሽ። ስለገጠመን እንጂ ስለሚገጥመን እርግጠኛ መሆን አይቻልም። አረኛችን እኮ አይደለም መንጋውን ሊበትን አንዲት ግልገል እንኳንእንድትጠፋበት አይፈልግም እመሩ ዛሬም አይኑ በኛ ላይ ነው። በህይወታችን ፈተና ሊገጥመን እንደሚችል ነግሮናል እርሱ ተፈትኗል። እኛም ለመፈተን የግድ ነው። እኔን አሳደውኛል እናንተንም ያሳድዷችኋል ብሏል እኮ። በባለቤቱ የመጣ በሎሌው ላለመምጣት ምን ይገደዋል እርሱም እኔ አለምን አሸንፌዋለው። እናንተማ ታሸንፉታላቹ ብሎ የማይታጠፍ ቃሉን ሰጥቶናል። ታድያ ማነው መዝገቡን ዘግቶ ዶሴውን የሚያቃጥል እናንተ ሰዎች እምነታቹ ወቴት አለ ጠላትን ባንፈቅድንለት እኛን የማሸነፍ ስልጣን እንደሌለው ታውቃላቹ

ትእማር፡- የኔ ቁስል እንዳላመመሽ ሁሉ የዚህ ቤት እጣም ወደምን አይመራእንደሆነ አልታየሽም እርሱ የሚጠላቸው ሀጣያቶች ሁሉ በዚህ ቤት ተፈፅመዋል እየሽ የዚህ ቤት ንጹህ ፍሬ አንቺ እና እማማናቹ ሌሎቻችን ግን በሀጥያት አንበጣ ተመተናል።

ራማ፡- የኛ ሀጥያት እኮ ከእርሱ ይቅርታ ባይነት አይበልጥም እግዚአብሔር እኮ እንዴት እንደሚሰራ አታውቂም አላዛር ከ 4 ቀን በኋላ ከሞት ይነሳል በሎ ማን ገመተ ማንም። በ 5 እንጀራ እና በ 2 አሰሳ የ 5 ገበያ ህዝብ ይመግባል እኮ የኛ ጌታ። የትኛው ጥበበኛ ነው ውሀን ወደ ወይን የቀየረ፤ እስራኤል ለ 430 አመት በግብፅ ባርነት ውስጥ በደማቸው ራምሴ እነ ጋምሴን፣ ሲገነቡ የራሄል እንባ ታላቁ ሊቀ ነብያተ ሙሴን ከባህር አስነስቶ ነፃ ያወጣቸዋል ብሎ ማን ገመተ፣ ማንምየቃዴስ በረሀ የሲና ሀሩረ ይታለፋል። የኤርትራ ባህርን በአንዲት ዘንግ እንደግንብ አቁሞ ያሻገረን፣ የማይደፈረውን ታላቁን የባቢሎን ገንብ በእልልታ ይንደዋል። እግዚአብሔር ይህን እንደሚሰራ ማን ያውቅ ነበር ማንም የዚህ ቤት ሰላምስ በእማ እንደበት ላይስ ቢሆን ተዘግቶ የሚቀር ይመስላችኋል?የቢታንያን ድንጋይ የበላአምን አህያ ያናገረህ ጌታ ይቻለዋል የእማማን ልሳን መክፈት እሱ ማን ይከለክለዋል። እስመአልቦ ነገር ዘይስህኖ ለእግዚአብሔር። ይህንን የማያምን አለ /ከውጭ አምኖን ይገባል የእናቱን ገልበት ይስማል/

ስምኦን፡- አምኖን ሂድ ከዚ

አምኖን፡- ምን?

ስምኦን፡- ሰምተከኛል

አምኖን፡- አልገባኝም ወዴት ነው የምሄደው?

ስምኦን፡- ወደፈለክበት

አምኖን፡- ለምን?

ስምኦን፡- ሁላችንም በአንተ ድርጊት አዝነናል በበደልህም አፍረናል አቢሰሎም ደግሞ ንደቱከቁጥጥር ውጭ ሆኖ ሊገድልህ ይፈልጋል። ውስጥ ነውና ያለው በቶሎ ከዚህ ሂድ።

አምኖን፡- ምን

ትእማር፡- ልቡ ጥላቻን አመረቀዘ ውስጡ የተቀባው የበቀል ጥላሸት ከጋለ ትንፋሽ ጋር ሲወጣይታያል። የአንተ ቃላተ የማይገልፀው በደል እርጥበት ሲነካው የሚያቃጥል ቁስል በምላሱ ላይ ፈጥሮለታል።

አምኖን፡- እና

ራሚ፡- እናማ ሊገልህ ይፈልጋል ከአይኑ ስር ሽሽ

አምኖን፡- ወዴት ነው የምሄደው?

ትእማር፡- ወደጣኦት ቤትህ

አምኖን፡- ባለ ጣኦቱ ሰውዬ በስራው አልፋ ወነወጀል በፖሊስ ተጠፍንጎ ሄደ። ያቆመውም ጣኦት ከሞቀ ማደርያው ወቶ ለእግዚቢት በመባል ከክሰል ጋር ተጭኖ ተከተለው ከነጭቅቅቴ ወደጌታዬ ብሄድ የገዛ ሀጥያቴ አዳልጦ ይጥለኛል ታድያ ቤቱን እናቴን ትቼ ወዴት ልሄድ? በዛላይ አንቺን ማጣቴ....

ትእማር፡- አንተ

አምኖን፡- አዎ! ከእንግዲ ማንንም አልፈራም። አንቺን ማጣቴ ላይ ቤተሰቤን ማስከፋቴ ተደምሮበት ህይወቴ ስቃይ ውስት ገብቷል። ከዚህ ሁሉ መአት ደግሞ የምድነው ስሞት ብቻ ነው።መድሀኒቴ በአቢሰሎም እጅ ካለ ላገኘው የሚገባኝ እኔ ነኝ። /ወደውስጥ ሊገባ ሲል ስምኦን መንገድ ይዘጋበታል/

ስምኦን፡- አትገባም አይንህን እያየ አይገድልህም በደምህ እጁን በማስታጠብ የዘለአለም ፀፀት አትሁንበት።

አምኖን፡- ስምኦን በምርጫዬ ባተገባ ደስ ይለኝ ነበር አለበለዝያ ግን

ስምኦን፡- አለበለዚያ ምን?

አምኖን፡- አለበለዝያ አንተው ግደለኝ

ስምኦን፡- ይሄ የጨዋታ ጊዜ አይደለም ለእማማ እንኳን ትንሽ አታዝንላትም ምን አይነት ጭንቅላት ነው ያለህ

አምኖን፡- የጭንቅላቴን ውጤትማ እያያችሁት ነው አሳልፈኝ

ስምኦን፡- ትፈነዳ እንደሆን አይሀለሁ አትገባም።

አምኖን፡- ከዚህ በላይ ትእገስቴን እንድትፈታተነኝ አልፈቅድልህም እንደታላቀነትህ የሚገባህ አክበሮት እዚህ ድረስ ብቻ ነው።

ትእማር፡- በማህፀኔ ስለቋጠርከው ፅንስ ስትል ውጣ የዚህ ቤት የከረረች ህልውና ጨርሳ ከመበጠሷ በፊት ለትንሽ ጊዜ እደጅ ቆይ /ከውስጥ አቢሰሎም ይወጣል አምኖንን ሲያየው ፊቱ ይለወጣለ።/

አቢሰሎም፡- አንተ አሪዮስ አይንህን ማየት ሳይሀን በህይወት መኖርህን አልፈልግም /ተንደርድሮ ሊያንቀው ሲል ስምኦን ይይዘዋል/

አምኖን፡- ልቀቀው ይምጣና ይገደለኝ ደሜ ወርደታችሁን ባያጥብም ለኔ ገን ሰላም ነው

ትእማር፡- አረ እግዚአብሔርን ፈርተህ ምናለ ዝም ብትል-?

አምኖን፡- አልልም

አቢሰሎም፡- አንተን ያልገደልኩ እንደሆነ እኔ አይደለሁም። /ሌጊዮን ዝም በሎ ይመለከታል ራማ ከእናቷ አጠገብ ቆማ ጭንቅላታቸውን ሆዷ ላይ ለጥፋ በፍርሀት ትመለከታቸዋለች እናት ያለቅሳሉ አቢሰሎም ስምኦንን መንጭቆ ያስለቅቅና ከምግብ ጠረጴዛው ላይ ቢላዋ ወስዶ አምኖን ሲንደረደር ትማር ድንገተ መሀል ትገባለች አቢሰሎም ለአምኖን የሰነዘረው ቱቤ የትእማርን ሆድ ይወጋል ሁሉም ደንግጠው ይጮሀሉ ትእማር ሆዷን ይዛ አቢሰሎም እገረ ሰር ተዝለፍልፋ ትወድቃለች/

መብራት ይጠፋል

ትዕይንት ስድስት

/መብራት ሲበራ ራማ እና ሌጊዮን ይታያሉ/

ራማ፡- ህልሜ ተፈቶ አየሁት

ሌጊዮን፡- የምን ህልም

ራማ፡- ሁሉም እንዳየሁት ሆነ፡፡ የእማማ እንባ እንደ ጅረት ፈሰሰ የትእማር በድን ፅንስ በሆዷ ውስጠ ፈረሰ፡፡ አቢሰሎም እምኖንን አሳደደው ስምኦንም ግራ የገባው ሆነ

ሌጊዮን፡- አሁንስ ተስፋ ቀረጥሽ መሰል፡፡ ለነገሩ እንዴት አትሸነፊ ፅንስ የቋጠረው ሆዷ በጩቤ ተማስሎ በሞት እና በህይወት መሀል ሆናለች፡፡ አምኖን ብን ብሎ ጠፍቷል ይሙት ይኑር እራሱ አምኖን እንኳን አያውቅም አቢሰሎም ከአይምሮ ውጭ ሆን በእግረ ሙት ታስሮ በፀበል ተወርውሯል፡፡ ስምኦንም የአለማችን ቁጥር አንድ ፈዛዛ ሆኖ ጎዳና ለጎዳና እግሩ ወደመራው ይንከራተታል በዚህ ሁኔታው የለየለት እብድ ይሆናል አልም መኪና ይበላዋል፡፡ እናትሽም ከቀናት አልያም ከሳምንታት የዘለለ እድሜ የላቸውም ታድይ እንዴት ተስፋ አተቆርጪ

ራማ፡- አቤቱ ከምስራቂቱ ከተማ ከታላቋ ኢትዮጵያ ምድር የታናሿ ብላቴንህን ጩኸት ስማ ሁሉ በአንተ የሆነ የሰላም ባለቤት የፍቅር ጌታ የነገስታት ንጉሳቸው ሆይ የገሀነምን ሆድ አጥልቀህ ገነትን አፅድተህ የፈጠርክ ተራሮችን በዝምታህ ያነፅክ ለምድር የብርሀን እና የሙቀት ልኬቷን ለማበጀት የፀሀይን መቃኛዎች በቃልህ ብቻ የበዛ የሆንክ መድህ ሀጥያት በበዛበት ፀጋህ ተበዛለችና በምህረትህ ጎብኘን ክብር ሁሉ ለአንተ እና ለእናትህ ይሁን አሜን፡፡

ሌጊዮን፡- እንደዚህ በጭንቀት እየታመሳቹ በዝምታ የሚመለከት ምን አይነት አምላክ ነው ያላቹ አንዳች ጠብ ሚል ለውጥ እንኳን ካለሳየ ለዚህ ቤት ጌትነቱ የቱ ጋር ነው፡፡ ህ.... ! የሰው ልጅ ነፍስ ከንፋስ ይረቃል መላእክት ደግሞ ከነፍስ እጅግ እረቂቅ ናቸው፡፡ ጌታም ከመላእክት እልፍ አላፍ ረቂቅ ከመሆኑ የተነሳ መላእክት እኳን በእርሱ ዘንድ የተራራ ያህል ግዙፍ ናቸው ይባላል፡፡ ታዲያ ካለ ረቂቅ ስልጣኑ እዚህ ቤት በምህረት እንዳይገባ ከእርሱ እርቀ የከለከለው ምንድን ነው ወይስ እስከነ አካቴው የለም?

ራማ፡- በቃ ሌጊዮን ንግግርህ ሰቀጠጠኝ ድፍረትህ የመጥፊያህን እሳት የሚያቀጣጥል መስሎ ተሰማኝ እንደዚህ ቤተ ክርስቶስን መፈታተን አይቻልም

ሌጊዮን፡- እኔ ነኝ እንዴ የዚህ ቤት ፈተና?

ራማ፡- አዎ ፡፡ እማማ እግር ስር ፊደል አነጠፍኩ ችግሯን በእግሮቿ ጣቶች ፊደሎችን እየጠቀመች አስነበበችኝ፡፡

ሌጊዮን፡- አሃ......! እንደዛ ነው ነገሩ?

ራማ፡- አንተ የእሷ ልጅ አይደለህም?

ሌጊዮን፡- ወልጄ ጣልኩት ብላ እንድትነግርሽ አስበሽ ከሆነ ይሄ ልጅነትሽ ነው፡፡

ራሚ፦ አምኖንንም በመስተፋቅር ነው ይህንነን ሁሉ መአት ያሰራከው።

ሌጊዮን፡ ደግ አደረኩ/ሊወጣ ሲል/

ራሚ፦ ሌጊዮን በእስራኤል ላይ ሚርት በያዕቀሎብ ላይ ድግምት የሚሰራ ይመስልሀል

ሌጊዮን፦ እያየሽው ገና ታያለሽ

ራሚ፦ አምኖን አልጠፋም ከድግምት እስራቱ ይፈታ ዘንድ በፀበል ነው ያለው

ሌጊዮን፦ በፀበል ሊድን ጥሩ ነዋ! /ትቷት ይወጣል/ /ራማ ቤቱን ታስተካክልና ወደውጭ ትወጣለች/ /ሌጊዮን ቀስ ብሎ ወደ ውስጥ ይገባል ሰው እዳልተከተለው ወደውጭ እየተገላመጠ ከኪሱ ጓ ንት አውጥቶ ያጠልቃል/

ሌጊዮን፦ እኔና ይቺን አሮጊት ያገናኘ መልካም አጋጣሚ፣ ከዚህ በላይ እሷን ማሰቃየት ግፍ ነው የሚሆንብኝ ቤቷ ምስቅልቅሉ ሲወጣ እየተመለከተች ልቧን በመፋቅ ጣሯን አብዠቼዋለው አሁን እንደቃሌ ነፍሷ ከስጋዋ የምነጥልበተ ግዜ ላይ ደረሻለው። /ከኪሱ የመርዝ ብልቃጥ እና ሲሪንጅ ያወጣና እየመጠጠ ያወራል/ ከእሷ በማስቀጣል ሁሉንም አንድ በአንድ በያሉበት ከመኖሩ ወደ አለመኖር አሸጋግራቸዋለሁ ያን ጊዜ ሁሉም የኔ ይሆናል ማለት ነው። /መድሀኒቱን ቀድቶ እንደጨረሰ ወደ ውስጥ ይገባል። ራማ ከውጭ ልብስ ይዛ ትገባለች። ታጣጥፍና ወደ ውስጥ ልትገባ ስትል ሌጊዮን ሲወጣ በር ላይ ይገናኛሉ። ደንግጣ ልብሱን ትጥለዋለች።/ ሁሉም ነገር አበቃ! /ራማ እየጮኸች ልትወጣ ስትል አፍኖ መሬት ላይ ይጥላታል።/ ራማ እንደማጠፋሽ ባውቅም እዚህ ቤት ግን ልገልሽ አልፈልግም ነበር። እያዘንኩ ሳጠፋሽ ደስ እያለሽ እናትሽን ተከተያት። /ያፍናታል ራማ ትንፈራፈራለች ከውጭ ከበደ በፍጥነት ይገባል።/

ከበደ፦ ሌጊዮን ተው

ሌጊዮን፦ እገላታለሁ መወገዷ የግድ ነው።

ከበደ፦ /ከብርቱካን ማቅረቢያው ላይ ቢላዋ አንስቶ ወደ ሌጊዮን እየተንደረደረ/ ይህን ቢላዋ ማንጅራትህ ላይ ሳልሰካው ልቀቃት

ሌጊዮን፦ /ይለቃታል ራማ ሮጣ ወደ ውስጥ ትገባለች/ ምን እየሰራህ ነው ከበደ?

ከበደ፡- እየሰራኸው ያለኸው ስራ ትክክል አይደለም። በህይወትህ ትልቅ ስህተት ውስጥ ነው የገባኸው

ሌጊዮን፡- በዚህ ጉዳይ አልተሳሳትኩም። ያመንኩበትን ስላመንክበት ነው በገንዘብ የተቀጠርከኝ። /ራማ ውስጥ ሆና ትጮህለች።

ከበደ፡- ምንድን ነው?

ሌጊዮን፡- ሴትየዋን ገድያቷለሁ

ከበደ፡- አይሆንም

ሌጊዮን፡- እንደማደርገው ታውቃለህ

ከበደ፡- ይህንን ስለማውቅ ነው ሳትገድላት ለመድረስ ስበር የነበረው

ሌጊዮን፡- ለምን

ከበደ፡- እናተህ አይደለችም

ሌጊዮን፡- እኔ እኮ ነኝ የማውቃት

ከበደ፡- አታውቃትም ስለማታውቃት ነው የተሳሳትከው

ሌጊዮን፡- ከበደ

ከበደ፡- ትናንትና ምን እንደነካኝ ባላውቅም ቤተሰቦቼን ለማየት ሀገር ቤት ሄድኩ ያንተንም አሳዳጊ ቤተሰቦች ሰላም ለማለት እቤታቸው ስገባ ወላጅ እናትህን አገኘሁት

ሌጊዮን፡- ሴትየዋ መንፈስ ካልሆነች በስተቀር እንዴት ሊሆን ይችላል

ከበደ፡- እኔም እንዳንተ ነበር የመሰለኝ። እውነታው ግን ሌላ ነው። እናትህም ይቺ ያለበደልዋ የቀጣሀት ሴትዮም ስማቸው ትህትና ነው። እናትህ ይሄ ቤት በተሰራበት ቦታ ላይ ነበር በደሳሳ ጎጆ የሚኖሩት። ችግር ሲበረታባቸው ይህንን ቦታ ትተው ተሰደዱ። የኚህ ምስኪን ሴትዮ ባልም በመንግስት ተመርተው ይህንን ቦታ ገዝተው ቤት ሰርተው መኖር ጀመሩ። /ሌጊዮን ግራ ይጋባል/ መድኃዓለም ልቤን አነሳስቶ ሀገር ቤት የላከኝ ይህንን ቤተሰብ እንድታደግ ስለፈለገ ነው። የአንተ ቀኝ እጅ በመሆኔ ህሊናዬ በፀፀት ነደደ። ይህንን ቤተሰብ መካስ አንተንም ከጥፋትህ ለመመለስ ስል ሳልውል ሳላድር እናትህን ይዤ ወደዚህ መጣሁ። ዛሬ እለቱ ኪዳነምህረት ስለሆነ በቤተክርስቲያኗ ግቢ የተሰበሰበው ምእመን ጠጠር እንኳን መሬት አያስጥልም። የዚህ ሀገር ነዋሪ ይህን ቤተሰብ ጣኦት አምላኪ አድርጎ ነበር የተቀበላቸው። እውነታው ይህ እንዳልሆነ በኔ ተባባሪነት ባንተ አቀነባባሪነት የተደረገውን ነገር ሁሉ ለተሰበሰበው ምዕመን ተናገርኩ። ሁሉም ጉድ አለ ይህን ቤተሰብ ያለበደሉ እንደኮነኑት ሲገባቸው ወይኔ ለኔ ማለት ጀመሩ። በቤተክርስቲያኗ ጠበል ውስጥ የሚገኙትን አቢሴሎምና አምኖንን አስጠርተው ካህናቱም ምእመኑም ይቅርታ

ጠየቋቸው። በዚህ ሰዓት ነበር ሴትየዋን ለመግደል ከራስህ ጋር መቃጠርህ ሲታወሰኝ እናትህን እዛው ትቼ ስበር የመጣሁት። /ራማ ከውስጥ እያለቀሰች ትወጣለች/

ራማ፡- እማን ... እናቴን ገደልካት የመዳንዋን ቀን በተስፋ ስትጠብቅ ደምዋን አቀዝቅዘከው ባዶነት ውስጤን ሞላው እናቴ ድና በፍቅር እጆቿ ሳትዳብሰኝ ገደልካት። ከልጆቿ ነጥለህ በቀዝቃዛ መቃብር እንድትጣል ፈረድክባት። ለምን ሌጊዮን ለምን እማዬ እንባዋ እንደፈሰሰ ጣረ ሞት ሲያሰቃያት ታወሰኝ አፍ ቢኖራት እኮ ልጄ ሆይ አድኚኝ ብላ ትጮህ ነበር። የናቴን የቀዘቀዘ አሬሳ አየሁት እናቴ ብጠራት ላትሰማኝ እጇን ብዘረጋ ላትዳብሰኝ አንቀላፋች። አድጌ ለማየት እንደጓጓች ሞት ቀደማት መሰለኝ። እናቴን መልስልኝ ምነው ከስዋ በፊት ባስቀደምከኝ ወንድሞቼን እህቴንም ነጠልከኝ ብቻዬን ቀረሁ እናት የለኝ አባት የለኝ እኔንም በረደኝ ታናሿን ነፍሴን ወደማይገላት ጌታ ላከኝ። በሰማይ የእናቴን ፍርድ አብሬያት ልካፈል። /ተምበርክካ እያለቀሰች ትፀልያለች ኤሎሄ.... ኤሎሄ.... ለማሰበቅተኒ አቤቱ አልቻልኩም በትከሻዬ የከበደው ተጫነው ተስፋዬ አንተነህና አስበኝ። ተጨንቃ ለምትቃትተው ነፍሴ እረፍትዋ በመዳፍህ ትሁን። አቤቱ በእኔና በእናቴ መሰዋትነት ወንድሞቼን ወደ ልባቸው መልስ። አባት ሆይ ተፈፀመ በል። /በተሰበረ መንፈስ ወደ በሩ ስታመራ

ሌጊዮን፡- ራ......ራማ

ራማ፡- ኑርበት። ትሻው የነበረው ይሄ ሀብትነውና ያንተ ይሁን። ጠፊው ምድራዊው ሀብት እንጂ የሰማይ ዘላለማዊ ፀጋችንን መንጠቅ አትችልም በስጋ እንጂ በመንፈስ ስልጣን የለህም ደግሞ የሰው ላብ ይመራል እንጂ ስለማይጣፍጥ በዘመንህ ሁሉ ያቅርሀል። ያገኘህ የሚያሳድድህ ተቅበዝባዥ ሆነህ ትኖራለህ። ከዘራኸው እንክርዳድ ጋር ፍርድህን በቁና እየሰፈርክ ወየው ለኔ ስትል ትኖራለህ። ሞትን ትመኘዋለህ እንጂ ያለ ጊዜው አታገኘውም። መአትና ቁጣ ሁሉ በራስህ ላይ ይወርዳል እኔም በ 13 ኛ ወንበር ላይ ሆኜ ፍርድህን በህልም ራዕይ የታየኝ ይህ ነው።

ሌጊዮን፡- ራማ .... ራማ.... ራማ

ከበደ፡- ምን አይነት ልጅ ናት

ሌጊዮን፡- ህልመኛ ያየችው ከመሬት ጠብ የማይል ባለ ራዕይ

ከበደ፡- እና ይሄ ሁሉ መአት ባንተ ላይ የሚዘንብ ነው? ጭንቅላትህ ተንኮልን ማምረት እንጂ ራስ ምታት እንኳን መቋቋም እንደማይችል አውቃለሁ። ኦ.... አምላኬ ምን ጥሩ ነገር አለኝና ነው ከክፉ መአት የጠበከኝ እኔ ለራሴ በሀጢያት የተጨማለኩ ቆሻሻፍጡር ነኝ (ከውጭ አቢሴሎምና አምኖን ይገባሉ ሌጊዮን ደንግጦ ያፈገፍጋል።

አቢሴሎም፡- አትሸሸኝ። ላምኖ ተዘንዝሮ ከትእማር የገባው ቢላ ይሰነቀርብኛል ብለህ ከሆነ ተሳስተሀል። ንፅህናችን በአደባባይ ተመስክሮ ያጣነው ሲመለስ የበቀል ስሜቴን እንደ ትቢያ ተኖ ጠፍቷል ወንድሜን ለመግደል የተነሳው እጄ እሱን በፍቅር ሲዳብስ ለአንተም ለይቅርታ ተዘርግቷል

አምኖን፡- በሙሉ አይንህ ተመልከተኝ፡፡ ከፊትህ የቆመው አንተ የቀረፅከው ሳይሆን የቀድሞ የእግዚአብሔር ባርያ ነው፡፡ ከእንግዲህ ሊቀ መዝሙርነቱ ላንተ አይደለም፡፡ ራማ በዮሀንስ ወንጌል ስታስተምረኝ "የቀድሞ ፍቅርህን ተተህል እና ሳይመጣብህ በጊዜ ተመለስ" ያለችኝ አንተ ፊት ነበር፡፡ ወደቀድሞ ልጅነቴ መመለሴን ደግሞ እፊትህ ቆሜ አረጋግጥልሀለሁ፡፡ ለከፋው በደሌ የመረረ ቅጣት ቢገባህም አንተ እኛን ከቀጣኸን በላይ ክርስቶስ በአይሁዳዊያን ተቀጥቷል፡፡ የሱ ቅጣት ከእኛ ጋር ሲነፃፀር ምንም ነው፡፡ ምንም ታወቃለህ በቃ ባዶ፡፡ ታዲያ እሱ ለገዳዮቹ ይቅርታ ሰጥቶ አንተን የምንበቀልህ እኛ ማን ነን ይቅር ባይም ተቀባይም እሱ፡፡ /ትእማር ከውጭ ትገባለች/

አቢሴሎም፡- የማይታመን ነገር እንዴት ሊሆን ይችላል፡፡

ትእማር፡- በሰው የማይቻል በእግዚአብሔር ይቻላል፡፡ ራማ በዛች በጭንቅ ሰዓት እንኳን " እስመአልቦ ነገር ዘይሰሀኖ ለእግዚአብሔር" ትል ነበር አምላከ ቅዱሳን መድኃኔዓለም እኔን ከሞት መንጋጋ ፈልቅቆ ለማውጣት ምንተስኖት፡፡ ሁላችሁም ዶክተሩ ያላችሁን ቃል ሰምታችሁ ሞቴን ነበር የምትጠባበቁት እሱ ከፈቀደ እንኳን የታመመ የሞተ ይነሳል፡፡

አቢሰሎም፡- ትእማር ያቆሰልኩሽ እኔነኝና ይቅርታሽን ስጪኝ /እግሯ ስር ሊወድቅ ሲል እያነሳችው/

ትእማር፡- ሆን ብላ የፈፀምከው ነገር የለም ከቁስሌ በላይ የነበረው ጎድቻታለሁ ብለህ እንደምትጨመቅ ስለሚገባኝ ነው ህመሜ

አቢሴሎም፡- በህመምሽ ውስጥ የኔን ጭንቀት ማዳመጥ በመቻልሽ በእውነት ትልቅ ሴት ነሽ፡፡

አምኖን፡- ትእማር በእንባዬ ተጠምቄ አዲስ ሰው ሆኗለሁ፡፡ ሌጊዮን የድግምት ጭቃ አይኔን ቀብቶት እህትነትሽን ከልሎት በፍቅር እንድመለከትሽ ቢያደርገኝም በእመቤቴ ፀበል ትብታቤ ተበጣጥሶልኝ የአይኔ ሰንኮፍ እንደሰም ቀልጧል፡፡ ክብር ሁሉ ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ከነ አንድያ ልጇ ይሁን

ትእማር፡- ሌጊዮን ያሁሉ የጠነሰስከው መከራ ታለፈ ልትለኝ አስበህ እንጂ አልሞትንም፡፡ ፈቃድ ሁሉ በሰው ልጆች ፍቃድ ቢሆን ኖሮ በምኞት ስካር ባለቅን ነበር፡፡ እየህ ሁሉም ይለወጣል ቀሻሻይፀዳል፣ የታመመ ይድናል፣ የሞተም ይነሳል፣ የተበጠሰም ይገመዳል፣ የወደቀም ፍሬ ይበቅላል፣ ስንዴውን ያነቀው አረም ሲነቀል ተከትሎት የበቀለውን እንክርዳድ አብሮት ይነቀላል፡፡

ከበደ፡- በትክክል፡፡ የተዳፈነው የዚህ ቤት ፀጋም እንደዚህ ተመልሷል፡፡ ጠላታችሁ አይኑ እያየ ነው እግዚአብሔር የባረካችሁ፡፡ ይህ ቤተሰብ እምነት፣ ፍቅር፣ ተስፋ፣ ሰላምና ርህራሄ የተዘራበት አዝመራ ነው፡፡ ፍሬዎቹን እናንተንጠላት ለሰላሙ ሁከትን፣ ለርህራሄው ጭካኔን ዘራበት የእርሻው ባለቤት የናቡቴ ጌታ ግን አረሙን ከስሩ ነቀለው፡፡ ገና መኮትኮቿውንም ያቃጥለዋል፡፡ /አቢሴሎምን፣ አምኖንና ትእማር ይተቃቀፋሉ/ VO በዚህ ደስታቸው መሀል እንዴት ነው የእናታቸውን ሞት የምታበስራቸው? ከሬት የመረረ እውነታውን ሲጋቱት ልባቸው ላይጠገን ዳግም ይቆስላል፡፡

ሌጊዮን፡- ጠባቡ ጭንቅላቴ ሊፈነዳ ተወጠረ፡፡ ነፍሴ ስጋዬን በማዘልዋ ተጨነቀች፡፡ የራማ ራዕይ መፈፀሚያዋ ጊዜ ደረሰ መሰል በሀጢያቴ ያበቀልኩት እሾክ የገዛ ልቤን ቧጠጠው /እያቃሰተ ሽብረክ ብሎ ይንበረከካል አምኖን ሊያነሳው ሲል/ ተው አምኖን ባለቀ ሰዓት አዲስ ምዕራፍ ስለመከፈቱ የማወቅ ተስፋ አልነበራችሁምና የዚህ ቤት ሀዘን ጨርሶ ማብቃቱን ሳታረጋግጥ አታንሳኝ

አምኖን፡- እንስማዋ ለዚህ ቤት ያልተነሳላት ሽክም ምንድን ነው? ከዛሁሉ መአት ተሰንጥሮ በመዳኒታችን ሳትወገድ የቀረች ምን አይነት ሀዘን ይሆን

ሌጊዮን፡- እ.... እ.... እናታችሁን ......

አቢሴሎም፡- ጨርሰዋ እንስማሀ

እናት፡- ሰላም ለእናንተ ይሁን (አቢሴሎም፣ አምኖን እና ትእማር በአንድ ላይ) ምን!

ትእማር፡- የማይታመን ነገር (ሁለቱም እናታቸው ላይ ይጠመጠማሉ ሌጊዮንና ከበደ ይተያያሉ/

አቢሴሎም፡- የእጅሽን እስራት በጥሶ እንደበትሽን ከፍቶ ያሰማን እንዴት ያለ ድንቅ ተአምር ነው።

እናት፡- እግዚአብሔር ድንቅ አምላክ ነው። በሞቱ ህይወትን የሰጠ በገዳይ መርዝ ውስጥ ፈዋሽ መድሀኒትን አዘጋጀ። ሌጊዮን ያለበደልህ ስለፈፀምከብኝ ግፍ እንዳልወቅስህ በአንድ በኩል ፈውሰኸኛል። የእንባ ከረጢቴን እንዳልሸነቆርከው መልሰህ ደዌዬን ባልጠበከው ሞቴን ባትደግስ ባልዳንኩ ነበር። "ከሚባላው ውስጥ ጣፋጭ የሚበላ ወጣ" ያለው ሳምሶን ይህንን ነው። ራማም ይህ እውነት አንድ ቀን እዚህ ቤት ሊፈፀም እንደሚችል ብርቱ እምነት ነበራት። እለቱም ዛሬ ነው። የቤቴን ሰላም የልጆቼን ፍቅር ዳግም ያሳየኝ የድንግል አንድያ ልጁ የተመሰገነ ይሁን ይኸው በሱ ተአምር ባንተ ገቢር እየተናገርኩ መንቀሳቀስ ችያለሁ። ሌጊዮን ያንተ ካብራኬ አልተከፈልከም። እነሱም የመንፈስ እንጂ የስጋ ወንድሞችህ አይደሉም። ይህንን ብታውቅ ኖሮ ሀብት እንኳን እንደማያሳስትህ አምናለሁ። እውነት እንኳን ቢሆን የሰው ልጅ እንዲበቀል አልተፈቀደለትም። የታሉ ሰምኦንና ራማ

አቢሴሎም፡- አልተገናኘንም /ከውጭ ትህትና ትገባለች

ከበደ፡- ሌጊዮን እሰዋ ናት እናትህ

ሌጊዮን፡- /ሲያያት በንዴት ፊቱ ይለዋወጣል/ አንቺ..... አንቺ ሰይጣን /ሊያንቃት ሲንደረደር

ትእማር፡- ሌጊዮን! /ሌጊዮን ይቆማል/

ትህትና፡- /እየተጠጋችው/ ልጄ

ሌጊዮን፡- እንዳትጠጊኝ። አሁንስ ያሳረፍሽብኝ ጠባሳ በዛ። አንቺን ለመበቀል ስል እነሱን አቆሰልኩ። ለመጥፊያቸው በጥልቀት የቆፈርኩት ጉድጓድ ለኔው ሆኖ አረፈው። እሰዋ ናት ጥፋተኛ መጥፎ ሰው እንድሆን ያደረገችኝ። እሰዋ ናት! የነሱ አይን ያቃጠለኝ ይበቃኛል ከፊቴ ዞር በይ

አምኖን፡- ይቅርታ አድርግላት።

ሌጊዮን፡- ምን አልክ?

አቢሴሎም፡- ሰምተኸዋል

ሌጊዮን፡- አላደርገውም

ትእማር፡- ሌጊዮን

ሌጊዮን፡- በጭራሽ

አምኖን፡- እስዋ በደለችን ከምትለው በላይ አንተ እኛን አልበደልከንም? እኛ ይቅርታ ሰጥተንህ ለምንድን ነው አንተ ይቅርታ ማድረግ የተሳነህ? የሰራዊት አምላክ እኮ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ ይላል። ከህጎች ሁሉ የበላይ ደግሞ ይቺ ናት ይቅር በላት

ትህትና፡- /ትህትና ሌጊዮን እግር ስር እየተንበረከከች ልጄ ንፁህ ይቅርታህን አግኝቼ ብሞት እንኳን ለኔ ህይወት ነው። እባክህን እራሴን ቀጣሁት ይበቃኛል። በህይወት ዘመኔ እስካገኝህ ድረስ ልቤ በቁጭት እየነደደ ደሜ በትኩሳቴ እየፈላ ያቃጠለኝ መኖሬ ከኔ በስተቀር ለማንም ያልተሰጠ ቅጣት ነው። ይህን እያወክ በዝምታ ካለፍከኝ ለማንም ያልተሰጠ ደንዳናና ጨካኝ ልብ ነው ያለህ።/ ሌጊዮን ከአጠገቧ ዞር ብሎ/

ከበደ፡- እስኪ ሁላችንም የይቅርታን ጣፋቅ ፍሬ እርስ በርሳችን በመጎራረስ አዲሱን የህይወት ምዕራፍ እንጀምር።

አቢሴሎም፡- አንድ ቀን አለም በቃኝ በማለት ሁላችንም ገዳም ለመግባት እናስብ ነበር። ዛሬ ያጊዜ ደርሶ የማብቂያው ታላቅ ደውል ጮኸ/ ከእንግዲህ እምነታችን ብቻ ሳይሆን ሀብታችንም እግዚአብሔር ብቻ ነው። አብርሃም ከካራን ሲወጣ ብቻውን ነበር። እኛም እንዲሁም ክርስቶስን ብቻ ወደምናገኝበት ገዳም እንሄዳለን። /ወደ ከበደ እየተጠጋ/ አንተ የዚህ ቤት መከራ መገኘት ልታበስር ከኖህ መርከብ ላይ በእግዚአብሔር የተላክ የሰላም እርግባ ነህ። የዚህን ቤት እሳት አንተን ልኮ ሲያቀዘቅዝ ውርደታችን ሁሉ ተገፈፈ። ወደ ገዳም ስንገባ ሌጊዮን ካልተከተለን ንብረታችንን በሙሉ ለማውረስ ያሰብነው ለሱ ነበር። አሁን ግን ወዳጄ ሆይ ሀብት ንብረታችን በጠቅላላ ያንተ ነው። በምድር የሰጠንህን በሰማይ ቤት ገንባበት።

ሌግዮን፡- ወይኔ.... አልቻልኩም.... አልቻልኩም /ትቷቸው ይወጣል/

ትህትና፡- ልጄ.... ልጄ /ተከትላው ትወጣለች

ከበደ፡- ይህን ተዝቆ የማያልቅ ሀብት ስለሰጣችሁኝ አመሰግናለሁ። ሀብታም መንግስተ ሰማያት ከሚገባ ይልቅ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢሾልክ ይቀላል ያለው ጌታ ከእዮብ በስተቀር ነው። እኔ ደግሞ እንደ እዮብ ትእግስተኛና ብርቱ ስላልሆንኩ በዘመናት ውስጥ ነዋይ ሊያሸንፈኝ ይችላል። ኢየሱስም ያንን ባለ ፀጋ ሀብት ንብረትህን ሸጠህ ተከተለኝ እንዳለው አደርገዋለሁ። እኔም እንደናንተ ሀብት ንብረቴ እግዚአብሔር ይሆናል። /ራማና ስምኦን ይገባሉ/ የራማ ፊት በደስታ ይበራል።

ራማ፡- ጌታ ሆይ እኔ አላምንም /ተንደርድራ እናትዋ ላይ ትጠመጠማለች ሁሉም በአንድነት ይተቃቀፋሉ/

ተፈፀመ

ወስብሀት ለእግዚአብሔር፣ ለወላዲተ ድንግል፣ ወለመስቀሉ ክብር አሜን።